
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3567 | ቅዳሜ መጋቢት 26 ቀን 2018 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር




# የመጋቢት ብስራት

- የተለያዩ ዕይታዎች እና መረዳት ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲ አባላት ስልጣን መጋራታቸው ሀገርን የመገንባት ሂደት ያጠናከረ ተግባር መሆኑ ተመላክቷል



ግራፊክስ በዳንኤል ተስፋይ

በኢትዮጵያ ያለፉት 8 ዓመታት የተለያየ እሳቤ ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ለሀገራዊ ጥቅም በጋራ የሰሩበት ታሪካዊ ክስተት ነው

**በመለሰ ተሰጋ**

የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም ኃይላት የመጨረሻ ግባቸው ስልጣን ይዞ ያሰቡትን በተግባር ላይ ማዋል እንደሆነ የፖለቲካል ሳይንስ ምሁራን ይናገራሉ፡፡ በዓለማችን በተለያዩ ክፍሎች የሚገኙ ፖለቲከኞችም ስልጣንን በተለያዩ መስመሮች እየጨበጡ ህዝብን በአሉታም ሆነ በአዎንታ መንገድ ሲያስተዳድሩ ማየት የተለመደ ነው፡፡

በአንዳንድ የዓለማችን ክፍል በተለይም በአፍሪካ ፖለቲካ ኃይሎች ስልጣንን በውድም በግድም ከያዙ በኋላ እንደ ነብር ጅራት ሆኖባቸው ለመልቀቅም ሆነ ለማካፈል ሲንገዳገዱ ማየት አዲስ ነገር አይደለም። በዚህም አፍሪካ በፖለቲካ ፓርቲዎች ሽኩቻ አንድ እርምጃ ወደፊት ሁለት ወደኋላ እየተጓዘች ዘመናት ነጉደዋል፡፡

ለዚህ ደግሞ በአፍሪካ ፖለቲካ እና በመንግስት ስርዓቶች ላይ ባደረጓቸው የተለያዩ ጥናቶች የሚታወቁት ፈረንሳዊው የፖለቲካል ሳይንስ ተመራማሪው ፕሮፌሰር ዣን-ፍራንሷ ባዋርት 'The State in Africa' በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ 1989 ያሳተሙትን ጥናታዊ መፅሐፍ በዋቢነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## በተግባር የተገለጠው የመሪነት ሚና

14



ፎቶ- ከፋይል

5ኛው የአዲስ መሶብ አዲስ ከተማ ቅርንጫፍ የምረቃ ሥነስርዓት

## ከሸማችነት ወደ አምራችነት የተሸጋገሩ ከተሜዎች

15



ፎቶ- በገነት ወንድሙ

አቶ ለማ ስሜ ዶሮዎችን ሲንከባከቡ

## የዓለም ዝነኞች ተመራጭ መዳረሻ

11



ፎቶ- ከገፀ ድር

ዝነኛው አሜሪካዊ የራፕ ሙዚቃ ኮከብና የዲጂታል ይዘት ፈጣሪ ዲዲጂ የዓድዋ ድል መታሰቢያን ሲጎበኝ

# ማህበራዊ ፍትሕን የማንገስ አብነቶች

**"የተሰበሩ ማህበራዊ እሴቶችን በማከም ማህበራዊ ፍትሕ እንዲነግስ የሚያስችሉ በርካታ ውጤቶች ተመዝግበዋል"**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ**

**በመለሰ ተሰጋ**

አዲስ አበባ ልክ ከዘመናት እንቅልፍ እንደመንቃት፣ አሊያም የመቃብርን ድንጋይ ፈንቅሎ እንደመውጣት፣ በድቅድቅ ጨለማ እንደሌት ጨረቃ ፈክቶ እንደመታየት፣ ጉስቁልናውን እና እርጅናውን አሽቀንጥሮ ጥሎ በማራኪ ውበት፣ በአስደማሚ ጉልበት ታጅቦ እንደሚነሳ ንስር አሞራ የኋላ ቀርነትን ጨለማ ሰብራ እንደ ንጋት ኮከብ ደምቃ ትታያለች፡፡

በተለይም ሰውን ማዕከል ባደረጉት ፕሮጀክቶቿ

ወደ ገጽ 5 ዞሯል



ፎቶ- ከገፀ ድር

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ከለውጡ ወዲህ የተመዘገቡ ስኬቶች የጋራ ጥረት ውጤቶች መሆናቸውን አመላክተዋል




# የአዲስ አበባ የተምሳሌትነት ምስጢር

- በመዲናዋ 24 ሰዓት፤ በሳምንት ሰባት ቀን መስራት ባህል እየሆነ መጥቷል


**በስንታየሁ ምትኩ**

አዲስ አበባ በሰሉ እጆች ጥረት ልክ እንደ ስሟ ውብና አበባ እየሆነች መጥታለች፡፡ መንገዶቿ የሚያሳሱ፣ ፅዱ፣ ውብና ንፁህ ሆነዋል፡፡ ህንፃዎች፣ አረንጓዴ ስፍራዎች፣ ዘመናዊ የመንገድ መብራቶች፣ የተሽከርካሪ ማቆሚያዎች ልዩ ገፅታንና ውበትን አላብሰዋታል፡፡ ወንዞች ወደ ቀደመው ወዝና ማንነታቸው ተመልሰዋል፡፡

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

**አድራሻ** +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

# ርዕሰ አንቀፅ



## ሀገራዊ ለውጡ ተምሳሌታዊት ከተማን ወልዷል!

ኢትዮጵያ ሀገራዊ ለውጥ ውስጥ ከገባች እነሆ ስምንት ዓመታት ተቆጥረዋል። በእነዚህ ዓመታት ውስጥ በተለይም አዲስ አበባ ስሟንና ዝናዋን የሚመጥን እና የታሪክ አቅጣጫን የቀየረ አስደናቂ የለውጥ ጉዞ በማድረግ ላይ ትገኛለች። ቀደም ሲል በጠባብ መንገዶች፣ በቆሻሻ አወጋገድ ችግሮችና የከተሜነት ደረጃዋን በማይመጥን መሰረተ ልማት ትታወቅ የነበረችው ከተማ፣ ዛሬ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚደነቅ ውበትን ተላብሳለች። ይህ ለውጥ በአጋጣሚ የመጣ ሳይሆን፣ ግልጽ ርዕይን ሰንቆ በተተገበረው የኮሪደርና የወንዝ ዳርቻ ልማት እንዲሁም ታላላቅ ፕሮጀክቶችን በጥራትና በአጭር ጊዜ የማጠናቀቅ ስትራቴጂ የተገኘ ውጤት ነው።

የአዲስ አበባን አዲስ ገጽታ የፈጠረው ትልቁ ምስጢር “የሥራ ባህል” ነው። ከተማዋ በቀን ብቻ ሳይሆን በሌሊት፣ በሳምንት ሰባት ቀን ለ24 ሰዓታት ያለማቋረጥ የመሥራት ልምድን እያዳበረች ትገኛለች። ይህ አዲስ የሥራ ባህል ቀደም ሲል ዓመታትን ይወስዱ የነበሩ ፕሮጀክቶችን በ60፣ በ90 እና በ120 ቀናት ውስጥ ለማጠናቀቅ አስችሏል። በከፍተኛ አመራሩ የሚደረገው የቅርብ ክትትልና ድጋፍ፣ ችግሮችን በቦታው ላይ ሆኖ የመፍታት ልምድ ለስኬቱ የጀርባ አጥንት ሆኗል። ይህም አዲስ አበባን ጠንካራ የሥራ ባህል ካላቸው የጃፓንና ደቡብ ኮሪያ ከተሞች ተርታ እንድትሰለፍ እያደረጋት ይገኛል።

መዲናዋ እያከናወነች ያለው ልማት ውበትን ብቻ ሳይሆን ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ያረጋገጠና አካታች ነው። በ2017 በጀት ዓመት ብቻ መንግስት በራሱ እና ህብረተሰቡን በማሳተፍ 19 ሺህ በላይ ፕሮጀክቶች አጠናቅቆ ለአገልግሎት በቅቷል። በ2018 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት ደግሞ ከ12 ሺህ በላይ ፕሮጀክቶች ተከናውነዋል። እነዚህ ስራዎች ከመንገድና መብራት ዝርጋታ ባለፈ ለህፃናት፣ ለወጣቶች፣ ለአረጋውያንና ለአካል ጉዳተኞች ምቹ የሆኑ መሠረተ-ልማቶችን ያካተቱ ናቸው። በተጨማሪም የቤት ፍላጎትን ለማርካት 100 ሺህ ቤቶችን ለመገንባት ታቅዶ በ18 ሳይቶች እየተከናወነ ያለው ሰፊ ስራ የዜጎችን ኑሮ ለማሻሻል ያለውን ቁርጠኝነት ያሳያል።

አዲስ አበባ ዛሬ የዲጂታላይዜሽንና የስማርት ሲቲ ግንባታን በማፋጠን ላይ ትገኛለች። እንደ ሳይንስ ሙዚየም፣ ዓድዋ ድል መታሰቢያ፣ አንድነትና እንጦጦ ፓርኮች ያሉ ግዙፍ ፕሮጀክቶች ከተማዋን ለኮንፈረንስ ቱሪዝም፣ ለንግድና ኢንቨስትመንት ምቹ አድርገዋታል። የኮሪደር ልማቱ የእግረኛ፣ የሳይክልና የተሽከርካሪ መንገዶችን በዘመናዊ መልኩ በማስተሳሰር የከተማዋን እንቅስቃሴ አዘምኗል። ይህ የልማት ጉዞ በጊዜ መጓተት ምክንያት ይባክን የነበረን በጀት በመቆጠብና የዋጋ ንረትን በመቀነስ ረገድም ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ እያስገኘ ይገኛል።

በአጠቃላይ፣ ባለፉት ስምንት ዓመታት የተመዘገቡት ድሎች አዲስ አበባን ለኢትዮጵያም ሆነ ለአፍሪካ ከተሞች የለውጥ ተምሳሌት አድርገዋታል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ “ከተሜ፣ ከተሜነት፣ ከትመትና የኮሪደር ልማት” በሚል ርዕስ በቅርቡ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክን ጨምሮ በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን በተላለፈው ቃለ ምልልሳቸው “አዲስ አበባ በስም ብቻ ሳይሆን በተግባርም አብባለች” ንግግራቸው የከተማዋን ወቅታዊ እውነታ በሚገባ ይገልጸዋል። ይህንን ስኬት ዘላቂ ለማድረግና ምርታማነትን ይበልጥ ለማሳደግ፣ አሁን የተጀመረውን ህዝባዊ የሥራ ባህልና የልማት ተነሳሽነት አጠናክሮ ማስቀጠል የሁላችንም ድርሻ ሊሆን ይገባል። አዲስ አበባ የጀመረችው የብልጽግና ጉዞ ለሌሎች ከተሞችም ተስፋንና መነሳሳትን የሚሰጥ ታላቅ ምሳሌ ነው።

# የእኔ እይታ

**ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።**

## የምርጫ ካርድ መውሰድ መብት ወይስ የዜግነት ግዴታ?

### በቸርነት ዋለልኝ ከአራብሳ

ምርጫ የአንድ ሀገር የዴሞክራሲ ስርዓት መገለጫ ነው፡፡ የዴሞክርሲ ስርዓት ግንባታን ውጤታም ከሚያደርጉት ተግባራት ውስጥ አንዱ ፍትሐዊ እና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ማድረግ ነው፡፡ ይህም የአንድን ሀገር ሕዝቦች ከሰለጠነ ማህበረሰብ ጎራ ከሚያሰልፉቸው ተግባራት ውስጥ ግንባር ቀደም ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፤ እናም በህዝብ ቅቡልነት ያገኘና የተመረጠ መንግስት እንዲያስተዳድረው የምርጫ ካርድ መውሰድ የዜግነት ግዴታና ኃላፍነት ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ ይህን ርዕሰ ጉዳይ ያነሳሁት ያለምክንያት አይደለም፡፡

ሰሞኑን የ7ኛው ጠቅላላ ምርጫ የመራጮች ምዝገባ ጊዜ መሆኑ ይታወቃል። ብዙዎቻችን ይህንን ሂደት እንደ አንድ ቀላል ተግባር ልንቆጥረው እንችላለን። ሆኖም ግን፣ በአንድ ወቅት ከቅርብ ወዳጄ ጋር ያደረግነው ጨዋታ አንድ ትልቅ ትዝብት ጭሮብኛል።

በሳምንቱ መጨረሻ የእረፍት ቀን ሻይ ቡና እያልን ሳለ፣ የምርጫ ካርድ መውሰዴን ስነግረው፣ እርሱ ግን “በህይወቴ መርጨም ሆነ ካርድ ወስጄ አላውቅም” በማለት በኩራት ተሞልቶ አጫወተኝ፤ እኔም ንግግሩን ቀበል አድርጌ እንግያውማ መብትህን በገዛ እጅህ አልተጠቀምክበትም አልኩት፡፡ ይህ ንግግሩ አንድ ጥያቄ እንዳነሳ አደረገኝ፤ ካርድ አለመውሰድ በእርግጥም መብትን መጠቀም ነው? ወይስ መብትን አሳልፎ መስጠት?

በመረጡት ሰው መመራትና ባልመረጡት ሰው መመራት ልዩነት እንዳለው ሁሉ፣ የመረጡት ሰው ብቻ ያስተዳድራል ማለትም አይደለም፤ ለምርጫ ከቀረበው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወንበር አብላጫውን በያዘው እንጂ፡፡ እናም የፖለቲካ ፓርቲዎች ምርጫ ቦርድ ባስቀመጠላቸው አግባብ መሰረት በሚያቀርቡት የየራሳቸው አማራጭ ሀሳብ ላይ ተመስርቶ ሀገሪቱ የሰጠችውን መብት ተግባራዊ ማድረግ የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት ነው ብዬ አስባለሁ።

ምርጫ ካርድ መውሰድ የዜግነት መብትም ግዴታም ነው፡፡ ዴሞክራሲ የሚገነባው በታዛቢነት ሳይሆን በተሳታፊነት ነው። እያንዳንዱ ካርድ የራሱ ክብደትና ትርጉም አለው፤ የብዙዎች ‘አንድ ካርድ’ ተደምሮ ነው የሀገርን አቅጣጫ የሚቀይረው።

በመሆኑም በየምክንያቱ ከምርጫ ካርድ የምንርቅ ዜጎች፣ መብታችንን ለሌሎች አሳልፈን እየሰጠን መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል እላለሁ። ዛሬ ካርድ መውሰድ ነገ በኩራት የምንጠይቅበትን ሞራል መገንባት መሆኑን አምነን ግዴታችንን እንወጣ።

በጥቅሉ የምርጫ ካርድ መያዝ የአንድ ወረቀት ባለቤት መሆን ሳይሆን የሀገር ዕጣ ፈንታ ባለቤት መሆን ነው። እንዲሁም ምርጫ ካርድ መውሰድ ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ‘መግቢያ ትኬት’ እንደሆነ ይሰማኛል። ያለ ትኬት ደግሞ ጨዋታውን መታዘብ እንጂ በውጤቱ ላይ ተፅዕኖ ማሳደር አይቻልም። መምረጥ የምንፈልገውን መንግስት ለመሰየም ብቻ ሳይሆን፣ የማይወክሉንን ሀሳቦች ‘አይወክሉኝም’ ለማለት የምንጠቀምበት ዋነኛ መሣሪያችን ነው።

ጓደኛዬ እንዳደረገው ከምርጫ ካርድ መራቅ እና ካርዱን ባለመውሰድ መብቱን እንደተጠቀመ ቢሰማውም፣ እውነታው ግን መብቱን አሳልፎ መስጠቱ ነው። እንዲሁም በሌሎች ውሳኔ ለመመራት ፈቃደኝነትን እንደማሳየት ይቆጠራል። ስለዚህ እኛ ግን መብታችንንም ሆነ ኃላፊነታችንን ተረድተን፣ በ7ኛው ጠቅላላ ምርጫ ድምፅ አልባ ከመሆን ይልቅ፣ ካርዳችንን በመያዝ ለሰለጠነ የፖለቲካ ስርዓት ግንባታ የድርሻችንን እንወጣ መልዕክቴ ነው።

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እየተዘጋጀች

ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን
የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ

ግንቦት 1985 ዓ.ም
ተመሰረተች

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት
በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ዳንኤል ተስፋይ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ፋንታነሽ ተፈራ
ይግለጡ ጓዴ
ሸዋርካብሽ ቦጋለ
ለይላ መሀመድ

**ዋና አዘጋጅ**
ተካልኝ አማረ
Tekalignteke123@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር B91/17

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለሰ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ




# ለፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ቅስቀሳ የተዘጋጀ

## ኢትዮጵያን ወደ ተምሳሌት ሀገር፡- ከመደመር ዕሳቤ እስከ ሁለንተናዊ ብልጽግና




ኢትዮጵያ ባለፉት ጥቂት የለውጥ ዓመታት የመጣችበት ጉዞ፣ ፈተናዎችን እንደ ምሽግ ሳይሆን እንደ ድልድይ በመጠቀም ወደ ላቀ ከፍታ ለመሸጋገር የተደረገ ጥረት ነበር። ይህ ጉዞ የሀገሪቱን የታሪክ አቅጣጫ የቀየረና በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች የዴሞክራሲ ጥማቸውን ያረጋገጡበት 6ኛው ሀገራዊ ምርጫ በስኬት መከናወኑ ሕያው ማሳያ ነው። የዚህ ሁሉ ለውጥ ማዕከል ደግሞ የቆዩ ስብራቶችን የሚጠግንና የነገውን ጉዞ የሚያቀናው የ"መደመር" ፍልስፍና እና የብልጽግና ፓርቲ መመሥረት ነው።

### የታሪክ እርቅ እና የጋራ ትርክት ግንባታ

የብልጽግና ፓርቲ መሪ ዕሳቤ የሆነው መደመር፣ ቀደምት የሀገሪቱን የታሪክ እሴቶች ከዘመናዊ የዲሞክራሲ ግንባታ ጋር በማዋሃድ የጋራ ሀገራዊ ትርክትን ለመገንባት ያለመ ነው። ይህ ፍልስፍና ኢትዮጵያ የነጠላ ትርክት ውጤት አለመሆኗን በመገንዘብ፣ አሰባሳቢና አቅም ደማሪ በሆነ መንገድ የተዛቡ የታሪክ አረዳዶችን በመመካከር ለመፍታት ይሠራል።

### በዚህ ረገድ የተከናወኑ ተጨባጭ ተግባራት የለውጡን ቁርጠኝነት ያሳያሉ፡-

- **የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን መቋቋም፡-** ለዘመናት የቆዩ መሠረታዊ ልዩነቶችን በውይይት ለመፍታት ታሪካዊ እርምጃ ተወስዷል።
- **የታሪክ ቅርሶች እድሳት፡-** የዓድዋ ድል መታሰቢያ እና የአንድነት ፓርክ ግንባታ ዜጎች ያለፈውን ታሪካቸውን በኩራት እንዲገነዘቡና ለጋራ የወደፊት ጉዟቸው እንዲነሳሱ እያደረገ ይገኛል።
- **የፖለቲካ ምህዳሩን ማስፋት፡-** "ተቃዋሚ" የሚለውን የጥላቻ ስያሜ በ"ተፎካካሪ" በመተካት እና በስደት የነበሩ የፖለቲካ ኃይሎች ወደ ሀገር እንዲመለሱ በማድረግ አካታች ሥርዓት ተዘርግቷል።

### ከጎራ ፖለቲካ ወደ አካታች ብሔራዊ አንድነት

ቀደም ሲል የነበረው የአብዮታዊ ዲሞክራሲ አስተሳሰብ የቡድን መብትን ብቻ በማጉላት በዜጎች መካከል መጠራጠርን ፈጥሮ ነበር። የመደመር ዕሳቤ ግን "አጋር" ተብለው ከውሳኔ ሰጪነት ተገልለው የነበሩ ክልሎችን (ሶማሌ፣ አፋር፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላና ሐረሪ) ወደ መሀል በማምጣት የአንድ ሀገራዊ ፓርቲ ባለቤት እንዲሆኑ አድርጓል። ይህም በዳርና በመሐል መካከል የነበሩ የልዩነት ግንቦችን አፍርሷል።

### የምጣኔ ሀብት አብዮት እና ግዙፍ ፕሮጀክቶች

የመደመር ኢኮኖሚ ሞዴል ሙሉ በሙሉ በመንግሥት የሚመራ ወይም ለገበያ ብቻ የተተወ ሳይሆን፣ የመንግሥትን የቁጥጥር ሚና ከግል ዘርፉ ተሳትፎ ጋር ያቀናጀ ነው። በዚህም ዘርፈ-ብዙ ስኬቶች ተመዝግበዋል፡-

- **የስንዴ አብዮት፡-** ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በበጋ መስኖ ስንዴ በማምረት ራሷን ለመቻልና ወደ ውጭ ለመላክ በቅታለች።
- **ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን፡-** የአፍሪካ የመጀመሪያው የሰው ሠራሽ አስተውሎት (AI) ኢንስቲትዩት መቋቋምና የ"ፋይዳ" ዲጂታል መታወቂያ አሰጣጥ የቢሮክራሲ ማነቆዎችን እየቀነሱ ነው።
- **የአረንጓዴ አሻራ፡-** በአካባቢ ጥበቃ ረገድ የታየው ተዓምር የዜጎችን የ"እንችላለን" መንፈስ አድሷል።

### የወደፊት ተስፋና ቃል ኪዳን

ምንም እንኳ እንደ ሀገር የሰላም እጦት፣ የኑሮ ውድነት እና የመልካም አስተዳደር ጉድለቶች አሁንም ተግዳሮት ቢሆኑም፣ እነዚህ ችግሮች ከድሮው ሥርዓት የተወረሱና በሽግግር ወቅት የሚከሰቱ መሆናቸውን ፓርቲው ይገልጻል። ብልጽግና እነዚህን ችግሮች "በወርቃማው አማካይ" መርህ ለመፍታት ቁርጠኛ ነው።

### ለቀጣዮቹ ዓመታት የተነደፈው ፍኖተ-ካርታ ግዙፍ ግቦችን አካቷል፡-

- **የቢሾፍቱ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ፡-** በ2030 በዓመት 110 ሚሊዮን መንገደኞችን የማስተናገድ አቅም ይዞ እንዲጠናቀቅ ይደረጋል።
- **የማዳበሪያና ነዳጅ ማጣሪያ ፋብሪካዎች፡-** በጎዴ የዩሪያ ማዳበሪያ ፋብሪካን ጨምሮ በሀገር ውስጥ ምርትን ለማሳደግ ታቅዷል።
- **የኤአይ (AI) ዩኒቨርሲቲ፡-** ወጣቶችን በዘመናዊ እውቀት ለማነጽ የቴክኖሎጂ ማዕከል ይገነባል።

### ሁሉም ያለውን አቅም ለሀገር ግንባታ የሚያውልበት፣ ማንም የማይገፋበት ሥርዓት ለማስፈን ብልጽግናን ይምረጡ!!!

- ብልጽግናን ይምረጡ!
- ብልጽግናን መምረጥ...... የኢትዮጵያን ከፍታ መምረጥ ነው።
- ምልክታችን የስንዴ ነዶ ነው።
- የስንዴ ነዶ የመደመር፣ የትብብር እና የአንድነት ምልክት ነው።
- ኢትዮጵያን ወደ ተምሳሌት ሀገር!

**ይህ ቦታ ለነፃነት እና እኩልነት ፓርቲ እንዲሁም ለሱማሌ ፌዴራሊስት ፓርቲ ምርጫ ቅስቀሳ የተሰጠ ቢሆንም ፓርቲዎቹ የቅስቀሳ ጽሑፍ ባለማምጣታቸው ጋዜጣው ከዚህ በታች ያለውን የራሱን ጽሑፍ አስተናግዶበታል።**

## ምርጫ፡- የዜጎች የሥልጣን ባለቤትነት ምንጭ

**በቶለሳ መብራቴ**

በዓለም አቀፍ የፖለቲካ ተሞክሮ ውስጥ የአንድ ሀገር የብልጽግና እና የሰላም ዋስትና የሚመነጨው ከዜጎች ቀጥተኛ ተሳትፎ ነው። ከእነዚህ የዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ መስኮች መካከል ደግሞ ምርጫ የዜጎችን የሥልጣን ባለቤትነት የሚያረጋግጥበት ዋነኛውና ቀዳሚው መሣሪያ ነው።

ምርጫ የዲሞክራሲ ማገር ብቻ ሳይሆን፣ ዜጎች የሀገራቸውን የወደፊት አቅጣጫ በነፃነት የሚቀርጹበት ታላቅ የሥልጣኔ መገለጫ ነው። ይህ ፖለቲካዊ ሂደት ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ ግንባታ የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ ሲሆን፣ ሂደቱም ተዓማኒነትን የሚያረጋግጡ ወሳኝ ምዕራፎችን ማለፍ ይጠበቅበታል።

የፖለቲካ ምርጫ ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ ብልጽግና፣ ዘላቂ ሰላምና ለሉዓላዊነት መከበር ያለው ሚና የማይተካ ነው። ይህ ሂደት ዜጎች በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን የሥልጣን ባለቤትነት በተግባር የሚያረጋግጡበት ዋነኛውና ታላቁ የዲሞክራሲ መገለጫ ነው።

ምርጫ ሕዝቡ የሚያስተዳድሩትን መሪዎች በነፃነት የሚሰይምበት መድረክ ብቻ ሳይሆን፣ መንግሥት ከሕዝብ የሚቀበለው 'ሕጋዊ ውክልና' (Legitimacy) ዋነኛ ምንጭ ነው። ይህ ዴሞክራሲያዊ ሂደት በመንግሥት እና በዜጎች መካከል ያለውን የውል ስምምነት የሚያጸና መሠረት ነው።

የምርጫን አስፈላጊነት ከሚያሳዩ ተጨባጭ ማሳያዎች መካከል አንዱ የመንግሥታት ሕጋዊነትና ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት ነው። ያለ ምርጫ የሚመጣ ሥልጣን ፋይዳ-ቢስ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ እንደ ኖርዌይና ስዊዘርላንድ ያሉ ሀገራት በምርጫ ስኬታቸው አማካኝነት የገነቡት ፖለቲካዊ መረጋጋት ለሌሎች ሀገራት ትልቅ ትምህርት የሚሰጥ ነው።

ምርጫ የፖለቲካ ሥልጣን ሽግግርን ከደም መፋሰስ እና ከጦርነት አዙሪት የሚያድን ዲሞክራሲያዊ መሣሪያ ነው። ታሪክ እንደሚነግረን በሥልጣን ሽኩቻ ምክንያት የሚፈጠሩ ጥፋቶችን መግታት የሚቻለው፣ የሥልጣን ባለቤትነት በጠመንጃ ሳይሆን በዜጎች ነፃ ድምፅ ሲረጋገጥ ብቻ ነው።

ሰላማዊ የምርጫ ሥርዓት ለኢኮኖሚ ዕድገት መሠረት መሆኑን እንደ ጋና እና ሴኔጋል ያሉ የምዕራብ አፍሪካ ሀገራት በተግባር አሳይተዋል። የሥልጣን ሽግግርን በስምምነትና በሕዝብ ድምፅ ማከናወናቸው፣ ከጦርነት ይልቅ ለልማት ቅድሚያ እንዲሰጡ አስችሏቸዋል።

የምርጫ ሥርዓት መኖር ባለሥልጣናት ለሕዝብ ጥያቄ ምላሽ እንዲሰጡ የሚያደርግ 'ዴሞክራሲያዊ ሚዛን' ነው። መሪዎች በየአራት ወይም አምስት ዓመቱ በድምፅ የመሸነፍ ዕድል እንዳለ ሲያውቁ፣ ለገቡት ቃል ታማኝ እንዲሆኑና ለአሠራራቸውም ተጠያቂነት እንዲሰፍን ይገደዳሉ።

ምርጫ ዜጎች የፓርቲዎችን የፖሊሲ አማራጮች የሚመዝኑበት ታላቅ አጋጣሚ ነው። ሕዝቡ በተለያዩ የትምህርት፣ የጤና እና የኢኮኖሚ ዕቅዶች ላይ በመመስረት በመረጃ የተደገፈ ውሳኔ እንዲያስተላልፍ በማድረግ፣ የሀገሪቱን ቀጣይ የጉዞ አቅጣጫ በድምፁ ይቀርጻል።

የምርጫ ጥቅም የሚረጋገጠው ሂደቱ ነፃና ፍትሐዊ ሲሆን ነው። ሂደቱ የሚጀምረው በመራጮች ምዝገባ ሲሆን፣ ይህም ድምፅ የመስጠት መብታቸው የተጠበቀ ዜጎች በሙሉ እንዲመዘገቡ በማድረግ ሰፊ የሕዝብ ተሳትፎ እንዲኖር መሠረት ይጥላል።

ምዝገባው ከተጠናቀቀ በኋላ ደግሞ የዕጩዎች ክርክር የሚካሄድበት መድረክ ይዘጋጃል፤ በዚህም የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ዓላማቸውንና የፖሊሲ አማራጮቻቸውን ለሕዝብ በማብራራት፣ መራጩ ሕዝብ በቂ መረጃ ኖሮት በትክክለኛው ግንዛቤ ላይ ተመሥርቶ እንዲመርጥ ይረዳዋል።

ዋናው የምርጫ ቀን ሲደርስ ደግሞ ድምፅ የመስጠት ተግባር ይከናወናል፤ ይህም ሂደት እያንዳንዱ ዜጋ ፍላጎቱን ያለምንም ተፅዕኖ በነፃነት መግለጽ እንዲችል በሚስጥር ድምፅ የሚሰጥበት አግባብ ነው።

በመጨረሻም፣ የተሰጠው ድምፅ በግልጸኝነት ተቆጥሮ አሸናፊው የሚታወቅበት የውጤት ማሳወቅ ደረጃ ይከተላል። ይህ የመጨረሻ ምዕራፍ የሕዝቡን ውሳኔ በይፋ በመቀበል ለሥልጣን ሕጋዊነትን የሚሰጥና ሉዓላዊነቱን የሚያረጋግጥበት ወሳኝ ሂደት ነው።

በአጠቃላይ፣ ምርጫ የሥልጣን ባለቤትነቱ የሕዝብ መሆኑን የሚያረጋግጥ፣ ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግርን የሚያሰፍንና መሪዎች ለሥራቸው ተጠያቂ እንዲሆኑ የሚያደርግ ወሳኝ መሣሪያ ነው።

ይሁን እንጂ የምርጫ ጥቅም በተሟላ ሁኔታ ሊገኝ የሚችለው ሂደቱ ከምዝገባ እስከ ውጤት ማሳወቅ ድረስ ነፃ፣ ፍትሐዊና ግልጽ ሲሆን ብቻ ነው። በመሆኑም፣ እያንዳንዱ ዜጋ ይህንን መብቱን ተጠቅሞ ለሀገሩ የሚበጀውን የፖለቲካ አማራጭ በመምረጥ ረገድ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት ሊወጣ ይገባል።

**ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ**

## የመደመር ዕሳቤ ለኢትዮጵያ ፍቱን መፍትሔ




መደመር ማለት ካለን ነገር ላይ የተሻለውን ወስደን፣ ጎጂውን ጥለን፣ አዲስ ነገር በመጨመር ነገን የተሻለ የማድረግ ጥበብ ነው። ብልጽግና ፓርቲ በሚቀጥለው ምርጫ የሕዝብን ድምፅ በማግኘት፣ ኢትዮጵያን ካለፈው የጥል ትርክት አውጥቶ ወደ ጋራ ብልጽግና ለማሸጋገር ቃል ኪዳኑን ያድሳል።

### በጋራ ትርክት ወደ ጋራ ከፍታ ለመጓዝ ብልጽግናን ይምረጡ!

- **ብልጽግናን ይምረጡ!**
- **ብልጽግናን መምረጥ...... የኢትዮጵያን ከፍታ መምረጥ ነው።**
- **ምልክታችን የስንዴ ነዶ ነው።**
- **የስንዴ ነዶ የመደመር፣ የትብብር እና የአንድነት ምልክት ነው።**
- **ኢትዮጵያን ወደ ተምሳሌት ሀገር!**

# የመጋቢት ... ከገጽ 1 የዞረ

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክም “የነብርን ጅራት አይዙም፤ ከያዙም አይለቁም” ይሉት አባባል ሰምሮ የፖለቲካ ፓርቲዎች ስልጣንን ከያዙ አይለቁም። ለሌሎችም አያካፍሉም፡፡ በዚህም የኢትዮጵያን ከፍታ ሳይሆን የራሳቸውን ጥቅም ብቻ እያስቀደሙ ሀገርን ለከፋ ችግር መዳረጋቸውን የተለያዩ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡

መጋቢት 24 ቀን 2010 ዓ.ም የለውጡ መንግሥት ሀገራዊ ኃላፊነትን የተረከበበት ታሪካዊ ቀን ነው፡፡ ታዲያ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ትብብርና በጋራ የመሥራት ባህል እንዲዳብር መደረጉን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ለአብነትም የፖለቲካ ፓርቲዎች የተለያዩ ዕይታዎች፣ አሰላለፎች እና መረዳቶች ቢኖሯቸውም ለጋራ ሀገር ብሔራዊ ጥቅምን መሠረት አድርጎ በትብብር ለመሥራት ሥልጣን እስከማጋራት የተደረገው ጥረት አዲስ ፖለቲካ ባህልን ያዋለደ ተግባር ነው ሲሉ ዓለም አቀፍ ተቋማት ሳይቀር መስክረውለታል፡፡

ለአብነትም ቢቢሲ ጥቅምት 7 ቀን 2021 ይዞት በወጣው ዘገባ “አዲስ በተመሰረተው የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አስተዳደር ካቢኔ ውስጥ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ከተቋቋመ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የተቃዋሚ አመራሮች በሚኒስትርነት ተሹመዋል” በማለት የነገሩን አዲስነትና ታላቅነት ዘግቧል፡፡

በወቅቱም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርበው እንዲሾሙ ካደረጓቸው 22 ሚኒስትሮች መካከል ሦስቱ በተለየ መልኩ ከተለያዩ የተቃዋሚ ፓርቲዎች የመጡ ናቸው። ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር) የትምህርት ሚኒስትር ከኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)፣ በለጠ ሞላ (ዶ/ር)፣ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ከአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) እና አቶ ቀጀላ መርዳሳ የባህልና ስፖርት ሚኒስትር ከኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ) ናቸው። ይህም ቀደም ሲል በሀገሪቱ ባልተለመደ መልኩ የተከናወነ እንደነበር የቢቢሲ ዘገባ ያመለክታል፡፡

ይህንንም ተከትሎ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ባስተላለፉት መልዕክት “የብልጽግና ፓርቲ አባል ባይሆኑም ሀገራቸውን በቅንነት፣ በብቃት እና በታማኝነት ማገልገል የሚችሉ ዜጎችን በካቢኔ ውስጥ የማካተት ስራ ተጠናክሮ ይቀጥላል” ብለዋል፡፡ በተከታታይነትም ከብልፅግና አባላት ውጭ ለሆኑ ለተለያዩ እና ብቃት እንዳላቸው ለታመነባቸው ኢትዮጵያውያን ልዩ ልዩ ሹመቶች እንደተሰጡም ይታወቃል፡፡

በወቅቱም በኢትዮጵያ ፖለቲካ ባልተለመደ መልኩ የተፎካካሪ ፓርቲ አመራሮች በሚኒስትርነትና የተለያዩ ኃላፊነቶች ላይ ተሹመው እያገለገሉ መሆኑን ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በቀጣይም ተመሳሳይ ዕድሎች የሚሰጡ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ ይህ ቃል በተግባርም ተጠናክሮ መቀጠሉን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡


ግራፊክስ በዳንኤል ተስፋይ
በኢትዮጵያ ያለፉት 8 ዓመታት የተለያየ እሳቤ ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ለሀገራዊ ጥቅም በጋራ የሰሩበት ታሪካዊ ክስተት ነው

በአምቦ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር ሰኔሳ ታደሰ ከአዲስ ልሳን ጋዜጣ ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደገለፁት፣ በምርጫ ያሸነፈው ፓርቲ የተወሰደው እርምጃ በሀገሪቱ ፖለቲካ እንቅስቃሴ ላይ አዲስ ምዕራፍን የከፈተ ነው፡፡

የአማራ ብሄራዊ ንቅናቄ (አብን) ሊቀመንበር በለጠ ሞላ (ዶ/ር) በወቅቱ የተሰጣቸውን ሹመት አስመልክቶ እንደተናገሩት ደግሞ፣ ከ6ኛው ሀገራዊ ምርጫ በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በኢትዮጵያ ውስጥ በምርጫ የሚሳተፉትን የተፎካካሪ ፓርቲዎችን በፅህፈት ቤታቸው ጋብዘው በቀጣይ አዲስ መንግስት ምስረታ ሲደረግ እስከ ዛሬ በመጣንበት መንገድ ላለመሄድ መንግስታዊ አቅጣጫ እያስቀመጠን ነው፤ በማለት ሀሳባቸውን እንዳካፈሏቸው ያስታውሳሉ፡፡ እንደ በለጠ ሞላ (ዶ/ር) ገለፃ፣ ይህንን ውሳኔ ማድነቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ውሳኔ አዲስ ነው፡፡ ለውጥ እንዲመጣ ይፈልጉ የነበሩ ኃይሎች ይናፍቁት ነበርም ብለዋል፡፡

ፕሬፌሰር ብርሃኑ ነጋ በበኩላቸው፣ በወቅቱ የተሰጣቸውን ሹመት አስመልክቶ እንደገለፁት ትምህርት ሚኒስቴር ትልቅ ተቋም ነው፡፡ በመሆኑም በአዘቦት ጊዜ ከሚደረግ የፖለቲካ ፉክክር ባሻገር በዚህ ጊዜ ተባብሮ ሀገርን ለማዳን መስራት ከጤነኛ ሰው ይጠበቃል ማለታቸው አይዘነጋም፡፡

ከዚህ በፊት የፖለቲካ ባህላችን ሆኖ የቀጠለው አንድ ሰው ሚኒስትር አይደለም በቀበሌና በወረዳ ደረጃ ሕዝብን ለማገልገል ሹመት ሊያገኝ የሚችለው፣ ኃላፊነት የሚሰጠው የግድ የፖለቲካ ፓርቲ አባል በተለይ ደግሞ ያሸነፈው የፖለቲካ ፓርቲ አባል መሆን እንደ ግዴታ ይወሰድ እንደነበርም የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር ሰኔሳ አስታውሰዋል፡፡

ይህም በመሆኑ በዕውቀት ላይ የተመሰረተ አገልግሎት ከመስጠት ይልቅ በስሜት፣ በግለሰብ እና በቡድን ፍላጎት ብቻ እንዲመራ ይደረግ ነበር፡፡ በዚህም በጉዳዩ ወይም በቦታው ላይ ልምድ የሌላቸው ሰዎች በስሜት እና በፈለጉት መንገድ የራሳቸውን ፍላጎት በህዝብ ላይ የሚጭኑበት ሁኔታዎች እንደነበሩ እና ይህም ሀገርን በብዙ መልኩ እንደጎዳም አውስተዋል፡፡

የዓለም ባንክ “World Development Report 2017: Governance and the Law” በሚል ርዕስ በ307 ገፅ ይፋ ያደረገው መረጃ ላይ እንዳሰፈረው ሥልጣንን የሚጋሩ የፖለቲካ ኃይላት በመካከላቸው ጤናማና ሚዛናዊ ቁጥጥርና መልካም ውድድር እንዲኖር ያደርጋሉ፡፡ የሀገራቸውን ፖለቲካዊ አስተዳደር በማሻሻል እና ሰላምን በማስፈን ኢኮኖሚያዊ ውጤት ያስገኛሉ።

የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ባለሙያውም በዚህ ሀሳብ እንደሚስማሙ ገልፀው፣ አሁን ስልጣን በምርጫ በያዘው ፓርቲ አባል ያልሆኑ ሰዎች በሚኒስትር ደረጃ ተመርጠው ትልቅ ሀገራዊ ኃላፊነት ሲሰጣቸው ይህ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያ ነው ብለዋል፡፡

የተለያዩ ዕይታዎች፣ አሰላለፎች እና መረዳቶች ያላው የፖለቲካ ፓርቲ አባላት ስልጣን መጋራታቸው በዕውቀት ላይ የተመሰረተ ሀገርን የመገንባት ሂደትን የሚያጠናክር ነው፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥም ጠቃሚ ያልሆኑ፣ እንደ ባህል የተወሰዱ ድርጊቶችን እና ልማዶችን የሚያስወግድ ነው፡፡ የፖለቲካ ባህላችንን ከስር መሰረቱ የሚቀይር ጥሩና የአዲስ ምዕርፍ መጀመሪያ እንደሆነም ተናግረዋል፡፡

ለህዝብ እና ለሀገር የሚያስብ ቡድንና ግለሰብ ይህንን ያደርጋል የሚሉት የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህሩ፣ ስልጣንን በዚህ መልኩ ማካፈል ሀገር በሁሉም ዘርፍ አሸናፊ ሆና እንድትቀጥል የሚያደርግና ኢትዮጵያን የፖለቲካ ባህል የሚቀይር እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር ሰኔሳ ታደሰ ልምድና እውቀት ላላቸው ሰዎች ይህን መሰል ዕድል መስጠት እንደ ሀገር ትልቅ ጥቅም ያለውና የፖለቲካ ፓርቲዎችም ትምህርት ሊወስዱበት የሚገባ ነው ብለዋል፡፡

አክለውም ይህንን መሰል አሰራር በሌሎች ዓለማትም ያለ በመሆኑ ዘመኑ ከደረሰበት ስልጣኔ ጋር አብረን መጓዝ አለብን፡፡ ፖለቲካ ፓርቲዎችም ይህንን እውነት መቀበል አለባቸው፡፡ ምክንያቱም አንድ ፖለቲካ ፓርቲ ሲመሰረት ስልጣን ይዜ ሀገሬን እና ህዝቤን አገለግላለሁ፤ ሀሳቤን እና ፍላጎቴን አራምዳለሁ ብሎ ነው፡፡

ታዲያ ይህን ብሎ ወደ ስልጣን የመጣው ፓርቲ ሀገር እንድታሸንፍ የእኔ አባላት ባይሆኑም የተሻለ ብቃት ስላላቸው በሚል መስፈርት ስልጣኑን ሲያካፍል ግለሰቦችም በተሰጣቸው ዕድል ህዝባቸውን ማገልገል እና በመካከላቸውም ለአንድ ሀገር እንደሚያስቡ ህዝቦች መተያየት አለባቸው፡፡

አክለውም ኢትዮጵያ እንደ ዘመናዊ ሀገር ከተመሰረተችበት ጊዜ አንስቶ ባለው ታሪክ ስልጣን ከአንዱ ወደ አንዱ የሚሸጋገረው በዚህ መልኩ አልነበረም። በተለይ ለአንድ ሀገር እንደሚሰራ ሳይሆን እንደ ጠላት የሚተያዩበት ነበር፡፡ አሁን ግን ተፎካካሪ የምንላቸው ኃይሎች ስልጣንን በዚህ መልኩ ሲያካፍሉ በታሪካችን ያየናቸው የግጭት አዙሪቶች እየተቀረፉ እንደሚሄዱም አመላክተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አሕመድ (ዶ/ር) ለተፎካካሪ ፓርቲዎች ስልጣን በተጋራበት ወቅት ለምክር ቤቱ አባላት ባስተላለፉት መልዕክት የኢትዮጵያ ፖለቲካ እሳቤ ያላቸው ሰዎች የሚሰደዱበት፣ የሚጣሉ እና አሸናፊ ብቻ የሚገዛበት ሁኔታ መቀየር አለበት ካልን ይህ ትልቅ ነገር ነው ማለታቸው ይታወሳል፡፡

# ማህበራዊ ... ከገጽ 1 የዞረ

በርካቶችን እንባ እያበሰች፣ ደስታቸውን እየመለሰች ስለመሆኑ አያሌ ምስክሮችን ማንሳት እንችላለን፡፡ ወደ ትናንት ብዙም ርቀን ሳንሄድ በከተማዋ ማዕከላዊ ስፍራ የዶሮ ማነቂያን ያለፈ ጎስቋላ መልክ ስንመለከት በርግጥም ከተማዋ በአቦ ሸማኔ ፍጥነት ራሷን ምን ያህል እያዘመነች እንደሆነ እንመለከታለን፡፡ ሁሉም ነገር የሚሰራው ለሰዎች ደስታ ነውና ከአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ጋር ቆይታ ያደረጉ የመዲናዋ ነዋሪዎች ይህንን እውነት ይመሰክራሉ፡፡

ወይዘሮ ሮማን ጌታቸው በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 በተለምዶ ዶሮ ማነቂያ አካባቢ በልማት የተነሱ ነዋሪ ናቸው፡፡ ባለትዳር እና የአራት ልጆች እናት የሆኑት ወይዘሮ ሮማን በዶሮ ማነቂያ አካባቢ ለ40 ዓመታት ኖረዋል፡፡ አኗኗራቸው ግን ሰው ለመኖር ከሚገባው በታች ነበር፡፡ በአንድ ግቢ ውስጥ ከ20 በላይ አባወራዎችና እማወራዎች ይኖሩ እንደነበር የሚያስታውሱት ወይዘሮ ሮማን በኮምፖርሳቶ እና በካርቶን የተከፈለች የይስሙላ ቤት ውስጥ እየኖሩ አንድን መጸዳጃ ቤት ደግሞ ለ40 ሰዎች እንደሚጠቀሙ በማስታወስ አሁን ግን የከተማ አስተዳደሩ ከዚህ ሁሉ መከራ እንደታደጋቸው ይናገራሉ፡፡

ትናንት በዶሮ ማነቂያ ከቤት ውስጥ ወደላይ ቆጥ ተሰርቶ ሰው እንደዶሮ በቆጥ አልጋ ውስጥ እንኖር ነበር፡፡ ፒያሳ ፊት ለፊት ያማረች ከተማ ብትመስልም ውስጥ ውስጡ ግን ሲኦል ነበር ባይ ናቸው፡፡

ባለቤታቸው ህመምተኛ በመሆናቸው በአልጋ ላይ ይውሉ እንደነበር ገልጸው፣ ከምግብ ቤት የሚያገኟትን ገቢ ለባለቤታቸው የህክምና ወጪ ያወጡም ነበር፡፡ በቀሪ ገቢያቸው ቤተሰባቸውን ያስተዳድራሉ፡፡ ከረጅም ጊዜ የአልጋ ቁራኛ በኋላ ባለቤታቸውን በሞት አጥተዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ለእነ ወይዘሮ ሮማን ህይወት ፈታኝ ሆኖባቸው እንደነበር አስታውሰዋል፡፡

መኖሪያ ቤታቸው እና አካባቢያቸው ቦታው ጠባብ በመሆኑ እንደፈለጉ ለመንቀሳቀስ አስቸጋሪ ነበር፡፡ ቤታቸው አልጋ አያዘረጋም ነበር፡፡ አራት ልጆችን ይዞ አልጋ በማታዘረጋ ትንሽ ቤት መኖር ምን ያህል ፈታኝ እንደነበር ጠቁመዋል። ቀን ለሶፋ ማስቀመጫ ማታ ደግሞ ለመኝታነት ይጠቀሙበታል፡፡

ክረምት ፍሳሽ እና ብርድ ይፈራረቅባቸው እንደነበር አስታውሰው፣ በ21ኛው ክፍለ ዘመን የሰው ልጆች ይኖሩበታል ተብሎ በማይታሰበው መኖሪያ ቤት ውስጥ እና አካባቢ ህይወታቸውን ይገፉ እንደነበር ተናግረዋል፡፡ የጋራ ሽንት ቤታቸው ፈርሶ በባልዲ ይጠቀሙም ነበር፡፡

የሽንት ቤት ሽታ ለጤናቸው ጠንቅ ሆኖባቸው ነበር፡፡ እስከ ቤታቸው ድረስ የሚያስገባው መንገድም ምቹ ባለመሆኑ የታመመ ሰው ወደ ህክምና ቦታ ለማድረስ በጀርባቸው አዝለው ያወጡ ነበር፡፡ ከህክምና ቦታ የሞተ ሰው ደግሞ ወደ ቤት ሳይገባ በዚያው ወደ ቀብር ቦታ ይወስዱ ነበር፡፡ በሰፈራቸው አካባቢ እና በቤታቸው ህይወት ምንያህል



ፎቶ- ከገፀ ድር
በአዲስ አበባ ከተማ ማህበራዊ ፍትሕን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል

ፈታኝ መሆኑን በትዝታ ወደ ኋላ በመሄድ የነበረውን ማህበራዊ ውስብስብ ችግር በአዲሱ ቤታቸው ሆነው አስታውሰዋል፡፡

ዛሬ ወይዘሮ ሮማን ከፒያሳ ዶሮ ማነቂያ አካባቢ በልማት የተነሱ የአንድ አካባቢ ነዋሪዎች በሰባ ደረጃ አካባቢ በተሰራው ምቹ የመኖሪያ ስፍራ አዲስ ሕይወትን እየመሩ ነው፡፡

የዝግጅት ክፍላችን በተለያዩ የከተማዋ አካባቢዎች ተዘዋውሮ እንደተመለከተው ከተማዋ በቅርብ ዓመታት ውስጥ አሮጌ መልኳን እንደ ንስር አድሳ፣ አዲስ ግርማና ሞገስን ተላብሳለች፡፡ አዲስም፣ አበባም ሆናለች፡፡ እነ እሪ በከንቱ፣ እነ ካዛንቺስ፣ እነ ዶሮ ማነቂያ፣ እነ ተረት ሰፈርን የመሳሰሉ አካባቢዎች የትናንት ጎስቋላ መልካቸው እንደ ደመና ተገፍፎ አዲስ ድምቀትን እየተላበሱ ነው፡፡

እነዚያ ጭንቅንቅ ያሉ መንገዶች፣ ጣሪያቸው ያረጀ፣ ማገራቸው የላላ፣ ምሶሷቸው ያዘመመ እና ባለ ላስቲክ ግድግዎቹ የደቀቁ ስፍራዎች በውብ መናፈሻዎች፣ በሰፋፊ መንገዶች እና በሰማይ ጠቀስ ህንፃዎች እየተተኩ ነው። በእርግጥም አዲስ አበባ ገና ከጫጉላ ቤት እንደወጡ ሙሽሮች፣ እንደ ቀይ ሐር ፈትል፣ በለምለም መስክ ላይ እንደሚቦርቁ እንቦሶች እና እንደ ተከፈለ ሮማን ዐይንንም ልብንም እየማረከች ነው፡፡ በዚህ ውበት ውስጥ ደግሞ እየነገሰ ያለ ማህበራዊ ፍትሕ ይታያል፡፡

አንድም የሰዎችን መኖሪያ ምቹ በማድረግ፣ የእለት ጉርስ ለቸገረው ደግሞ ልክ እንደ መማፀኛ ከተማ የሚያገለግሉ የምገባ ማዕከላትን በማቋቋም እንዲሁም ለሀገር ተረካቢው ትውልድ የትምህርት ቤት ምገባን ተግባራዊ በማድረግ፣ ደሳሳ ጎጆዎችን ብቻ ሳይሆን የነዋሪውን መንፈስ በልዩ ልዩ መልኩ በማደስ የተሰሩ ማህበራዊ ፍትሕን ማንገሻ ልማቶችን መጥቀስ እንችላለን፡፡

ለአብነትም በጉለሌ ክፍለ ከተማ እንጦጦ አካባቢ የተገነባው የጉለሌ የተቀናጀ ስራን መጥቀስ እንችላለን። ይህ ልማት በዋነኛነት በአካባቢው እንጨት ከጫካ በመልቀም ለሚተዳደሩ የአካባቢው ነዋሪዎች የስራ ዕድል የፈጠረ ነው፡፡ መቼም በእንጦጦ ተራራና አካባቢው ወገባቸው በዕድሜና በእንጨቱ ሸክም ጎብጦ የእንጦጦን ብቻ ሳይሆን ለቤተሰቦቻቸው ሲሉ የኑሮን አቀበት ሲወጡ ሲወርዱ የነበሩ እናቶች የሚረሱ አይደሉም፡፡

ታዲያ ይህ ፕሮጀክት የታደገው እነዚህን እናቶችና ቤተሰቦቻቸውን ነው፡፡ ማዕከሉ 450 ዘመናዊ የእንጀራ መጋገሪያ ምጣድ የተገጠመለት፣ ዘመናዊ የሊጥ ማቡኪያ ማሽን፣ ዘመናዊ የአብሲት መጣያ ማሽን እና ሁለት ወፍጮዎች ያሉት ሲሆን፣ ከ550 በላይ እናቶች ወደ ስራ ገብተው በተሻለ የሕይወት ምዕራፍ ላይ እንደሚገኙ ቀደም ሲል ከዲስ ልሳን ጋዜጣ ጋር ቆይታ ያደረጉት የጉለሌ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ወልዴ ወገሴ ይናገራሉ፡፡

ባሳለፍነው ሐሙስ (መጋቢት 24 ቀን 2018 ዓ.ም) ደግሞ ሀገራዊ ለውጡ የተበሰረበትን 8ኛ ዓመት አስመልክቶ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች በነቂስ ወጥተው ድጋፍ አድርገዋል፡፡ ድጋፉንም አስመልክቶ አዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ "የተሰበሩ ማህበራዊ እሴቶችን በማከም ማህበራዊ ፍትሕ እንዲነግስ የሚያስችሉ በርካታ ውጤቶች ተመዝግበዋል። በተለይም በከተማችን የሚገኙ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ወገኖችን በተለይም የሀገር ባለውለታዎችን፣ አቅመ ደካሞችን፣ አካል ጉዳተኞችንና ረዳት የሌላቸውን ወገኖች ከአስቸጋሪ ኑሮ አውጥተን የሰውን ክብር በሚመጥን መልኩ እንዲኖሩ አድርገናል" ብለዋል፡፡

አክለውም፣ "የለውጥ ፍሬዎች ዋንኛ ተጠቃሚ የሆነው የአዲስ አበባ ህዝብ ማልዶ ወደ አደባባዮች በመውጣት የዘወትር ድጋፉን እንደገና አጽንቷል። ጅማሬያችን ትናንት ቢሆንም ከህዝባችን ጋር ያሳካነው ድል እና የደረስንበት ርቀት ቀላል አይደለም" ብለዋል ከንቲባዋ፡፡

በከተማዋ እየተከናወኑ ያሉ ማህበራዊ ፍትሕን የማንገስ ጥረቶችን አስመልክቶ ከአዲስ ልሳን ጋር ቆይታ ያደረጉት በወራቤ ዩኒቨርሲቲ የማህበራዊ ሳይንስ ትምህርት ክፍል መምህር አንዋር ጫሚሶ እንደገለፁት፣ በከተማዋ እየተከናወኑ ያሉ እንዲህ አይነት ሰው ተኮር ተግባራት ማህበራዊ መስተጋብሩን እውን ለማድረግ እንደሚያግዙና የሀገሪቱን ልማት በተሻለ መሰረት ላይ ለማንበርም ትልቅ ድርሻ አላቸው፡፡

የማህበራዊ ሳይንስ ምሁሩ እንደሚሉት ብልፅግናን ለማረጋገጥ እንደ ሀገር ከተቀመጡት የዘላቂ ልማት ግቦች መካከል አንዱ አካታች የሆነ ዕድገት ማምጣት ነው፡፡ ይሄውም ሴቶችን፣ አካል ጉዳተኞችን ወይም ለተለያዩ ማህበራዊ እና መሰል ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን አካታች በሆነ መልኩ መስራት ሀገራችን አሁን የምታደርገውን ጥረት ምልዑ ለማድረግ ያግዛል፡፡

እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የህብረተሰቡን መሰረታዊ ችግሮች ለመቅረፍ እየተሰሩ ያሉ ዘርፈ ብዙ ልማቶች የሚበረታቱ መሆናቸውን የጠቆሙት የማህበራዊ ሳይንስ ምሁሩ አንዋር ጫሚሶ፣ ይህን መሰል ተግባር ቀጣይነት መልኩ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጥረት ማድረግና ማገዝ እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል፡፡

የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያው አቶ ሶፎንያስ ፍሰሃ በበኩላቸው፣ ከተማዋ በተስፋ ብርሃን እና በተማሪዎች የምገባ መርሃ ግብር፣ በቤቶች ዕድሳት እና ለተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች እንደ ለነገዋ የሴቶች ተሃድሶና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል የመሳሰሉ የማገሚያ እና ወደ አዲስና አዋጭ የሕይወት ምዕራፍ መሸጋገሪያ ማዕከላት ወደ ተግባር በማስገባት የተጋላጭ ወገኖችን ተጠቃሚነት እያረጋገጠ እንደሆነም ገልፀዋል፡፡

በቅርቡም በልደታ ክፍለ ከተማ ከተገነባው ዘመናዊ የጂ+4 የመኖሪያ ህንፃ መመረቁ ይታወሳል፡፡ ይህንን አስመልክቶ የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በወቅቱ ባስተላለፉት መልዕክት በልደታ ክፍለ ከተማ የገነባነውን ዘመናዊ የመኖሪያ ህንፃ፣ ለማህበራዊ ችግር ለተጋለጡ ወገኖች፣ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ፣ ለአካል ጉዳተኞች እና የሀገር ባለውለታ ለሆኑ ነዋሪዎቻችን መተላለፉን መግለፃቸው ይታወሳል፡፡

በተጨማሪም በተለያዩ የልማት ስራዎች ለተነሱ፤ በቀበሌ ቤት ውስጥ በደባልነት፣ በጥገኝነትና በላስቲክ ቤት ውስጥ ይኖሩ ለነበሩ እንዲሁም የመፀዳጃ ቤት ፍሳሽ በላያቸው እያለፈ እጅግ አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ለነበሩ ወገኖቻችን ጭምር ቤት አስረክበናል ያሉት ከንቲባ አዳነች፣ አዲስ አበባ በሰው ተኮር ስራዎቿ ተምሳሌት እንደሆነችም ተናግሯል፡፡

አክለውም ሰው ተኮር ስራዎችን ጠቅላይ ሚኒስት ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አስጀምረው መመሪያ ከሰጡበት ጊዜ ጀምሮ ላለፉት 7 ዓመታት በሰው ተኮር እሳቤያችን እና በበጎነት አገልግሎት ተሳትፎ ከ45 ሺህ በላይ ቤቶችን ለአቅመ ደካሞች መገንባት ችለናልም፡፡ ከተማችን ለሁላችንም ትበቃለች፤ መተሳሰብና ፍቅር ካለ ደግሞ ይበልጥ መስራት ይቻላል። በቀጣይም ለብዙዎች ለመድረስ በትጋት እንሰራለን ማለታቸውም አይዘነጋም፡፡

ሀገራዊ ለውጡ የተበሰረበትን ስምንተኛ ዓመት አስመልክቶ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ባሳለፍነው ሐሙስ (መጋቢት 24 ቀን 2018 ዓ.ም) ባደረጉት ሰላማዊ ሰልፍ ላይ የከተማ አስተዳደሩ ማህበራዊ ፍትሕን ለማንገስ እና የመዲናዋ ነዋሪዎችን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እያደረገ ያለውን ጥረት የሚያደንቁና ለልማቱ ቀጣይነት እገዛቸውን የሚያንፀባርቁ መልዕክቶችንም አስላልፈዋል፡፡

## የአዲስ ... ከገጽ 1 የዞረ

አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ፣ የአፍሪካ መዲናና በዓለም አቀፍ ደረጃ ሶስተኛዋ የዲፕሎማሲ ማዕከል ብትሆንም ከጥቂት ዓመታት በፊት የነበራት መሰረተ ልማት፣ የምታቀርበው አገልግሎት፣ የከተሜነት ደረጃዋ ስሟንና ሚናዋን የሚመጥን አልነበረም፡፡ በብዙ የከተሜነት መለኪያዎች ወደኋላ ቀርታ እንደነበር ማንም የማይክደው ሀቅ ነው። ይህንን ሁኔታ ለመቀየር፣ ለነዋሪዎች እና ጎብኚዎች ምቹ የሆነች ከተማ ለማድረግ ሀገራዊ ለውጡ ከመጣ ጀምሮ የተለያዩ ተነሳሽነቶችን በመንደፍ ሲሰራ ቆይቷል፡፡

ቀደም ሲል ተሽከርካሪን ማዕከል አድርገው የተሰሩ ጠባብ መንገዶች፣ ኋላቀር የፍሳሽና የቆሻሻ አወጋገድ፣ ያልዘመኑ የመንገድ መብራቶች፣ የመጥፎ ሽታና በሽታ ምንጭ የነበሩት ወንዞች የከተማዋ መገለጫ ነበሩ፡፡ በኮሪደር ልማት የተሽከርካሪ፣ እግረኛና ሳይክል መንገዶች ምቹ ሆነው ተሰርተዋል፡፡ የመኪና ማቆሚያዎች፣ የመንገድ ዳርቻ ማረፊያዎች፣ የህዝብ መናፈሻዎች፣ ደረጃቸውን የጠበቁ የመንገድ መብራቶች፣ ሰው ሰራሽ ፏፏቴዎችና ሌሎች ልማቶችን በማካተት ተሰርተዋል። እንደ ፒያሳ፣ አራት ኪሎ፣ ሽሮ ሜዳ፣ መገናኛ፣ ሲኤምሲ፣ ጎሮ፣ ሜክሲኮ፣ ሳሪስን ጨምሮ በርካታ አካባቢዎች ውበትን ተላብሰዋል፡፡

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) “ከተሜ፣ ከተሜነት፣ ክትመትና የኮሪደር ልማት” በሚል ርዕስ በቅርቡ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክን ጨምሮ በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን በተላለፈው ቃለ ምልልሳቸው፣ “አዲስ አበባ በስም ብቻ ነበረች፡፡ ዛሬ ግን ስም ብቻ አይደለም። አብባለች፤ ነጽታለች፡፡ ማበቧ ስሟ ብቻ ሳይሆን መገለጫዋ ሆኗል፡፡ ይህንን ያመጣው የኮሪደር ልማት ነው” ብለዋል፡፡

አዲስ አበባ ትላልቅ ፕሮጀክቶችን፣ የህዝብ አገልግሎት መስጫ ህንጻዎችን በመገንባትም ሆነ የኮሪደርና የወንዝ ዳርቻ ልማቶችን በፍጥነት፣ በጥራትና በአጭር ጊዜ እንድታከናውን ያደረጋት ከአዳዲስ የስራ ባህል ጋር መተዋወቋ ነው፡፡ በቀን ብቻ ሳይሆን በሌሊት፣ በመደበኛ ብቻ ሳይሆን 24 ሰዓት፣ በሳምንት ሰባት ቀን የሰው ሀይልና ማሽነሪዎችን በማንቀሳቀስ መስራትን ባህል አድርጋለች፡፡

ከዚህም ጋር አብሮ ያልተቋረረጠ የአመራር ክትትል ሥራዎችን በፍጥነት ማጠናቀቅ እንዲቻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ ከተማዋ ባለፉት ዓመታት ከፍተኛ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያላቸው በርካታ ፕሮጀክቶችን በመጀመር በ60፣ በ90፣ በ120 ቀናትን ጨምሮ በአጭር ጊዜ በፍጥነት እያጠናቀቀች ትገኛለች፡፡ የመንግስት አገልግሎት መስጫ ቢሮዎች፣ የጤና ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶች፣ ፖሊስ ጣቢያዎች፣ የስፖርት ሜዳዎች፣ የህጻናት መጫወቻና ሌሎች ፕሮጀክቶችም ተገንብተው ለአገልግሎት ክፍት ሆነዋል፤ እየሆኑም ይገኛሉ፡፡

ወረታው በዛብህ (ዶ/ር) የአዕምሮ ኢንተርፕርነርሺፕ ማስፋፊያ አገልግሎቶች አክሲዮን ማህበር ሥራ







ፎቶ- ከፋይል

ጠንካራ የስራ ባህልና የአመራሩ ያልተቋረጠ የስራ ክትትል አዲስ አበባ ለኢትዮጵያ ከተሞች ተምሳሌት እንድትሆን አድርጓታል

**በአዲስ አበባ ፕሮጀክቶችን ቀንና ሌሊት ሰርቶ በማጠናቀቅ እና የንግድ እንቅስቃሴዎችን በምሽት ጭምር የሚካሄዱበት ምቹ ሁኔታ በመፍጠር እየተከናወነ ያለው ሥራ ከፍተኛ ለውጥ እያመጣና ለሌሎች ከተሞች ተምሳሌት እየሆነ ነው**

አስኪያጅና የሥራ ፈጠራ አሰልጣኝ ናቸው፡፡ ጃፓን ብዙ የተፈጥሮ ሀብትና ለም የሚታረስ መሬት ሳይኖራት፤ ብዙ የምትሸጠው ነገር ፈጥራ፣ በዓለም ላይ ሶስተኛውን ግዙፍ ኢኮኖሚ መገንባት ችላለች፡፡ ለዚህም ያላት ጠንካራ የስራ ባህል ትልቁን ሚና ተጫውቷል፡፡ እንደ ደቡብ ኮሪያ፣ ሲንጋፖር፣ ማሌዥያ ያሉ የሩቅ ምስራቅ ሀገራት ጠንካራ የሥራ ባህል ካላቸው ሀገራት ተርታ እንደሚመደቡ ያነሳሉ፡፡

በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አነሳሽነት በአዲስ አበባ የተሰሩት የአንድነት እና እንጦጦ ፓርኮች፣ የወዳጅነት አደባባይ፣ የሳይንስ ሙዚየም፣ የዓድዋ ድል መታሰቢያ፣ በኮሪደር ልማት መሠረተ ልማቶችን በማዘመን የተሰሩ ሥራዎች ውብና ለማየት የሚያጓጉ ናቸው። የአዲስ አበባን ገፅታም በእጅጉ የቀየሩ መሆናቸውን ወረታው (ዶ/ር) ያነሳሉ፡፡ “ፕሮጀክቶቹ በአጭር ጊዜና በጥራት የተጠናቀቁ ከመሆናቸው ባሻገር የአዲስ አበባን ገፅታ በእጅጉ የቀየሩ ናቸው፡፡ ውበት ብቻ ሳይሆን ገቢን የሚፈጥሩ፣ የከተማዋን የወደፊት ህይወትና እንቅስቃሴ ታሳቢ ያደረጉ ናቸው፡፡ እነዚህ ዓይነት ሥራዎች በብዙ ዓመታት አይተናቸው የማናውቃቸው ናቸው፡፡” ሲሉም የተገኘው ውጤት የሚደነቅ እንደሆነ ያነሳሉ፡፡ በአዲስ አበባ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ለተገኘው ውጤት አዲስ የሥራ የባህል ለውጥ መኖሩና የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) እና የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ጨምሮ የአመራሩ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

በመጣው አዲስ የሥራ ባህል ለውጥ ለማሳካት ከተያዙ ሥራዎች መካከል በከተማዋ የሚታየውን የመኖሪያ ቤት ፍላጎት ለማርካት ከሶስት ወራት በፊት የተጀመሩ የቤቶች ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች ይጠቀሳሉ፡፡ በዘንድሮው ዓመት ብቻም በአዲስ አበባ 100 ሺህ ቤቶችን ለመገንባት ታቅዶ በ18 ሳይቶች የግንባታ ሥራዎች እየተከናወነ ይገኛል፡፡ የአዲስ አበባ ቤቶችና አስተዳደር ልማት ቢሮ አማካሪ ኢንጂነር አውራሪስ ከበደ ከሶስት ወራት በፊት ለአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ በሰጡት ማብራሪያ፣ የተያዘውን ሰፊ የሆነ እቅድ ለማሳካት እየተለመደ የመጣው በቀን ሃያ አራት ሰዓት፤ በሳምንት ሰባት ቀናት የመስራት የሥራ ባህል ወሳኝነት አለው፡፡ ከዚህ ቀደም ባለ 14 ወለል ያላቸው 24 ህንጻዎች ከዘጠኝ ወራት ባነሰ ጊዜ ማጠናቀቅ ከተቻለበት ተሞክሮ በመውሰድና ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም በፍጥነት ለማጠናቀቅ እየተሰራ ነው፡፡

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

# አዳዲሶቹ የኢኮኖሚ አቅሞች

- **ፕላዛዎችን ማስፋፋት አዲስ አበባን የዓለም ከተሞች ከደረሱበት ደረጃ በማድረስ ህዝብን ተጠቃሚ የማድረጉ አካል እንደሆኑ ተጠቁሟል**

**በስንታየሁ ምትኩ**

አዲስ አበባ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ያከናወነቻቸው ተግባራት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየፈካች፣ ስሟንና ያላትን ድርብርብ ሚና የሚመጥን ከተማ እየሆነች እንድትመጣ አድርጓታል፡፡ የከተማዋን ገፅታና መልክ በመቀየር ረገድ የኮሪደር ልማቱ ጉልህ ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡ ልማቱ ይዟቸው ከመጣ በረከቶች መካከል ህብረተሰቡ በእግሩ እየተንቀሳቀሰ እየተዝናና የሚገበያይባቸው የተለያዩ አገልግሎቶችን አካትተው የያዙ ፕላዛዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ አራት ኪሎ፣ ሳር ቤት፣ ቴዎድሮስ አደባባይ ፕላዛዎች ከሚገኙባቸው የከተማዋ አካባቢዎች መካከል ናቸው፡፡









ፎቶ- ከፋይል

ፕላዛዎች የንግድና የስራ ዕድል አማራጭ እየሆኑ መጥተዋል

ከሁለት ሳምንት በፊትም ከፒያሳ በቸርቸል መንገድ ወደ ቴዎድሮስ አደባባይ ወረድ ብሎ በስተቀኝ በኩል የሚገኘው የድል ፕላዛና የቁርጡሚ የወንዝ ዳርቻ ልማት ግንባታ ተጠናቅቆ ለአገልግሎት ክፍት ሆኗል፡፡ በምርቃ ስነ ስርዓቱ ላይ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ እንደተናገሩት፣ የቆሻሻ መጣያ፣ ሰዎች ላስቲክ ወጥረው የሚኖሩበት፣ ገደላማና ለኑሮ የማይመች፣ ጥቅም ላይ ያልዋለ አካባቢ ነበር፡፡ ይህንን ቦታ በመልሶ ማልማት የተንጣለሉ ሱቆች፣ ከመሬት በታች ባለ ሶስት ወለል በአንድ ጊዜ አምስት መቶ ተሽከርካሪዎችን ማቆም የሚያስችሉ ዘመናዊና በቴክኖሎጂ የተደራጀ የመኪና ማቆሚያ፣ አረንጓዴ ስፍራ፣ የስፖርት ሜዳ፣ የህጻናት መጫወቻ፣ አምፊ ቴአትር፣ የስጦታ እቃ መሸጫዎች፣ ሁለት ትላልቅ የቡና መሸጫ ካፍቴሪያዎች እንዲገነቡበት ተደርጓል። የመኪና ማቆሚያው የንግድ ማእከል ከሆኑት ተክለ ሃይማኖትና መርካቶ በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኝ ስትራቴጂክ ስፍራ በመሆኑ ሰዎች ወደ እነዚህ ቦታዎች በመሄድ ንግዳቸውን በቀላሉ እንዲያከናውኑ ዕድል ይፈጥርላቸዋል፡፡

አካባቢው በርካታ ቅርሶች የሚገኙበት እንደመሆኑ ለዚህም የሚመጥን አገልግሎት ማቅረብ የሚችሉ እንደዮድ አቢሲኒያ ባርና ሬስቶራንት እንዲሁም የተለያዩ የስጦታ እቃዎችን ማቅረብ የሚችሉ ተቋማት እየሰሩበት ይገኛሉ፡፡ በፕላዛው አገልግሎት መስጠት ከጀመሩት መካከል ዮዲ አቢሲኒያ የባህል ምግብ አዳራሽ አንዱ ነው፡፡ የዮድ አቢሲኒያ መስራችና ባለቤት አቶ ትዛዙ ኮሬ ፕላዛው በተመረቀበት ወቅት እንደተናገሩት፣ የከተማ አስተዳደሩ ከገነባቸው ውብና ማራኪ ህንጻዎች መካከል አንዱን ዮድ አቢሲኒያ የባህል ምግብ አዳራሽ በኪራይ አገልግሎት እንዲሰጥበት ባስተላለፈው ውሳኔ መሰረት በአጭር ጊዜም አስፈላጊ እቃዎችን በማሟላት በተደራጀ መንገድ ወደ ስራ መግባታቸውንና ለዚህም ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡ ድርጅቱ የኢትዮጵያን ቱባ ባህልና የቱሪዝም ሀብቶች ለዓለም በማስተዋወቅ፣ መልካም ገፅታ በመገንባት፣ ሰፊ የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ ለመንግስት ከፍተኛ ገቢ በማስገኘት ባበረከተው አስተዋፅኦ "የኢትዮጵያ የባህልና ቱሪዝም አምባሳደር" የሚል እውቅና ከመንግስት ተሰጥቶታል። ድርጅቱ ስራውን በሰፊው ማከናወን እንዲችል በቀድሞ ካዛንቺስ ቶታል አካባቢ የግንባታ ቦታ እንደተሰጠው ያነሱት አቶ ትዛዙ፣ መንግስት ለአልሚዎች የሚጨነቅ፣ ሱቅ ሲፈርስ ሱቅ የሚተካ፣ የንግድ ድርጅት ገንብቶ የሚሰጥ መሆኑን ከእነሱ በላይ ማስረጃ እንደሌለ አንስተዋል፡፡ ይህም ለስራ ፈጣሪዎች ተነሳሽነት የሚፈጥር እንደሆነና ለዚህም ለአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤና ለከተማው አመራሮች ምስጋና አቅርበዋል፡፡

የድል ፕላዛን በማሳያነት አነሳን እንጂ ከአንድ ዓመት በፊት ተገንብቶ ወደ ስራ የገባው የአራት ኪሎ ፕላዛ ከተማዋ ልዩ ገፅታ እና ዘመናዊነትን እንድትላበስ ከማስቻሉም ባሻገር የተነቃቃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እንዲኖር ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡ በፕላዛው የምድር ውስጥ መሸጋገሪያ ዋሻ እግረኞች ደህንነታቸው ተጠብቆ ከአንዱ የመንገድ አካል ወደ ሌላው ሲያቋርጡ፤ በተለያዩ የንግድ ሱቆችም ሲገበያዩና ሲዝናኑ ይታያል፤ በሱቆቹ ከሚሸጡ ምርቶችና አገልግሎቶች መካከል የሞባይልና ስልክ መለዋወጫዎች፣ የጽሕፈት መሳሪያዎች፣ መጽሀፍ መሸጫዎች፣ መነፅር ቤቶች፣ የኤሌክትሮኒክስ ውጤቶች፣ አልባሳትና ካፌዎች ይገኙበታል፡፡ ሱቆቹ ከተለመደው የስራ ሰዓት በዘለለ ከጠዋቱ 12፡30 እስከ ምሽቱ 3፡00 ድረስ ክፍት ሆነው አገልግሎት ይሰጥባቸዋል፡፡

የፈረንሳይ አካባቢ ነዋሪው ወጣት ሻምበል ግርማ የባንክ ባለሙያ ሲሆን የስራ ቦታውም ፕላዛው ባለበት አካባቢ እንደመሆኑ አራት ኪሎን በደንብ እንደሚያውቀው ይናገራል፡፡ አራት ኪሎ ከዚህ በፊት የነበረው ገፅታ ደስ የማይል ነበር፡፡ በመንገዶች ይካሄዱ የነበሩ የጎዳና ላይ ንግዶች፣ በመንገድ ዳር የቆሙ የማስታወቂያ ሰሌዳዎች ለእይታ የማይስቡና የሰዎችን እንቅስቃሴ የሚገድቡ ነበሩ፡፡ በአሁኑ ወቅት እነዚህ ችግሮች ተቀርፈዋል፤ የአካባቢው ገፅታ ተቀይሯል፤ ዘመናዊነትን ተላብሷል። በፕላዛው ምድር ውስጥ ባሉት ሱቆች የተለያዩ አገልግሎቶች ይገኛሉ፡፡ እንደዚህ ዓይነት ንግድና መዝናኛን ያማከሉ ዘመናዊ ማዕከላት በየአካባቢው መስፋፋት እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡

በአራት ኪሎ የመኪና ማቆሚያና የገበያ ማዕከል ውስጥ ተሽከርካሪያቸውን አቁመው ሲወጡ ያገኘናቸው አቶ ቢኒያም ተስፋሁን፣ "ፕላዛው የአካባቢውን ውበትና ገፅታ ከመቀየር ባሻገር ዘርፈ ብዙ አገልግሎቶች በአንድ አካባቢ የሚገኙበት በመሆኑ ለነዋሪው ከፍተኛ ጥቅም ያስገኛል፡፡ ለምሳሌ፡- ከዚህ ቀደም በቂና ደህንነቱ የተጠበቀ የመኪና ማቆሚያ ባለመኖሩ መንገድና ደህንነቱ ያልተጠበቀ ቦታ ተሽከርካሪ አቁሜ ስፖኪዮና የተለያዩ የመኪና አካላት መሰረቅ አጋጥሞኝ ነበር፡፡ አሁን ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ አገልግሎቱን እንድናገኝ አስችሎናል" ሲሉ ፋይዳውን አብራርተዋል፡፡

**በአዲስ አበባ ከዚህ ቀደም ሰዎች በመንገድ ዳር፣ በቆርቆሮ በታጠሩ ቤቶች ውስጥ... ይሰሩ ነበር። ፕላዛዎች መገንባታቸው በተደራጀ መልኩ በአንድ አካባቢ የተለያዩ ምርትና አገልግሎቶች የሚገኙበትን ሁኔታ ፈጥሯል**

ሌላው በጦር ሀይሎች አካባቢ ነዋሪ የሆኑት አቶ ማናዬ እሱባለው ለስራ ወደ አራት ኪሎ በመጡበት አጋጣሚ ፕላዛው ውስጥ ካሉት ሱቆች እንደ አትክልትና ስኳር ያሉ የፍጆታ ምርቶችን ሸምተው ሲወጡ ነበር ያገኘናቸው፡፡ "እንደዚህ ዓይነት ገበያዎች መበራከታቸው ይበል የሚያሰኝ ነው፡፡ በተመጣጣኝ ዋጋ የፈለግነውን ምርትና አገልግሎት መሸመት እንድንችል እድል ፈጥሮልናል፡፡ ሱቆቹ የሚገኙበት ቦታ ማዕከላዊ በመሆኑ፣ የፈለግነውን እንድንሸምትና በዚህም ጊዜና ጉልበት እንድንቆጥብ አስችሎናል፡፡ አካባቢው ፅዱ እና ሰፊ በመሆኑ እንደ ልብ ለመንቀሳቀስ ያስችላል፡፡ በተጨማሪም ንጹህና ጥራቱን የጠበቀ ምርትም እያገኘን ነው፡፡" ሲሉ እያስገኙት ስላለው ጥቅም ገልጸዋል፡፡

ፕላዛዎቹ ለሸማቹ ብቻ ሳይሆን ለበርካቶች በተለያየ የንግድ ዘርፍ የስራ ዕድል ፈጥረዋል፡፡ ወጣት ሜላት ንገሴ በአራት ኪሎ ፕላዛ የምድር ውስጥ መተላለፊያ ባላት ሱቅ ጫማና ቦርሳዎችን ትሸጣለች፡፡ ፕላዛው ከዚህ ቀደም ያልነበረ፣ አዲስ አበባን ልዩ ውበትና ዘመናዊነትን ያላበሰ እንደሆነ የምትገልፀው ወጣት ሜላት፣ ሰዎች በአካባቢው ሲሸጋገሩ እግረመንገዳቸውን በቀላሉ መገበያየት እንዲችሉ ጥሩ እድል መፍጠሩንም ትናገራለች፡፡

ፕላዛዎቹ እንደሷ ላሉ ወጣቶች የስራ ዕድል የሚፈጥሩ መሆናቸውን የምትናገረው ወጣት ሜላት፣ በአካባቢው አስተማማኝ የ24 ሰዓት ጥበቃ ስላለ ያለምንም የደህንነት ስጋት ንግዳቸውን እንዲያቀላጥፉ እድል ፈጥሮላቸዋል። ከጠዋት አንስቶ እስከ ምሽት 3፡00 ድረስ እንደሚሰሩና ከጊዜ ወደ ጊዜ ሰዎች

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ የሚቀርብ

# የምርጫ ምንነት፣ መርሆች እና ዓይነቶች

## ክፍል አራት

ናደው ወርቁ (ዐቃቤ ህግ)

ውድ አንባቢዎቻችን ባለፈው ዕትማችን በዋናው ርዕስ ስር በምርጫ ወቅት የተከለከሉ ተግባራት እና ቅጣታቸው፣ በኢፌዴሪ የወንጀል ህግ ምርጫን የተመለከቱ ድንጋጌዎች ስር ለምርጫ የሚደረግ ስብሰባንና የምርጫ ሂደትን ማወክና ማሰናከል፣ የምርጫ ድምጽ የመስጠትን ወይም የመመረጥን መብት መንካት እንዲሁም በምርጫ ሂደት መደለያ መስጠት እና ተያያዥ ጉዳዮችን አስነብበናችኋል። የመጨረሻውን ክፍል ደግሞ እንደሚከተለው አዘጋጅተንላችኋል፡፡ መልካም ንባብ።



**4. የማይገቡ አሰራሮች መፈጸም፡- በአንቀጽ 669 መሰረት የሚከተሉትን ያልተገቡ ነገሮች መፈጸም በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 በወንጀል ያስቀጣል።**

- በህግ ከተፈቀደው ውጭ ለምርጫ ዘመቻ ወጪ የሚሆን ገንዘብ ከማንኛውም ሰው፣ ቡድን ወይም ድርጅት መሰብሰብ፣ የምርጫ ውድድር የሒሳብ ደንቦችን አለማክበር፣ በምርጫ ውድድር ሒሳብ ውስጥ ወጪን አስቦ እና አሳንሶ ማመልከት ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ያስቀጣል፤
- ከእጩ ተመራጭ ፈቃድ ሳያገኝ የአንድን እጩ ተመራጭ የምርጫ ወጪ ለመሸፈን ገንዘብ ማሰባሰብ፣ መስጠት እንዲሁም በሌላ በማንኛውም መንገድ አስተዋጽኦ ማድረግ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ያስቀጣል፡፡

በኢትዮጵያ የምርጫና የፖለቲካ ፓርቲዎች አዋጅ 1162/2011 አንቀፅ 109(1) መሰረት ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፡- ከውጪ ሀገር ዜጎች ተቋማት ወይም ድርጅቶች፤ ከውጪ ሀገር መንግሥት ወይም ከውጪ ሀገር የፖለቲካ ድርጅት፣ ከበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት፣ ከኃይማኖት ድርጅት፣ ከፍርድ እስረኞች፣ በህገ-መንግስቱ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ሥልጣን ለመያዝ ከተደራጀ ቡድን ወይም ሰው፣ በሽብርተኛነት ከተሰየመ ድርጅት፣ ካልታወቀ ምንጭ የሚቀርብ ስጦታ ወይም እርዳታ፣ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመንግስት ከሆኑ የልማት ድርጅቶች፣ አንድን ነገር ወደፊት ለማስፈፀም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ወይም ከህግ ውጭ ጥቅም ለማግኘት ከሚያልም ማንኛውም አካል የሚሰጥ ስጦታ ወይም እርዳታ መቀበል አይችልም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 469(3) በተገለጸው መሰረት በማንኛውም መንገድ በማጭበርበር የመራጭን ድምጽ ማግኘት ወይም በመራጭ ድምጽ ያለአግባብ መገልገል ወይም ድምጹ መራጩ ለመረጠው ሰው እንዳያገለግል ማድረግ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ያስቀጣል፡፡

**5. በአመዘጋገብ ላይ የሚፈጸም ማጭበርበር**

በአንቀጽ 470 መሰረት የሚከተሉትን የማጭበርበር ተግባራት መፈጸም ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ያስቀጣል፡፡

- በምርጫ ዝርዝር ወይም በምርጫ መዝገብ ውስጥ በሐሰተኛ ስም ወይም ማዕረግ ወይም በሌለው ችሎታ እንዲመዘገብ ማድረግ ወይም ያለበትን በሕግ የታወቀ ችሎታ ማጣት ሳይገለጽ መመዝገብ፤
- በአንድ ጊዜ በሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ ዝርዝሮች ወይም መዛግብት ስሙን ማስመዝገብ ወይም ያለአግባብ ብዙ የድምጽ መስጫ ወይም የምርጫ ወረቀቶችን መቀበል ወይም እንዲሰጠው ማድረግ፤
- ያለአግባብ በሕይወት ያሉ፣ የሞቱ፣ የጠፉ ወይም በሕይወት ኖረው የማያውቁ ሰዎችን ማስመዝገብ ወይም በእነርሱ ስም የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን መቀበል፡፡

ነገር ግን እነዚህ ድርጊቶች የተፈጸሙት በእጩ ተመራጩ በሆነ ጊዜ ቅጣቱ ከሁለት ዓመት ያልበለጠ ጽኑ እስራት ወይም ከአስር ሺህ ብር ያልበለጠ መቀጮ ይሆናል፡፡

**6. በድምጽ አሰጣጥ ጊዜ የሚፈጸሙ ማጭበርበሮች (አንቀጽ 471)፣**

ማንም ሰው ማንኛውም ዓይነት የታወቀ ምርጫ በሚደረግበት ወቅት፣ ከምርጫው በፊት ወይም ከምርጫው በኋላ በሚፈጸም በማንኛውም ድርጊት በተለይም በሚከተሉት ምክንያቶች የምርጫውን ትክክለኛ ውጤት ያሳሳተ እንደሆነ በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል፡፡

- የምርጫ መዝገብን፣ የተጠናቀቀ የምርጫ ዝርዝርን፣ ወይም ድምጽ የተሰጠበትን የድምጽ መስጫ ወረቀትን አስመስሎ በመስራት፣ ሐሰተኛ በማድረግ፣ በመለወጥ፣ በሚያሳስት ዘዴ በላዩ ላይ በማተም ወይም በማስቀረት፣ በማጥፋት ወይም በመውሰድ፤
- በአንድ የምርጫ ጊዜ ከአንድ ጊዜ በላይ ድምጽ በመስጠት፤
- የድምጽ መስጫ ወረቀትን በድምጽ መስጫ ሳጥን ውስጥ በመጨመር ወይም ከምርጫ ሳጥን አውጥቶ በመውሰድ፣ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ ያለአግባብ ሕጋዊ መኖሪያ ቦታው ምርጫ በሚደረግበት አካባቢ ውጭ የሆነውን፣ ችሎታ የሌለውን፣ ችሎታ ያጣውን ሰው ድምጽ እንዲሰጥ ወይም በሞተ ሰው ስም ድምጽ እንዲሰጥ በማድረግ ወይም ለድምጽ መስጫ እንዳያገለግል የተደረገ፣ ወደ ሐሰተኛነት የተለወጠ፣ ወይም በሀሰት የተሰራ የድምጽ መስጫ ወረቀትን እያወቀ በምርጫ ሳጥን ውስጥ በማስገባት ወይም እንዲገባ በመፍቀድ፤
- የድምጽ መስጫ ወረቀትን በትክክል ባለመቁጠር ወይም ታስቦ የተሠጠ ድምጽ፣ ድምጽ የተሰጠበትን ወረቀት፣ ስምን ወይም ፊርማን በመተው፣ ወይም ከተጻፈው ፊርማ ወይም ስም ሌላ በማንበብ ወይም በምርጫው ሥነ ስርዓት ቃለ ጉባኤ ወይም በአፈሳላዊ የምርጫ ውጤት ላይ ከእውነተኛው ነገር ውጭ በመመዝገብ፤
- የምርጫ ውጤትን ወይም ሰነድን በማስቀረት፣ በመደበቅ፣ በመለወጥ፣ በመለዋወጥ ወይም በማጥፋት ወይም እነዚህን ለመቀበል ስልጣን ለሌላቸው ሰዎች ያለአግባብ በመስጠት፡፡

**7. የድምጽ አሰጣጥ ምስጢር አጠባበቅን መጣስ (አንቀጽ 473)**

አንድ መራጭ ያለውን መብቱን በምን ዓይነት ሁኔታ እንደተገለገለበት ወይም ድምጹን እንደሰጠ ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ለማወቅ የቻለ ወይም በአጋጣሚ ካወቀ በኋላ በቃልም ሆነ በጋዜጣ ወይም በሌላ ዓይነት ዘዴ አስቦ ለህዝብ የገለጸ ወይም ወሬውን የነዛ ሰው በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል፡፡

**8. የድምጽ መስጫ ወረቀቶችንና የምርጫ ሳጥኖችን መውሰድና ማጥፋት (አንቀጽ 474)**

ድምጽ ተሰጥቶባቸው ያልተቆጠሩ የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን የያዘ የምርጫ ሳጥንን ወይም በሳጥኑ ውስጥ የሚገኙትን የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን በሙሉ ወይም በከፊል ከቦታው ማንሳት፣ እንዲሰወሩ ማድረግ ወይም ማጥፋት በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ያስቀጣል፡፡ ነገር ግን ድርጊቱ የተፈጸመው ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች ወይም በኃይል ድርጊት ከሆነ ለአለቆቹ ወይም ለመሪዎቹ ስለቅጣት ማክበጃ የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ ቅጣቱ ከአስር ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እስራት ይሆናል፡፡

ምርጫን በሚመለከት ለሚፈጸሙ ወንጀሎች የእስር ቅጣት በተወሰነ ጊዜ በተደራቢነት ለተወሰነ ጊዜ ከህዝባዊ መብት የመታገድ ቅጣት ይወሰናል፡፡

ከተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየወሩ የሚቀርብ

# ለሀገር በቀል እውቀት ትኩረት የሠጠው ኮሌጅ

- 1 ሺህ 37 ኢንተርፕራይዞች በተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ድጋፍ እየተደረገላቸው ነው

**በሄለን ጥላሁን**

ወጣት ሰዓዳ ሰዒድ ትባላለች፡፡ በልብስ ስፌት የሙያ ዘርፍ ተሰማርታ እየሰራች ትገኛለች፡፡ ሥራዋን የምታከናውነው በተለምዶ አዲሱ ገበያ፣ ሸማ ማዕከል ህንፃ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ መንግስት በሰጣት የመስሪያ ሼድ ውስጥ ነው። የተለያዩ የህፃናት አልባሳትንና ሴቶች ለማጌጫነት የሚጠቀሟቸውን የግንባር ፀጉር ማስያዢያዎች ታመርታለች፡፡

ወደ ስራው ዓለም ከመግባቷ አስቀድማ የሦስት ወር ስልጠና በግል ትምህርት ቤት የተማረች ቢሆንም በሙያዋ ሠርታ ራሷን ማስተዳደር የምትችልበት ገቢ ማግኘት ሳትችል ቆይታለች፡፡ ይሁን እንጂ የተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ለእርሷ እና ለመሰሎቿ ያዘጋጀው የስልጠና ድጋፍ ዛሬ ለደረሰችበት ደረጃ ትልቅ እገዛ አድርጎላታል፡፡ በተለይም እርሷ በተሰማራችበት የልብስ ስፌት ስራ ከፖሊ ቴክኒክ ኮሌጁ አንድ አሰልጣኝ ተመድቦላት በስራዋ ውጤታማ እንድትሆን አግዟታል፡፡

እንደ ወጣት ሰዓዳ ገለፃ፤ የተለያዩ የልጆች አልባሳትን የመስራት ፍላጎት ቀድሞም ነበራት፡፡ ከኮሌጁ ያገኘችው የሙያ ስልጠና ያሰበችውን እንድትከውን አድርጓታል፡፡ ሙያዋን በሂደት ማሻሻል ከመቻሏም ባሻገር፣ በምትሰራው ስራ ኑሮዋን በጥሩ ደረጃ ለመደገፍ አስችሏታል፡፡ ግለሰቦች ያላቸውን የሙያ ክህሎት እና እውቀት ተጠቅመው የተለያዩ ምርቶችን ለገበያ በማቅረቡ ሂደት ላይ የደጋፊ አካላት ሚና እጅግ የላቀ ነው፡፡

"ሀገር በቀል እውቀትን ተጠቅመን በቂ የሀገር ውስጥ ምርቶችን ለማምረት በሚደረገው ጥረት ከፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች የምናገኛቸው ድጋፎች ትልቅ ሚና አላቸው" የምትለው ወጣት ሰዓዳ፤ "ከተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በልብስ ስፌት ሙያ መሰረታዊ የሚባሉ እንደ ዲዛይን ማውጣት፣ ስኬች፣ ፓተርን አወጣጥ እንዲሁም የልብስ አቆራረጥ ላይ ትምህርት አግኝቻለሁ። ሙያዬን ለማሳደግ የተሰጠኝ ስልጠና እጅግ አግዞኛል፡፡ የካይዘን ትምህርት አግኝቻለሁ፡፡ በተለይም በውስን ስፍራ ላይ ያለኝን የቦታ አጠቃቀም በአግባቡ እንድቃኝ አድርጎኛል" በማለት ሥራዋን አብራርታለች፡፡

አክላ እንዳስረዳችው፤ እስከሁን የተሰጣት ሙያዊ ስልጠና በሥራዋ ተወዳዳሪና ውጤታማ እንድትሆን አቅም ፈጥሮላታል፡፡ በቀጣይም የራሷን ሱቅ በመክፈት የተለያዩ የልጆች አልባሳትን በመስራት የምርታማነት መጠንና ተደራሽነት ለማሳደግ ዕቅድ ይዛለች፤ አስፈላጊ ድጋፎችንም ከተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጁ እያገኘች ነው፡፡ ይህ በቀጣይ ለምትሰራቸው ስራዎች ትልቅ አቅም ይፈጥርላታል፡፡

ወጣት አባይ ተስፋ ይባላል፡፡ በቆዳ ምርት ተሰማርቶ ይሰራል፡፡ በማህበር ተደራጅቶ እንደ ቀበቶ፣ ቦርሳ፣ ጫማ እና ዋሌት (የኪስ ቦርሳ) ማምረት ከጀመረ





ፎቶ- ከፋይል

ወጣት አባይነህ ተስፋ እና ወጣት ሰዓዳ ሰይድ በተሰማሩበት የስራ መስክ ምርቶቻቸውን ሲያመርቱ

ሦስት አመታትን አስቆጥሯል፡፡ ከዚህ አስቀድሞ በግሉ የተለያዩ የእጅ ስራዎችን የመስራት ልምድ ነበረው፡፡ "በዋናነት ጥራት ያለው ምርት አምርተን ለገበያ እንድናቀርብ ኮሎጁ የቅርብ ሙያዊ ድጋፍ አድርጎልናል፤ ይህም በስራችን ላይ ለውጥ እንድናመጣ አስችሎናል" በማለት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጁ ለአካባቢው ወጣቶች እና ኢንተርፕራይዞች ዕድገት እየተወጣ ስላለው ተቋማዊ ኃላፊነት ተናግሯል፡፡

"የኮሌጁን ድጋፍ ከማግኘታችን አስቀድሞ እንሠራበት የነበረው የስራ ቦታ ምቹ አልነበረም፡፡ የመስሪያ ማሽኖቻችንን በአግባቡ ለመጠቀም የስራ ከባቢው የተደራጀ እና ምቹ መሆን ይገባዋል፡፡ ጥራት ያለው ስራ ለመስራት አካባቢያችን ፅዱ፣ ለእይታ ማራኪ ብሎም ያልተወሳሰበ መሆን አለበት፡፡ ከዚህ በፊት ስራዎችን በዘፈቀደ እንሰራ ነበር፡፡ አሁን ላይ ከኮሌጁ ባገኘነው የካይዘን ስልጠና መሰረት በተቀላጠፈ እና ምቹ በሆነ አግባብ ለመስራት ችለናል" የሚለው ወጣት አባይ፤ በሂደት ውጤታማ መሆኑንና አሁን ላይ ማህበሩ ለሶስት ሰዎች ቋሚ የስራ እድል መፍጠር መቻሉን አስረድቷል፡፡

ወጣት አባይ በማብራሪያው፤ ማህበሩ በቀጣይም የቆዳ ምርት ስራዎችን በስፋት በመስራት ከሀገር ውስጥ ገበያ ባሻገር ወደ ውጭ ለመላክ ትልቅ ርዕይ አለው። የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ የቆዳ ምርቶችን በማምረት ሂደት ውስጥ የኮሌጁ ሚና ትልቅ ነው፡፡ በተለያዩ ጊዜያት ሀገር በቀል እውቀቶች በዘመናዊ ሥልጠና እንዲታገዙ ሲያደርግ የነበረውን ድጋፍ አጠናክሮ እንዲቀጥል ጠይቋል፡፡

በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ሀገር በቀል እውቀቶችን አካትቶ መተግበር እንደ ሀገር ያለው ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ብሎም ማህበራዊ ፋይዳው እጅግ የላቀ ነው። የተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅም

> **በተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በድጋፍ ማዕቀፍ ተጠቃሚ የሆኑ ማህበራት የምርትና ምርታማነት አቅማቸውን በማጠናከራቸው ኢኮኖሚያዊ እድገት ማሳየት ችለዋል**

በአካባቢው በተለያየ ሀገር በቀል ሙያ ላይ ተሠማርተው የሚሰሩ ሙያተኞችን በተለያየ አግባብ ድጋፍ እንደሚያደርግ በኮሌጁ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አስተባባሪዋ ወይዘሪት ራኬብ ጌታቸው ገልፃለች፡፡

እንደ አስተባባሪዋ ገለጻ፤ በተለይ በጥቃቅንና አነስተኛ ዘርፎች የተደራጁ ማህበራት ሀገር በቀል እውቀቶችን በመደገፍ ረገድ ኮሌጁ አስተዋጽኦው የላቀ ነው፡፡ በወረዳ አስተዳደር አማካኝነት ለተመረጡና በጥቃቅንና አነስተኛ ተደራጅተው ለሚሰሩ ወጣቶች ፍላጎታቸውን መሰረት ያደረገ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡

እንደ ራኬብ ገለፃ፤ በአራቱም የድጋፍ ማዕቀፎች (በቴክኖሎጂ፣ ቴክኒካል ክህሎት፣ በኢንተርፕረነር ሺፕ እንዲሁም በካይዘን ትግበራ) ዙሪያ ድጋፍ ይደረጋል። በእነዚህ የድጋፍ ማዕቀፎች ተጠቃሚ የሚሆን አካል የምርትና የምርታማነት አቅሙን ያደረጃል፡፡ ከጥራት አንፃርም ተወዳዳሪነትን ለማትረፍ የሚያስችል ስራ እንዲሰራ ያግዛል፡፡ ድጋፍ የማድረጉ ጠቀሜታ የጋራ ነው፡፡ ይህ ለባህል ጥበቃ እጅግ ጠቃሚ ሲሆን ትውልድ ተሻጋሪ የሆኑ ጥበባት እንዳይጠፉ ያደርጋል። ሰልጣኞች አልያም ድጋፍ የሚደረግላቸው አካላት የፈለጉትን የስልጠና ማዕቀፍ በመምረጥ ስለሚማሩ በስራቸው ላይ የሚያሳዩት ለውጥ ቀላል የሚባል አይደልም፡፡ ቁጥራቸው 1ሺህ 37 የሚሆኑ ኢንተርፕራይዞችም በተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ድጋፍ እየተደረገላቸው ነው።

በማኑፋክቸሪንግ፣ በንግድ፣ በአገልግሎት፣ በከተማ ግብርና እንዲሁም በኮንስትራክሽን ዘርፎች ለተለዩት ስልጠና ይሰጣቸዋል፡፡ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጁ እንደ አስፈላጊነቱ ቦታቸው ድረስ በመሄድ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ በተለይም ሀገር በቀል እውቀትን መሰረት አድርገው በልብስ ስፌት፣ በሸክላ እንዲሁም በሽመና ስራ ለተሰማሩት በድጋፍ ማዕቀፉ መሰረት ስልጠናዎች እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ኮሌጁም ድጋፍ ለተደረገላቸው አካላት ሲኦሲ እንዲፈተኑ ጭምር ያደርጋል። ከድጋፍ በፊትና በኋላ ያፈሩት ሃብት እንዲሁም የመጣውን ልዩነት በማጤን የድጋፍ አግባቡን እንደሚቀጥልም አስታውቃለች፡፡

እንደ ራኬብ ገለፃ፤ ሀገር በቀል እውቀትን ከቴክኖሎጂ ጋር አስተሳስሮ መስራት የምርት አቅማቸውን ለማሳደግ በእጅጉ ይጠቅማቸዋል፡፡ በራስ ልምድና የሙያ አቅም ይሰራ የነበረውን በቴክኖሎጂ መደገፍ ምርታቸው እንዲጨምር ያግዛል፡፡ ኮሌጁ የመስሪያ ማሽን ችግር ላለባቸው ማህበራት በኮሌጁ ውስጥ መጥተው ጭምር መገልገል የሚችሉበትን አግባብ ፈጥሯል። በተለይም በቆዳ እንዲሁም በሽመና ስራ የተሰማሩ በሀገር ልብስ ሙያተኞች የሚሰሩት ስራ እጅግ አድካሚና ጊዜን የሚፈጅ በመሆኑ በቀላሉ በግቢ ውስጥ መጥተው ማምረት የሚችሉበት አግባብ ተፈጥሯል፡፡

በዚህም በቀላሉ ሊገኙ የማይችሉ እውቀቶችን ድጋፍ ለሚያሻቸው ይሰጣል። በቴክኖሎጂ የተደገፈ የዘመነ አሰራርን በቀላሉ እንዲለማመዱ ያግዛቸዋል። በዚህም ምርትና ምርታማነታቸው እንዲጨምር ያግዛቸዋል፣ ተወዳዳሪ ምርት እንዲያቀርቡ ያደርጋል፣ ጊዜና ጉልበታቸው እንዲቆጠብ ያደርጋል፣ እውቀታቸውንም እለት ተዕለት እንዲያሻሽሉ እንዲሁም ከቴክኖሎጂ ጋር እንዲተዋወቁ ያደርጋቸዋል፡፡ በሀገር በቀል ሙያዎች ላይ ለተሰማሩት በይበልጥ ኮሌጁ የሚያደርግላቸው ድጋፍ ቴክኒካል ስልጠና ብቻም ሳይሆን የካይዘን አተገባበር ላይ ጭምር ትኩረቱን እንደሚያደርግ ገልጻለች፡፡

እስካሁን በተሰራው ስራ በተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በድጋፍ ማዕቀፍ ተጠቃሚ የሆኑ ማህበራት የምርትና ምርታማነት አቅማቸውን በማጠናከራቸው ኢኮኖሚያዊ እድገት ማሳየት ችለዋል፡፡ በርካቶች ከጥቃቅንና አነስተኛ ወደ ኢንዱስትሪ ደረጃ ለመሸጋገር ችለዋል፡፡ ሀገር በቀል የእውቀት ባለቤቶችን በመደገፍ ሂደት ውስጥ የፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች ሚና እጅጉኑ የላቀ ነው፡፡

# ኪነ ጥበባዊ መረጃዎች




ፎቶ- ከገፀ ድር
በከተማችን ከተዘጋጁ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች በከፊል

በጊዜው አማረ

በመዲናችን አዲስ አበባ ባሳለፍነው ሳምንት የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል። ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም መሰል መሰናዶዎች ይቀርባሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል መጽሐፍ፣ የጥበብ አውደ ርዕይ እና የቴአትር መርሃ ግብር ይገኙበታል። ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡

## መጻሕፍት

ወጣቱ ደራሲ ናትናኤል ቀረዓለም፣ በዛሬው ዕለት የመጽሐፍ የፊርማ ሥነ ሥርዓት ያከናውናል፡፡ ይህ የፊርማ መርሃ ግብር የሚካሄደው በቅርቡ በለገሃር ተወልደ ህንጻ ተመርቆ ሥራ በጀመረው አዲሱ የጃዕፈር መጽሐፍ መደብር ሲሆን፣ ከቀኑ 8፡00 ሰዓት እስከ 10፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ለአንባቢያን ፊርማውን ያበረክታል። ዝግጅቱ ለሥነ ጽሑፍ አፍቃሪያንና መታደም ለሚፈልጉ በሙሉ ክፍት መሆኑ ተገልጿል። ደራሲው “ዛሬ ቅዳሜ አይደለም”፣ “እውነት አዛምድ” እና “ትናንትና እመጣለሁ” የተሰኙ መጻሕፍትም ለንባብ አብቅቷል።

በሌላ መረጃ “ሮድ ቱ ዲትሮይት” መጽሐፍ ተመርቆ ለንባብ በቅቷል። በአውቶሞቲቭ ኢንዱስትሪ ውስጥ ለግማሽ ክፍለ ዘመን ገደማ የዘለቀ ሙያዊ ተሞክሮ ባላቸው አሸናፊ ጸጋዬ (ዶ/ር) የተጻፈው ይህ መጽሐፍ የዘርፉን የቴክኖሎጂ ሽግግርና የወደፊት አቅጣጫ የሚቃኝ ነው ተብሏል፡፡

መጽሐፉ፣ የአውቶሞቲቭ ዓለም ከተለምዷዊ ሜካኒካል አሠራር ወደ ዘመናዊው የኤሌክትሪክ እና ራስ-አገዝ (Autonomous) ቴክኖሎጂዎች እያደረገ ያለውን ሽግግር በስፋት የሚዳስስ ነው፡፡ በቀጣይ በአማርኛ ቋንቋ ተተርጉሞ ለገበያ እንደሚቀርብም ተገልጿል፡፡ አሸናፊ ፀጋዬ (ዶ/ር) በአውቶሞቲቭ ኢንዱስትሪ ውስጥ ለ48 ዓመታት በተለያዩ ከፍተኛ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ያገለገሉ ሲሆን፣ በተለይም በዘርፉ በነበራቸው ዓለም አቀፍ ግንኙነትና የምክር አገልግሎት ይታወቃሉ፡፡

## የሥነ ጥበብ አውደ ርዕይ

“በሰማይ እና በምድር መካከል” የተሰኘ የስዕል አውደ ርዕይ ተከፈተ፡፡ የሰዓሊ መላኩ አየለ ሥራዎች የቀረቡበት ይህ አውደ ርዕይ እስከ ሚያዝያ 19 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ በዕይታ ላይ ይቆያል። አውደ ርዕዩ የሚታየው ሀያት ሪጀንሲ ሆቴል በሚገኘው ፈንድቃ የባህል ማዕከል ሲሆን መግቢያው በእስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን በኩል መሆኑ ተገልጿል፡፡

በሌላ መረጃ “የመንደር ሹክሹክታ፡ ትዝታ እና ንብረት” የተሰኘው የስዕል አውደ ርዕይ በነገው ዕለት ይጠናቀቃል። የሚኪያስ አበራ የግል የሥዕል ኤግዚቢሽን የሆነው ይህ አውደ ርዕይ የማህበረሰቡን አኗኗር፣ ታሪክ፣ ሕይወት እና ተስፋ የሚያሳዩ ሥራዎች የቀረቡበት ሲሆን እየታየ የሚገኘው ቦሌ፣ ብሪቲሽ ኢንተርናሽናል ስኩል አጠገብ ኬኬር ሆምስ 2ኛ ፎቅ በሚገኘው አርታዊ ጋለሪ ውስጥ ነው፡፡

በተጨማሪም የሰዓሊና ቀራጺ ታምራት ገዛኸኝ ሥራዎች የቀረቡበት “ኩይሳ” የቅርጻ ቅርጽ አውደ ርዕይ በዕይታ ላይ ነው፡፡ ይህ አውደ ርዕይ ከተለያዩ የወዳደቁ ቁሳቁሶች የተሰሩ ልዩ የጥበብ ውጤቶች ለተመልካች የቀረቡበት ነው፡፡ አውደ ርዕዩ እስከ ሚያዝያ 19 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ ለሕዝብ ክፍት ሆኖ የሚቆይ ሲሆን ቦታው ደግሞ ብስራተ ገብርኤል፣ ላፍቶ ሞልን አለፍ ብሎ በሚገኘው ሚካኤል ጸጋዬ ክሬቲቭ ስቱዲዮ ነው፡፡


## የቴአትር መርሃ-ግብር

“አዮ ቦራ” የአፋን ኦሮሞ የልጆች ቴአትር በህፃናት እና ወጣቶች ቴአትር ቤት ዘወትር ቅዳሜ ከ4:00 ሰዓት ጀምሮ ከልዩ ልዩ ጨዋታዎች ጋር ይቀርባል። “የሰማይ ልጆች” ቴአትር ደግሞ በዚሁ ቴአትር ቤት ዘወትር እሁድ ከ4:00 ሰዓት ጀምሮ ከልዩ ልዩ ጨዋታዎች ጋር ይቀርባል፡፡

# የቁጥር ጨዋታ


## የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር። የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ የመጀመሪያው ከላይ እና በስተቀኝ ያሉትን ቁጥሮች ከደመርን በኋላ በግራ ባለው ቁጥር ስናባዛው መሀለኛውን ቁጥር ይሰጠናል፡፡ ለምሳሌ የመጀመሪያው ባለሶስት ጎን $2+3\times1=5$ ይሆናል፡፡ በዚህ አመክንዮ መሰረት የመጨረሻው $2+6\times3=24$ ይሆናል። ስለዚህ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛ ቁጥር **24** ነው።




## የዛሬው የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት ዕትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# የዓለም ዝነኞች ተመራጭ መዳረሻ

**በጊዜው አማረ**

አዲስ አበባ ስሟን መመጠን ከጀመረችባቸው ጥቂት ዓመታት ወዲህ፣ ከተማዋን የሚያውቃት ሰው እንኳን ሊያስታውሳት እስከሚቸገር ድረስ በከፍተኛ ፍጥነት እየተለወጠች ትገኛለች። "አሮጌውን በማፍረስ አዲሱን መተካት" ብቻ ሳይሆን፣ ነባሩን ማንነት ከዘመናዊነት ጋር የማጣመር ጥበብ የታየበት ይህ የለውጥ ጉዞ፣ መዲናዋን በአፍሪካ መድረክ ያላትን ተሰሚነት በውበቷም እንዲደገፍ እያደረገው ነው። ይህ ለውጥ ከተማዋን ለነዋሪዎቿና ለጎብኚዎች ምቹ የሆነች የመኖሪያና የሽርሽር እንድትሆን አድርጓታል።

የከተማዋ አዲስ ገጽታ በተለይ በኮሪደር ልማት ፕሮጀክቶች አማካኝነት የተገለጠ ሲሆን፣ ሰፋፊ፣ ለእግረኛ እና ተሽከርካሪ ምቹ የሆኑ መንገዶች የአዲስ አበባን የከተማ ልማት ደረጃ ከፍ አድርገውታል። እነዚህ በዘመናዊ መብራቶችና በአረንጓዴ ተክሎች መታጀባቸው፣ ከተማዋ በቀንም ሆነ በሌሊት እኩል ውበት እንዲኖራት አስችሏታል። ይህ የመሰረተ ልማት ግንባታ የከተማዋን የትራፊክ ፍሰት ከማሳለጡ ባለፈ፣ ነዋሪው በነፃነት ወጥቶ እንዲንሸራሸርና በከተማው እንዲኮራ የሚያደርግ ሥነ-ልቦናዊ ለውጥ አምጥቷል ማለት ይቻላል።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት የተገነቡት ግዙፍ የመዝናኛ ፓርኮች አዲስ አበባን ውብ ከማድረግ ባለፈ፣ ከተማዋን "የአረንጓዴነት" ተምሳሌት አድርገዋታል። በፋውንቴን ከታጀቡ የመዝናኛ ፓርኮች በተጨማሪ እንደ አንድነትና እንጦጦ ፓርኮች እንዲሁም ወዳጅነት አደባባይ ያሉ ስፍራዎች ተፈጥሮን ከታሪክና ከዘመናዊ ጥበብ ጋር አጣምረው የያዙ በመሆናቸው፣ ለመዲናዋ ነዋሪዎችና እንግዶች ዋነኛ የመዝናኛ አማራጭ ሆነዋል። እነዚህ ስፍራዎች ነዋሪዎች ጊዜ የሚያሳልፉባቸው፣ ወጣቶች የሚዝናኑባቸውና የውጭ ሀገር ዜጎች የኢትዮጵያን እንግዳ ተቀባይነትና ውበት የሚመሰክሩባቸው የቱሪዝም ማዕከላት ሆነው እያገለገሉ ይገኛሉ።

ይህ አስደናቂ ለውጥና ውበት በርካታ ታዋቂ የፖለቲካ መሪዎችን፣ የዓለም አቀፍ ድርጅት ኃላፊዎችንና ዲፕሎማቶችን ቀልብ እየሳበ ይገኛል። አዲስ አበባ ዛሬ ላይ ትልልቅ አህጉርና ዓለም አቀፍ ጉባኤዎችን በብቃት የምታስተናግድ ብቻ ሳትሆን፣ መሪዎች በትርፍ ጊዜያቸው በፓርኮቿ ተዝናንተውና በውብ ጎዳናዎቿ በእግር ተጉዘው ስለለውጧ የሚመሰክሩላት ከተማ ሆናለች። ይህ ደግሞ የከተማዋን ዲፕሎማሲያዊ ተሰሚነትና የቱሪስት ፍሰት በከፍተኛ ደረጃ እንዲጨምር አድርጎታል።

ባለፉት ዓመታት በመዲናዋ የታየው ውበትና ጽዳት የዓለም አቀፍ ዝነኞችን ትኩረት የሳበ ሆኗል። ዓለም አቀፍ የጥበብ ሰዎች የከተማዋን አዲስ ገጽታ እንደ ስራዎቻቸው መነሳሻ እየተጠቀሙበት ይገኛሉ። በዘመናዊ የግድግዳ ስዕሎች (Murals) ያጌጡ ጎዳናዎች፣ የጥበብ ጋለሪዎችና ለኪነ-ጥበብ ስራዎች ምቹ የሆኑ ክፍት ቦታዎች መበራከታቸው፣ አርቲስቶችና የፈጠራ ባለሙያዎች ወደ መዲናዋ እንዲጎርፉ አድርጓል። አዲስ አበባ ዛሬ ላይ ለፊልም ቀረጻ፣ ለሙዚቃ ቪዲዮዎችና ለፎቶ ግራፍ ጥበብ ተመራጭ መዳረሻ ሆናለች፤ ይህም ከተማዋን የታሪካዊና ዘመናዊ ጥበብ መገናኛ አድርጓታል።







ፎቶ- ከገፀ ድር
በተለያዩ ጊዜያት አዲስ አበባን የጎበኙ ዓለም አቀፍ ዝነኞች

የከተማዋ ልማትና ለውጥ ለውበቷና ለመዝናኛ ተመራጭነቷ ትልቅ ድርሻ አበርክቷል። ቀደም ሲል የቆሻሻ መጣያና የመጥፎ ሽታ ምንጭ የነበሩ የወንዝ ዳርቻዎች ዛሬ ወደ ውብ የልማት ኮሪደሮችና የመዝናኛ ስፍራዎች መቀየራቸው፣ የአዲስ አበባን የጽዳት ደረጃ ወደ አዲስ ከፍታ አሳድጎታል።

ከ15 ዓመታት በላይ በአስጎብኝነት እየሰሩ የሚገኙት ወይዘሮ ሶስና ሙሉጌታ ቀደም ሲል ወደ አዲስ አበባ ለስብሰባና ለተለያዩ ጉዳዮች የሚመጡ እንግዶች ቆይታቸውን እንዲያራዝሙ መጠየቅ አዳጋች፣ ጎብኝዎችም በከተማዋ እንደ ልብ የሚዝናኑባቸውና ጊዜ የሚያሳልፉባቸው ፓርኮችም ሆኑ ሌሎች መዳረሻዎች ባለመኖራቸው ቅሬታቸውን ይገልጹ ነበር። ይህ ሁኔታ አዲስ አበባን ለስራ እንጂ ለቱሪስት መስህብነትና መዝናኛነት እንዳትመረጥ አድርጓት እንደቆየ ተናግረዋል።

ወይዘሮ ሶስና በአሁኑ ወቅት በከተማዋ የተገነቡት አዳዲስና ዘመናዊ የመዝናኛ ስፍራዎች የጎብኝዎችን ጥያቄ በሚገባ የመለሱና ለውጭ እንግዶች መዳረሻ መሆናቸውን ያስረዳሉ። እነዚህ አዳዲስ መዳረሻዎች የከተማዋን ገጽታ ከመቀየር ባለፈ፣ የውጭ አገር ዜጎችም ሆኑ የአገር ውስጥ ጎብኝዎች ጊዜያቸውን በደስታ የሚያሳልፉባቸው አማራጮችን በስፋት ፈጥረዋል። በአጠቃላይ ባለፉት ዓመታት በመዲናዋ የተሰሩት ስራዎች በርካታ የውጭ የኪነ ጥበብ ሰዎችና ጎብኝዎችን ቀልብም ጭምር ለመሳብ ችለዋል፡፡

## የመዲናዋ የጥበብ እንግዶችና ምስክርነታቸው

ባለፉት ስምንት ዓመታት የተከናወኑ ተግባራት ከተማዋን የአፍሪካ የዲፕሎማሲ መድረክ ብቻ ሳትሆን የጥበብና የውበት ማዕከል እንድትሆን አድርጓታል። ለኑሮ ምቹ ያልነበሩ የከተማዋ ስፍራዎች በአሁኑ ወቅት በዘመናዊ የመሠረተ ልማት ግንባታዎችና በፈጠራ ስራዎች እየተተኩ ይገኛሉ። ይህ ሽግግር የአገር ውስጥ ባለሙያዎችን ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ስም ያላቸው የኪነ-ጥበብ ሰዎችን ትኩረት የሳበና ከተማዋን በአዲስ መነጽር እንዲመለከቷት ያስገደደ ትልቅ ስኬት ሆኖ ተመዝግቧል።

መዲናዋን የጎበኙ የጥበብ ሰዎች በሰጡት ምስክርነት በዋናነት የሚጠቀሰው የአረንጓዴ ልማትና የፓርኮች ግንባታ የከተማዋን ድባብ ሙሉ በሙሉ መቀየሩን ነው። እንደ አንድነት እና እንጦጦ ፓርኮች፣ ወዳጅነት አደባባይ ያሉ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ ውበትን ያጣመሩ ፓርኮች ለከያንያኑ የፈጠራ መነሳሳትን የሚፈጥሩ ስፍራዎች ሆነዋል።

ከውበት ባሻገር፣ ከተማዋ ለዓለም አቀፍ የኪነ-ጥበብ መድረክነት ያላትን ብቃት በተግባር እያረጋገጠች ትገኛለች። በተለይ የዓድዋ ድል መታሰቢያ እና ዘመናዊው የቤተ-መጻህፍት ግንባታዎች የጥበብ ሰዎች ስለ ኢትዮጵያ ታሪክና ስልጣኔ ያላቸውን ግንዛቤ ከፍ አድርጎታል። ይህም ዝነኛ ድምፃውያን፣ የፊልም ባለሙያዎችና ዲዛይነሮች ስለ ከተማዋ እድገትና ንጽህና በአድናቆት እንዲናገሩ በር ከፍቷል። ባለፉት ዓመታት አዲስ አበባን ደቡብ ሱዳናዊቷን አርቲስት ስላቲን ፒሮን እና ዓለም አቀፋዊው ይዘት ፈጣሪን አይሾው ስፒድን ጨምሮ በርካታ የጥበብ ሰዎች መዳረሻ መሆን ችላለች፡፡

ለአብነትም ስመጥሯ የማሊ ሙዚቀኛ ኡሙ ሳንጋሬ በአዲስ አበባ ያደረገችው ጉብኝት፣ የመዲናዋን አዲስ ገጽታ ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ዳግም ያስተዋወቀ አጋጣሚ ነበር። ድምጻዊቷ በእንጦጦ ፓርክ፣ በሙዚየሞችና በተለያዩ የልማት ስፍራዎች ተገኝታ ባደረገችው ምልከታ እጅግ ተደስታለች። በተለይም በአጭር ጊዜ ውስጥ የተከናወነው የከተማዋ ለውጥ ከጠበቀችው በላይ ሆኖ እንዳገኘችው በመግለጽ፣ የአዲስ አበባን ፈጣን ሽግግርና ውበት በአድናቆት መስክራለች።

> **ባለፉት ስምንት ዓመታት የተከናወኑ ተግባራት ከተማዋን የአፍሪካ የዲፕሎማሲ መድረክ ብቻ ሳትሆን የጥበብና የውበት ማዕከል እንድትሆን አድርጓታል። ይህም የአገር ውስጥ ባለሙያዎችን ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ስም ያላቸው የኪነ-ጥበብ ሰዎችን ትኩረት የሳበና ከተማዋን በአዲስ መነጽር እንዲመለከቷት ያስገደደ ትልቅ ስኬት ሆኖ ተመዝግቧል**

ኡሙ ሳንጋሬ የአዲስ አበባን ለውጥ የገለጸችው "በኒው ዮርክ ከተማ ያለሁ ያህል ተሰምቶኛል" በማለት ነበር፡፡ ይህ አስተያየቷ አዲስ አበባ የደረሰችበት የለውጥ ደረጃ፣ የመዝናኛ አማራጮች እና የአረንጓዴ ልማት ስራዎች ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቁ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ነው። እንዲህ ያሉ የኪነ-ጥበብ ሰዎች ምስክርነት ከተማዋ ለቱሪዝም ያላትን ተመራጭነት ከማሳደጉም በላይ፣ አዲስ አበባ የታሪክና የዘመናዊነት መገናኛ መሆኗን በተግባር የሚያሳይ ነው።

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

ከአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየአስራ አምስት ቀኑ የሚቀርብ

# ብልሹ አሰራሮችን ለመቅረፍ የአካዳሚው አበርክቶ

- **አካዳሚው የአመራሩንና የባለሙያውን የአስተሳሰብና የክህሎት አቅም በስልጠና በመገንባት ከብልሹ አሰራር የጸዳ የመንግሥት አገልግሎት እንዲሰፍን እያደረገ መሆኑ ተገልጿል**

**በሸዋርካብሽ ቦጋለ**

በመንግሥታዊ ተቋማት ውስጥ የሚስተዋሉ ብልሹ አሰራሮች የዜጎችን መብት ከማጓደል ባለፈ በሀገር ኢኮኖሚና ማህበራዊ መስተጋብር ላይ ከፍተኛ ጠባሳ ጥለው ያልፋሉ። እነዚህን ችግሮች በዘላቂነት ለመቅረፍ የአሰራር ስርዓቶችን ወደ ዲጂታል አማራጮች ማሸጋገር ተመካሪ ነው። ግልጽነትን እና ተጠያቂነትን የሚያሰፍኑ እንዲሁም አገልግሎትን በቴክኖሎጂ የሚያሳልጡ የአሰራር ለውጦች በአገልግሎት አሰጣጥ ውስጥ የሚስተዋሉ ቀዳዳዎችን ለመድፈን ወሳኝ መሳሪያዎች ናቸው።



ፎቶ- ከገፀ ድር
የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ በሚሰጣቸው ስልጠናዎች ብልሹ አሰራሮች እየተቃለሉ ይገኛሉ

ይሁን እንጂ ስርዓቱ ብቻውን ውጤታማ ሊሆን አይችልም፤ ስርዓቱን የሚመራና የሚያስፈጽም ብቁ የሰው ኃይል ማፍራት የግድ ይላል። በዚህ ረገድ የአመራር አካዳሚዎች ሚና የጎላ ነው። አካዳሚዎቹ በተግባር የተፈተኑና የህዝብን አገልጋይነት ስሜት የተላበሱ መሪዎችን በማፍራት ረገድ የለውጥ ማዕከል መሆን ይጠበቅባቸዋል። አመራሩና ባለሙያው በስነ-ምግባር የታነጸና ለለውጥ ዝግጁ ሲሆን፣ የተቀረጹት የአሰራር ስርዓቶችም መሬት ወርደው ውጤት ማምጣት ይጀምራሉ።

በመሆኑም ብልሹ አሰራርን ለማክሰም የሚደረገው ትግል በሁለት ዘርፎች መቃኘት አለበት። በአንድ በኩል ዘመናዊና ግልጽ የአሰራር መመሪያዎችንና የቴክኖሎጂ መሰረተ-ልማቶችን መዘርጋት ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የአመራር አካዳሚዎች የለውጥ አጋፋሪ የሆኑ አመራሮችንና ባለሙያዎችን በማብቃት ተቋማዊ ባህልን እንዲቀይሩ ማስቻል ነው። እነዚህ ሁለት ተግባራት ተቀናጅተው ሲሄዱ ብቻ የህዝብን እርካታ የሚያረጋግጥና ከብልሹ አሰራር የጸዳ ቀልጣፋ የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት መገንባት ይቻላል።

ቀደም ባሉት ጊዜያት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር የሚገኙ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት የተገልጋዮች እንግልት በስፋት ይስተዋል ነበር። አንዱ የችግሩ መነሻ ደግሞ በርከት ባሉ አመራሮችና ባለሙያዎች ዘንድ የነበረው የስነ ምግባር፣ እውቀትና ዝግጁነት ጉድለት ነው፡፡

አሁን ግን በአገልግሎት አሰጣጥ በኩል በርከት ባሉ ተቋማት ዘንድ መሻሻሎች እየታዩ ነው። ለዚህ መሻሻል ደግሞ የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ የጀመራቸው የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች የራሳቸውን በጎ አስተዋፅኦ እያበረከቱ መሆናቸው ነው የሚነገረው፡፡ አካዳሚው የተቋቋመበት ዋነኛ ዓላማ የመዲናዋን አስፈጻሚ አካላት አቅም በመገንባት ቀልጣፋና ውጤታማ የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት እንዲሰፍን ማድረግ ስለመቻሉ ከአካዳሚው ያገኘነው መረጃ ያመላክታል።

በአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ የስራ አመራር ስልጠና ዳይሬክተር ምህረት ሃ/መስቀል (ዶ/ር)፣ አካዳሚው በሚሰጣቸው ስልጠናዎች አማካኝነት በተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ በርካታ ለውጦች መታየታቸውን ገልፀዋል፡፡ አክለውም፣ ስልጠናዎች በተሰጡ ቁጥር የስልጠናውን ሁኔታ ሰልጣኞች ስልጠናው ላይ እያሉ ከመለካቱም ሌላ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ደግሞ ስልጠናው ውጤታማ መሆኑ በጥናት የሚረጋገጥበት አግባብ መኖሩን በመጠቆም በዚህም መሻሻሎች መኖራቸው መረጋገጡን ተናግረዋል፡፡

የአካዳሚው ዋንኛ ስራ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅምን መገንባት ነው። ከዚህ አኳያ ከሚሰጣቸው በርካታ ስልጠናዎች አንዱ የአመራር አካዳሚ እንደመሆኑ ተቋማትንና ለተቋማት ስኬት አስተዋፅኦ ላላቸው ባለሞያዎች፣ ሿሚ አመራሮች፣ ዳይሬክተሮች እና ቡድን መሪዎችን ለማብቃት የሚሰጠው ስልጠና ተጠቃሽ ነው ብለው፣ ይህም ብልሹ አሰራሮችን በማቃለል ረገድ የጎላ ሚና እንዳለው አውስተዋል፡፡

አካዳሚው በሚሰጣቸው የአገልግሎት አሰጣጥና ደንበኛ አያያዝ ስልጠናዎች በተለይ ሙያዊ ስነ ምግባሮች፣ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅምን ሊገነቡ የሚችሉ የባህሪ ግንባታዎች፣ ሰራተኛን ማትጋትና የአመራር ክህሎት ስልጠናዎች መስጠታቸው አገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል ከፍተኛ ድርሻ ነበራቸው፡፡

ስልጠናዎቹ ተቋማት ከባህላዊ አሰራር ወጥተው ወደ ዘመናዊ፣ ፈጣንና ደንበኛ ተኮር አገልግሎት እንዲሸጋገሩ እያደረገ ነው ያሉት ዳይሬክተሯ፣ ብልሹ አሰራርን ለመከላከልና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የአገልግሎት አሰጣጥ ስልጠናው ትልቅ አስተዋፅኦ አለው ብለዋል፡፡

ይህን ስልጠና በዚህ ዓመት ብቻ በተቋማት ደረጃ ከ8 ሺህ ባላይ አመራሮች፣ ዳይሬክተሮች እና ባለሙያዎች እንዲሁም ከ3 ሺህ የሚበልጡ ወደፊት አመራር ሊሆኑ የሚችሉ ኤክስፐርቶች ሰልጥነዋል፡፡

በቀጣይም በየደረጃው ያሉ የአገልግሎት አሰጣጥ ክፍተቶችን ሙሉ በሙሉ ለመቅረፍ ቀጣይነት ያለው ክትትልና ስልጠና እንደሚሰጥ ጠቁመው፣ ተቋሙ ስልጠና እንደሰጠ ወዲያውኑ በሚያደርገው ምልከታና ሰልጣኞች በሚሰጡት ግብረ መልስ ስልጠናውን ወስደው ለአፈፃፀም ክፍተት መሙያና ለራሳቸውም ሆነ ለተቋማቸው የሚሆናቸውን ስንቅ ይዘው እንደሚሄዱ ነው፡፡

ከባለፈው ዓመት ተሞክሮ በመነሳት መናገር እንደሚቻለውም በአገልግሎት አሰጣጥ ረገድ የተሻለ አፈፃፀም መኖሩን ጠቁመው፣ ሰዎች በተመደቡበት ስራ በትኩረትና በትጋት የመስራት ዝንባሌ ከመኖሩም ሌላ የስራ ሰዓትን ቢሮ በመቆየት በአግባቡ በመጠቀም፣ተገልጋዮችን በቀናነት በማገልገል ረገድ አበረታች ውጤት መኖሩን አስረድተዋል፡፡

አንዱ የስልጠናው መሪ ቃል “ከፍ ለማለት ዝቅ ማለትን ልመድ” የሚል ሲሆን፣ አገልግሎት ስንሰጥ እኛም በሌላ ተቋም ስንሄድ ተገልጋዮች መሆናችንን እኛ ጋር የሚመጡትም ተገልጋዮች መሆናቸውን ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡

የመንግስት ሰራተኛ በመንግሰት እና በማህበረሰቡ መካከል እንደድልድይ ሆኖ የሚያገናኝ ነው ያሉት ዳይሬክተሯ፣ በመንግስት ተቋማት የአገልግሎት መጓደል ቢያጋጥም በመንግሰት እና በማህበረሰብ መካከል ያለው ግንኙነት ይቋረጣል ከሚለው አንፃር እንደሚለካም ተናግረዋል፡፡

እንደ ዳይሬክተሯ ገለፃ፣ አካዳሚው በተለይም በመንግሰት ተቋማት በሚሰጣቸው ስልጠናዎች የአመራር ክህሎትና የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት የተቻለ ሲሆን፣ አካዳሚው አገልጋይነት ላይ ያተኮረ ስልጠና በመስጠቱ፣ በቢሮክራሲው ውስጥ የነበረውን ‘ባለስልጣን ነኝ’ ከሚል አስተሳሰብ ወደ ‘የህዝብ አገልጋይ ነኝ’ ወደሚል መንፈስ እንዲቀየር አስችሏል።

ይህም ደንበኞችን በአክብሮት የማስተናገድ ባህልን አዳብሯል። እንደአጠቃላይ ሲታይ በተቻለ መጠን አገልግሎት ለመስጠት ቀናነቱና ዝግጁነቱ መኖሩ በተለያየ መልኩ የተረጋገጠ ቢሆንም በአንድ ጊዜ ስልጠና ሁሉም ነገር ይቀየራል ብሎ መደምደም አይቻልም፡፡

እንደ ከተማ አስተዳደርም በዚህ ዓመት ክፍተቶች ናቸው ተብለው ትኩረት ይደረግበት ተብሎ የተሰጠን አገልግሎት አሰጣጥ ላይ በሰፊው ችግር በመኖሩ ነው። በዚያ መሰረትም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት ቢሮ፣ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ቢሮ፣ የከተማ ፕላን ልማት ቢሮን ጨምሮ በርካታ ተቋማትና ክፍለ ከተሞች ስልጠናውን በስፋት ወስደዋል፡፡

ለተቋማቱ በሚሰጠው ስልጠና ሌላው ለውጥ መምጣት የተቻለው በቴክኖሎጂ አጠቃቀምና ዲጂታላይዜሽን ዘርፍ ላይ ሲሆን፣ አመራሩ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ አገልግሎት እንዲሰጥ በመሰልጠኑ ወረቀትን የቀነሱ አሰራሮች ከመስፋታቸውም ሌላ የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደቶች በሶፍትዌር እንዲታገዙ በማድረግ የሰው ግንኙነትን በመቀነስ ለሙስና ያለውን ተጋላጭነት መቀነስ መቻሉን ለስልጠናው ስኬታማት እንደማሳያ አንስተዋል።

ከምንም በላይ ደግሞ ስማርት ሲቲ (ብልህ መዲና) የመገንባት ራዕይን ወደ ተግባር ለመለወጥ የሚያስችል የቴክኖሎጂ ግንዛቤ ተፈጥሯል ብለው፣ የውሳኔ አሰጣጥ ፍጥነትና ግልጽነት በመፈጠሩ ቀደም ሲል ለቀናት ወይም ለሳምንታት ይንከባለሉ የነበሩ ጉዳዮችን በአመራሩ የጊዜ አጠቃቀምና የውሳኔ አሰጣጥ ስልጠና ምክንያት ማስቀረትና አላስፈላጊ የቢሮክራሲ ሰንሰለቶች መቀነስ ብሎም አገልግሎት ፈላጊዎች ጉዳያቸው በምን ደረጃ ላይ እንዳለ የሚያውቁበት ግልጽነት መስፈኑንም ተናግረዋል።

አካዳሚው ስራን በዕቅድና በውጤት የመመዘን ስልት ላይ ትኩረት በማድረጉም ተቋማት ግልጽ የሆነ ግብ እንዲኖራቸው ብሎም የሰራተኞች የስራ አፈጻጸም በውጤት ላይ ተመስርቶ እንዲለካ በማድረግ የውድድር መንፈስ እንዲፈጠር ረድቷል።

የቅሬታ አፈታት ስርዓት መሻሻልም አካዳሚው ለተቋማት በሚሰጣቸው ስልጠናዎች የመጣ ለውጥ እንደሆነ የሚገልፁት ዳይሬክተሯ በተለይ አመራሩ የህዝብን ድምጽ እንዲያዳምጥና ለቅሬታዎች ፈጣን ምላሽ እንዲሰጥ በመሰልጠኑ፣ በተቋማት ውስጥ የቅሬታ መቀበያና መፍቻ መንገዶች ይበልጥ ተደራሽ መሆናቸውን አስረድተዋል።

# ልጆች፡- ሃሳባችሁን የመግለፅ ችሎታችሁን እንዴት እያዳበራችሁት ነው?

**በፋንታነሽ ተፈራ**

ልጆች፤ በቤታችሁም ሆነ በትምህርት ቤታችሁ ልትገልጹት፣ ልትናገሩት፣ ልትጠይቁት... የምትፈልጉት ሀሳብ እንዳለ ይታወቃል፡፡ ከዚህ አንጻር ያላችሁ ልምምድ ምን ይመስላል? ሐሳብን መግለፅስ ምን ጥቅም ያስገኛል? የሚለውን ያነጋገርናቸውን ልጆች ተሞክሮ በሚያሳይ መልኩ እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡



ፎቶ- በገነት ወንድሙ

ከግራ ወደ ቀኝ ተማሪ ብሌን ሃብታሙ ፣ ተማሪ ኤሊያስ ገመቹ ፣ ተማሪ መታሰቢያ መንገሻ እና ተማሪ ኤርሚያስ ይርጋለም

ኤሊያስ ገመቹ እባላለሁ። ቁስቋም ጣይቱ ብጡል ቅድመ አንደኛ፣ አንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ6ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ፡፡ 12 ዓመቴ ነው፡፡ ክፍል ውስጥ መምህራንን በግልጽነት ያልገባኝን እጠይቃለሁ፡፡ የተለያዩ ድራማዎችን መድረክ ላይ እየወጣሁ እሰራለሁ፡፡ በሁሉም ነገር መሳተፍ ደስ ይለኛል፡፡

ሃሳቤን በግልጽነት መናገር መቻሌ የተለያዩ ጥቅሞችን አስገኝቶልኛል። ከነዚህም ውስጥ ክፍል ውስጥ በምሳተፈው ተሳትፎ ግልፅ ያልሆነልኝን ነገር እንዳውቅ አድርጎኛል፡፡ በራስ መተማመኔን ከጊዜ ወደ ጊዜ ጨምሮልኛል፡፡ ከመምህራንና ጓደኞቼ ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖረኝ ረድቶኛል፡፡ ወደፊት ተዋናይ መሆን እፈልጋለሁ፡፡ ለዚህም ዛሬ ላይ በነፃነት ሃሳቤን መግለፅ መቻሌ ያግዘኛል ብዬ አስባለሁ፡፡

ብሌን ሃብታሙ እባላለሁ፤ 15 ዓመቴ ነው፡፡ ከዚህ በፊት ሃሳቤን በነፃነት መግለፅ አልችልም ነበር፡፡ በክፍል ውስጥ ውጤት የሚሰጥበት ጥያቄ ሲጠየቅ እንኳን መልሱን ባውቀውም አልመልስም። ሀሳቤን በግልጽ ባለመናገሬ ይቆጨኛል። ከዚህ ለመውጣት የራሴን ጥረት አድርጌያለሁ፤ ለውጥም አምጥቻለሁ። አሁን ክፍል ውስጥ ጥያቄ ሲጠየቅ መልስ እመልሳለሁ። በተለያዩ ክበባት ላይ የመሳተፍ፣ ግጥሞችን የማቅረብ እንዲሁም ውዝዋዜ ላይ የመሳተፍ ልምዴን እያዳበርኩ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ሐሳቤን መግለፄ ከሌሎች ጋር ያለኝን ግንኙነት እንዲሁም በራስ መተማመኔን አዳብሮልኛል፡፡ ሐሳብን መግለፅ አዕምሮ በነፃነት እንዲያስብ ስለሚያደርግ አዳዲስ ነገሮችን ለመፍጠር ያስችላል፡፡ ወደፊት ለምኖረው ኑሮ መሰረት ይሆነኛል ብዬ አስባለሁ፡፡

ኤርሚያስ ይርጋለም እባላለሁ፡፡ 12 ዓመቴ ነው፡፡ የምማረውም ቁስቋም ጣይቱ ብጡል ቅድመ አንደኛ፣ አንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው። ክፍል ውስጥ እሳተፋለሁ፤ ያልገባኝን እጠይቃለሁ፤ ቤተሰቦቼ እንዲያደርጉልኝ የምፈልገውን በነፃነት እጠይቃለሁ፡፡ ሃሳቤን በነፃነት መግለፅ መቻሌ የንግግር ችሎታዬን ለማዳበር ረድቶኛል፡፡

ስሜ መታሰቢያ መንገሻ ይባላል። 14 ዓመቴ ነው፡፡ ሐሳቤን ለመግለፅ አልቸገርም፤ በድፍረት እናገራለሁ። ከቤተሰቦቼ ጋር ሳልፈራ የገጠመኝን ወይም እንዲደረግልኝ የምፈልገውን እገልፃለሁ። ክፍል ውስጥ ያልገባኝ ነገር ሲኖር እጄን አውጥቼ እጠይቃለሁ፡፡ ሚኒሚዲያ ላይ እሳተፋለሁ፤ ተሳትፎዬ ጥሩ በመሆኑ ኃላፊነት ተሰጥቶኛል። እኔም ዘወትር ሰኞ የሚያቀርቡ ተማሪዎችን የመጋበዝ፣ ሰንደቅ ዓላማ የመስቀል ሥነ ስርዓት አስከብራለሁ፡፡ ይህ ሲሆን የመናገር ችሎታዬ እንዲዳብር አድርጎኛል፡፡ በፊት የነበረብኝ ሀሳቤን ያለመግለጽ ችግር ተወግዶልኛል፡፡ መብቴን እንድጠይቅና ተጠቃሚ እንድሆን ረድቶኛል፡፡ “ሌሎች ምን ይሉኛል” በሚል በግልጽነት ሳልናገር ብቀር ተጎጂ እንደምሆን ተገንዝቤያለሁ፡፡

ልጆች ሃሳባችሁን በነፃነት እና በግልጸኝነት መናገራችሁ አሁን ለምትማሩት ትምህርት ውጤታማ እንድትሆኑ ያደርጋችኋል።፡ ለወደፊት ስብዕናችሁና ለስኬታችሁ መሰረት የሚጥል ነው። ስለዚህ ልጆች ሀሳባችሁን በነፃነት የመግለጽ ባህላችሁን አዳብሩ እንላለን።

## 10 ልዩነቶችን ፈልጉ



## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**ህይወት የለውም ሌት ቀን የሚሄድ**

**መልስ፡-** ሐ. ነፋስ

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**ራሱ ሳይቀምስ የቆረሰውን ለሌላ ያጎርስ**

ሀ. እናት
ለ. አባት
ሐ. እጅ

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ::**

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ መሶብ ዲጂታል የአንድ ማዕከል የመንግስት አገልግሎት ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# በተግባር የተገለጠው የመሪነት ሚና

- **ከለውጡ መንግሥት ስኬቶች መካከል የ'አዲስ መሶብ' ዲጂታል የአንድ ማዕከል አገልግሎት እንደሚጠቀስ ተጠቁሟል**

**በደረጀ ታደሰ**

በመዲናዋ ብሎም በሀገር አቀፍ ደረጃ እየታዩ ላሉ ስኬቶች በወርሃ መጋቢት፣ በ2010 ዓ.ም. በይፋ ወደ መሪነት የመጡት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አሕመድ(ዶ/ር) ሚና የላቀ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ ታላቅ እና ገናና ታሪክ ያላት፣ በተፈጥሮ ጸጋዎች የተትረፈረፈች፣ ለም መሬትና ከፍተኛ የውሃ ሃብትን የያዘች፣ ወጣት የሠው ኃይል የሚኖርባት፣ በነጻነት ፋና ወጊነቷ በቀዳሚነት የምትጠቀስ ... አገር፡- ኢትዮጵያ፤ በድህነትና ኋላቀርነት መጠቀሷ ቁጭት የፈጠረባቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ቁጭታቸውን በተግባር ውጤት ለመበቀል ወዲያው ነበር ሥራ የጀመሩት፡፡ መደመር በሚለው ፍልስፍና፣ እንደ ሀገር ለዘመናት ከቆየንባቸው ችግሮች ለመላቀቅ የሚያስችሉ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን አመላክተዋል፡፡ በተለይ የመፍጠር፣ መፍጠን፣ ማብዛትና ማጥራት እሳቤን ተላብሶ ተግባራትን በቁርጠኝነት መፈፀም ለሀገር ዕድገትና ብልፅግና ቁልፍ መሣሪያ መሆኑን በመጽሐፎቻቸው እና በተለያዩ አግባብ በተደጋጋሚ ገልፀዋል፡፡

የመደመር ፍልስፍና በተግባር እየተገለጠባቸው ካሉ በርካታ ተግባራት መካከል የአዲስ መሶብ ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት እና መሰል የዲጂታል አሠራሮች ዕውን መሆን ይጠቀሳሉ፡፡ የ2018 ዓ.ም. የአዲስ ዓመት ልዩ ስጦታ ተደርጎ የሚቆጠረው፣ የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት፣ ጷጉሜን 5 ቀን 2017 ዓ.ም. በይፋ ተመርቆ ለአገልግሎት የበቃው፤ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ቀጥተኛ አመራርና ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወደ ስልጣን ከመጡ ጊዜ አንስቶ፣ የኢትዮጵያን ምጣኔ ሀብት ለማሳደግ ቴክኖሎጂን እንደ ዋና ሞተር መጠቀም ቁልፍ ጉዳይ ስለመሆኑ አፅንኦት ሰጥተው ተናግረዋል፤ ጽፈዋል፣ ስትራቴጂ ቀርፀዋል፣ ተግባራዊም እንዲሆን አመራር ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ፤ "ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025" የተሰኘውን ሰነድ እንዲዘጋጅ እና ተግባራዊ እንዲሆን የሠጡት አመራር እና ያስገኘው ውጤት ይጠቀሳል፡፡ ይህ ስትራቴጂካዊ አመራር ኋላቀርና ለሕዝብ ምሬት ምክንያት የሆኑ የመንግስት አገልግሎቶች፣ በቴክኖሎጂ እንዲታገዙ፣ እንዲዘምኑ፣ ወረቀት አልባ እና ከሰው ንክኪ ነፃ እንዲሆኑ በማድረግ ቢሮክራሲያዊ ማነቆዎች የተቀረፈላቸው፣ የተገልጋይ እርካታን ከፍ ያደረጉ አሠራሮችን የሚፈፅሙ ተቋማት እንዲፈጠሩ የሚያስችል ነው፡፡ አዲስ መሶብም የዚህ አመራር ውጤት ነው፡፡

የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ዋና መሥሪያ ቤት ለአገልግሎት ሲበቃ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና ከንቲባ አዳነች አቤቤን ጨምሮ ከፍተኛ የመንግስት አመራሮች መገኘታቸው ይታወሳል፡፡ ይህ መርሃ ግብር፤ የትናንት ቁጭት ምላሽ መስጫ ቁልፍ፣ የነገ ስኬት መሸጋገሪያ ተደርጎ መወሰዱን በዕለቱ የተላለፉ መልዕክቶች ይመሰክራሉ፡፡

በወቅቱ ከንቲባዋ ባስተላለፉት መልዕክት፤ አዲስ መሶብ፣ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ በተመረቀ ማግስት ለአገልግሎት መብቃቱን በመጥቀስ፣ የተገልጋዮችን እንግልት በመቀነስ ፈጣንና ጥራት ያለው አገልግሎት ለመስጠት እና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል ያስችላል፡፡ በሁሉም ክፍለ ከተሞች ቅርንጫፍ እንዲኖር ለማድረግ በትኩረት እንደሚሰራ ቃል ገብተዋል፡፡

በአዲስ ዓመት ዋዜማ የተገባው ቃል በተግባር ለመገለጥ ብዙ ጊዜ አልፈጀበትም፡፡ በአራዳ ክፍለ ከተማ የወጣው የአዲስ መሶብ ጀንበር፣ ቁርጠኛ አመራር በታየበት የቀን ከሌት ሥራ በውጤት እየሠፋና እየደመቀ መዳዙን ቀጥሏል፡፡ እንደ ከተማ ሁለተኛው የሆነው የአዲስ መሶብ ዲጂታል የመንግስት አገልግሎትን በቦሌ ቅርንጫፍ በመክፈት መስከረም 28 ቀን 2018 ዓ.ም. ለአገልግሎት መብቃቱ ይታወሳል። በሁለቱ ማዕከላትም በወራት ዕድሜ ውስጥ ከ100 ሺህ ለሚበልጡ ተገልጋዮች፤ አገልግሎት ማቅረብ ተችሏል፡፡ በአገልግሎቱም ለተገልጋዮች እጅግ ደስ የሚያሰኝ እርካታ እንደተፈጠረ፣ ከተገልጋዮች ግብረ መልስ ተረጋግጧል። ገና ከማለዳው የታየው ተስፋ ሰጪ ውጤት፣ በበጀት ዓመቱ ለአገልግሎት እንደሚበቁ ቃል የተገባላቸው ቅርንጫፎች በፍጥነትና በጥራት ሥራ እንዲጀምሩ አግዟል። በወርሃ መጋቢት ማጠናቀቂያ ቀናት ለአገልግሎት የበቁት ተጨማሪ ሦስት ቅርንጫፎች ለዚህ ማሳያ ናቸው፡፡ በአውቶብስ አማካኝነት ለማቅረብ በመጨረሻ ምዕራፍ ላይ የሚገኘው የተንቀሳቃሽ አዲስ መሶብ አገልግሎትም እዚህ ላይ የሚጠቀስ ነው፡፡

ቃል በተግባር የመገለጡን ብሥራት ከሠሞኑ ለአገልግሎት በበቁት ተጨማሪ አዲስ መሶብ ቅርንጫፎች የምረቃ ሥነ ስርዓት ላይ የተገኙት ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አረጋግጠዋል፡፡ በበጀት ዓመቱ ከተያዙ 11 ቅርንጫፎች መካከል የልደታ፣ ቂርቆስ፣ አዲስ ከተማ እና የጉለሌ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፎች ተመርቀው ከሰሞኑ ለአገልግሎት በቅተዋል፡፡ በዚህም በተበታተነና በተንዛዛ መልኩ ይሰጡ


ፎቶ- ከፋይል
5ኛው የአዲስ መሶብ አዲስ ከተማ ቅርንጫፍ የምረቃ ሥነ ስርዓት

የነበሩ የመንግስት አገልግሎቶችን በማዘመን፣ በተቀናጀ አግባብ በአንድ ማዕከል እንዲሰጡ ማድረግ ተችሏል። በውስጣቸውም፡- ምቹ የተገልጋዮች ማረፊያ፣ ቤተ-መጻሕፍት፣ የሕፃናት ማቆያ እና ካፌቴሪያዎችን አካትተዋል።

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች እነዚህን የአዲስ መሶብ ቅርንጫፎች፣ በተለይም 5ኛውን የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት አዲስ ከተማ ቅርንጫፍ አገልግሎት ሲያስጀምሩ ባስተላለፉት መልዕክት፤ የምረቃ ሥነ ስርዓቱ በሀገራዊ ለውጡ ስምንተኛ ዓመት ዋዜማ ላይ በመከናወኑ ልዩ እንደሚያደርገው ጠቅሰዋል፡፡ "አዲስ አበባ አሁን የደረሰችበት ሁለንተናዊ ለውጥና ዕድገት፣ በለውጡ መንግሥት ቁርጠኝነት የተመዘገቡ የመጋቢት 24 ውጤቶች ናቸው። ከኢትዮጵያ መዲናነት ተሻግራ የአፍሪካ ኩራት የሆነችውን አዲስ አበባን በተግባርም እንደ ስሟ ውብ ለማድረግ፣ የለውጡ መንግሥት ገቢር ያደረጋቸው የልማት ሥራዎች ታሪካዊና ዘመን ተሻጋሪ ስኬትን አስመዝግበዋል" በማለት በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) መሪነት እየተከናወነ ያለው ዘርፈ ብዙ የልማት እንቅስቃሴ ለመዲናዋ ትርጉሙ የላቀ መሆኑን አንስተዋል፡፡

ከንቲባ አዳነች አያይዘውም፤ "ከለውጡ መንግሥት ስኬቶች መካከል አንዱ የ'አዲስ መሶብ' ዲጂታል የአንድ ማዕከል አገልግሎት ነው። የመንግሥት ሥርዓታት በተለዋወጡ ቁጥር ቃል እየተገባ ለመለወጥ ጥረት ቢደረግም፣ ሳይለወጥ ቆይቶ ተገልጋዩን ሲያማርር የኖረውን፣ ስር የሰደደና በተንዛዛ ቢሮክራሲ የተተበተበውን አሰራር ከመሠረቱ የሚቀይር ነው። ጊዜ፣ ወጪና ጉልበት የሚባክንበትን እንዲሁም ጥራትና ቅልጥፍና የራቀውን አገልግሎት አሰጣጥ በተግባር በመለወጥ አዲስ ምዕራፍ መክፈት ተችሏል። 'ማገልገል ክብር ነው' በሚል መርህ በንጹህ የአገልግሎት መስጫ ቦታዎች፣ በንጹህ አዕምሮ እና በንጹህ እጅ ማገልገልን ይዞ መጥቷል" ብለዋል በመልዕክታቸው፡፡

የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል አገልግሎት ቅርንጫፎች በታለመላቸው ጊዜ ተጠናቅቀው ለአገልግሎት እንዲበቁ ድጋፍ ላደረጉ አካላት ምስጋና ያቀረቡት ከንቲባ አዳነች፤ እንደ ከተማ አስተዳደር ለአገልግሎት በመብቃት 5ኛው የሆነው የአዲስ ከተማ የአዲስ መሶብ ማዕከል መገኛው፣ መርካቶን ጨምሮ ሰፊ የንግዱ ማህበረሰብ የሚንቀሳቀስበት አካባቢ በመሆኑ፣ ቀልጣፋና ፈጣን አገልግሎት በመስጠት ረገድ ትልቅ እፎይታን ይፈጥራል፡፡ እየተስፋፋ ያለው የዲጂታል የመንግሥት አገልግሎት መስጫ ማዕከል፣ ከከተማዋ ነዋሪዎች ባሻገር ለዲፕሎማቶች፣ ለቱሪስቶችና ለኮንፈረንስ ተሳታፊዎች ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ፈጣን አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችል መሆኑንም በመልዕክታቸው አንስተዋል፡፡

የአዲስ መሶብ መስፋፋት የመንግሥት አገልግሎትን በማላቅ፤ ደላላን፣ ሌብነትን፣ አድሎ እና እንግልትን በማስወገድ፣ ተደራሽነትን እና የዜጎችን እርካታ በማሳደግ፣ በተቋማት መካከል የነበረውን የተበታተነ አገልግሎት በማቀናጀት እንዲሁም ኅብረተሰቡ አገልግሎት ለማግኘት የሚያጠፋውን ጊዜና ወጪ በከፍተኛ ሁኔታ በመቀነስ ፍትሐዊ አገልግሎት ያሰፍናል፡፡ ማዕከላቱ የመንግሥት አገልግሎት አፈጻጸም ቁልፍ የክዋኔ መለኪያ እና አጠቃላይ የዜጎች እርካታን እያመጡ፣ አካታች እና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ማጎልበቻ ስርአት እየሆኑ ነው። ለተገልጋዩ ማህበረሰብ የተመቹ፤ በተለይም አረጋውያን እና አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረጉ፣ እንዲሁም ለሠራተኞች ምቹ የሥራ አካባቢን የፈጠሩ መሆናቸውን የልደታ እና ቂርቆስ ቅርንጫፎችን ባስመረቁበት ወቅት መግለፃቸው ይታወሳል፡፡ በኮሪደር ልማት የተዘረጉ መሠረተ ልማቶች ለተቀናጀ ዘመናዊ የዲጂታል አገልግሎት ወሳኝ ሚና እያበረከቱ እንደሆነም አብራርተዋል።

አዲስ መሶብ የሚሰጠውን የተቀናጀ ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን፣ አሁን ካለበት ደረጃም ለማሻሻል ቁልፍ ከሆኑ ግብዓቶች መካከል፡- ደረጃውን የጠበቀ የመሰረተ ልማት ግንባታ አንዱ ነው። በዚህ ረገድ ባለፉት ጥቂት ዓመታት የተሠሩ እና እየተሠሩ ያሉ ግዙፍ ሥራዎች መሰረታዊ ለውጥ አምጥተዋል። ለዚህም የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የአመራር ብቃት ጎልቶ ይነሳል። አብነት የብሔራዊ ዳታ ማዕከል መገንባት፣ የቴሌኮም ዘርፉን ለውጭ ውድድር ክፍት ማድረግ እና የ"ፋይዳ" ብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያን በልዩ ትኩረት ማስጀመራቸው ለአገልግሎቱ ተዓማኒነትና ደህንነት ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል። በተጨማሪም የአዲስ አበባው የአዲስ መሶብ ተሞክሮ ወደ ክልል ከተሞች እንዲሸጋገርና በሀገር አቀፍ ደረጃ ተመሳሳይ የተቀናጁ ማዕከላት እንዲቋቋሙ መመሪያ በመስጠት የዲጂታል ፍትሃዊነትን እያረጋገጡ ይገኛሉ።

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# ከሸማችነት ወደ አምራችነት የተሸጋገሩ ከተሜዎች

- **በአዲስ አበባ ከተማ በቤተሰብ ደረጃ የሚከወን የዶሮ እርባታ ሥራ 20 ሺህ ነዋሪዎችን በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ ተጠቃሚ ስለማድረጉ ተጠቁሟል።**

**በይግለጡ ጓዴ**

በቤተሰብ ደረጃ የሚሠራ የከተማ ግብርና ሥራ በጠንካራ ሥነ-ሥርዓት ከተመራ፣ ለትውልድ የሚሻገር ጠንካራ ሀብትና የቤተሰብ አንድነትን የሚፈጥር ወሳኝ የኢኮኖሚ መስክ ነው። በተለይ በአሁኑ ወቅት በሀገራችን እየታየ ያለውን የኑሮ ውድነት ለመቋቋም፣ ለቤተሰብ አባላት የሥራ ዕድል ከመፍጠር ባለፈ የጋራ ራዕይን ለማሳካት ትልቅ ሚና ያለው መሆኑ ይታወቃል። ይህ ዘርፍ የቤተሰብ አባላት በመመሪያ እና በእቅድ የሚመሩበት፣ የገቢና የወጪ የሂሳብ አያያዝን በተገቢው መንገድ በመተግበር ውጤታማ የሚሆኑበት መድረክ ነው።

በዶሮ እርባታ ዘርፍ የቤተሰብ ቢዝነስ መጀመር በአነስተኛ ቦታና በዝቅተኛ ካፒታል የሚከናወን በመሆኑ፣ ለብዙዎች አዋጭ እና የቤተሰብን የጋራ ገቢ የሚያሳድግ የሥራ ዘርፍ ሆኖ ተገኝቷል። አቶ ለማ ስሜ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የወረዳ 14 ነዋሪ ሲሆኑ፣ በዚህ የቤተሰብ ቢዝነስ ሞዴል ተደራጅተው በዶሮ እርባታ ውጤታማ ከሆኑ አርአያ ዜጎች አንዱ ናቸው። በ2018 ዓ.ም መስከረም ወር ላይ የጀመሩት ይህ ሥራ፣ በመንግስት በኩል በተደረገላቸው የ50 የዶሮ ጫጩቶች፣ የዶሮ ኬጅ እና ለሦስት ወር የሚያገለግል መኖ ድጋፍ ወደ ተግባር ተተርጉሞ ውጤታማም ሆነዋል።

አቶ ለማ ከባለቤታቸውና ከልጃቸው ጋር በመሆን በጋራ በመደራጀታቸው፣ ሥራው የቤተሰብ አባላትን የሥራ ስሜት ከማነቃቃቱም በላይ ኃላፊነትን የመጋራት ባህልን አዳብሯል። በሦስት ወራት ውስጥ ብቻ እንቁላል ወደ ገበያ ማቅረብ በመቻላቸው፣ በኢኮኖሚ ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ተጠቃሚ ማድረግ መቻላቸውን በኩራት ይናገራሉ። ይህ የሚያሳየው የቤተሰብ ቢዝነስ በትንሽ ግብዓት ተጀምሮ ፈጣን ለውጥ ማምጣት የሚችል መሆኑን ነው።

ይሁን እንጂ ሥራው ያለ ተግዳሮት አልነበረም፤ አቶ ለማ እንደሚጠቁሙት የመኖ ዋጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ መጨመር በሥራቸው ላይ ጫና ቢያሳድርባቸውም፣ በቤተሰብ ደረጃ የሚሠራ የዶሮ እርባታ ሥራ የራሳቸውን እና የቤተሰባቸውን ሕይወት መቀየሩን ይገልጻሉ። በአሁኑ ወቅት በቀን በአማካይ 25 እንቁላል በማግኘት ወደ ገበያ ያቀርባሉ። የወረዳ የከተማ ግብርና ባለሙያዎች የሚሰጡት ሙያዊና የሕክምና ድጋፍ ለሥራው ስኬት ትልቅ አቅም እንደሆናቸውም አክለው ገልጸዋል።

አቶ ለማ በቀጣይም ያላቸውን ክፍት ቦታ በመጠቀም ከኢትዮጵያ

“ባለፉት ዘጠኝ ወራት ውስጥ 4 ሺህ 101 አባወራዎችና እማወራዎች በቤተሰብ ደረጃ ወደሚሰራ የዶሮ እርባታ ሥራ ገብተዋል፤ ከቀደሙት ጊዜያት ጀምሮ በዚህ ሥራ የተሰማሩ ነዋሪዎች ምርታማነታቸውን በማሳደግ አሁን 600 ዶሮዎች አሏቸው”

ንግድ ባንክ ብድር በመውሰድ የዶሮ እርባታ ሥራቸውን ይበልጥ ለማስፋፋት አቅደዋል። መንግስት ያደረገላቸው ድጋፍ በሥራቸው እንዳነሳሳቸውና የሞራል ስንቅ እንደሆናቸው የሚናገሩት አቶ ለማ፣ በቤተሰብ ደረጃ የሚከወን የከተማ ግብርና ገበያን ለማረጋጋትና ራስን ለመቻል ወሳኝ የኢኮኖሚ አማራጭ መሆኑን ያስገነዝባሉ።

በተመሳሳይ ሁኔታ ወይዘሮ ተዋበች ባዩ በዚሁ ዘርፍ ተሰማርተው ውጤታማ የሆኑ ሌላኛዋ ጠንካራ እናት ናቸው። ባለቤታቸውንና ልጃቸውን በመያዝ ወደ ሥራ የገቡት ወይዘሮ ተዋበች፣ ቀደም ሲል እንቁላል ማግኘት ለቤተሰባቸው ትልቅ ችግር እንደነበር ያስታውሳሉ። እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ እንቁላልን



ፎቶ- በገነት ወንድሙ

አቶ ለማ ስሜ ዶሮዎችን ሲንከባከቡ

በበዓል ወቅት ብቻ የሚመገቡበት ጊዜ አልፎ፣ ዛሬ ግን ከራሳቸው ፍጆታ አልፎ ለገበያ የሚያቀርቡ ባለቤት መሆን ችለዋል።

ወይዘሮ ተዋበች የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ያደረገላቸው የሥራ ማስጀመሪያ ድጋፍ የቤት እመቤት ለነበሩት እሳቸው ትልቅ የሥራ ዕድል መፍጠሩን ይናገራሉ። በአሁኑ ወቅት እንቁላልን በ16 ብር ሒሳብ ለገበያ በማቅረብ ላይ ይገኛሉ። የቤት ውስጥ ሥራ ብቻ በመሥራት ተወስነው የነበሩት እኚህ እናት፣ አሁን ግን የቤተሰብን ኢኮኖሚ የሚደግፍ የዶሮ እርባታ ሥራን ጎን ለጎን እያከናወኑ ይገኛሉ።

የወይዘሮ ተዋበች ልጅ የሆነው ወጣት ምህረተአብ ሽመልስ፣ በቤተሰብ ደረጃ በሚሠራ የከተማ ግብርና ሥራ ተደራጅቶ መሥራቱ የተለየ የሥራ ስሜት እንደፈጠረለት ይገልጻል። በአካባቢያቸው ለሚገኙ ሱቆች በተመጣጣኝ ዋጋ እንቁላል በማቅረብ ላይ መሆናቸውንና ይህም ለቤተሰቡ ብቻ ሳይሆን ለማህበረሰቡም ትልቅ እፎይታ መሆኑን ጠቁሟል። መንግስት ምንም ገቢ የሌላቸውን ዜጎች ደግፎ ወደ ሥራ ማስገባት መቻሉ ይበል የሚያሰኝ ተግባር መሆኑንም ወጣቱ ይመሰክራል።

ሌላኛዋ ተጠቃሚ ወይዘሮ ሀረገወይን ነጋ፣ በዶሮ እርባታ ብቻ ሳይገደቡ በወተት ላሞች በተቀናጀ የከተማ ግብርና ዘርፍ ተጠቃሚ መሆን የቻሉ እናት ናቸው። የመሥሪያ ቦታ እጥረትና የመኖ ዋጋ መናር እንቅፋት ቢሆኑባቸውም፣ በቀን እስከ 34 እንቁላል በማግኘት ራሳቸውን መደጎም ችለዋል። ይህም የከተማ ግብርና በተወሰነ ቦታ ላይ ተቀናጅቶ ሊሠራ እንደሚችል ማሳያ ነው።

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የወረዳ 14 የከተማ ግብርና ልማት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ አቤ ሂኔ እንደሚሉት፣ በወረዳው በዶሮ እርባታ፣ በአትክልት፣ በከብት ማድለብና በንብ እርባታ የተሰማሩ በርካታ ግለሰቦች አሉ። በቤተሰብ ደረጃ የሚሠራ የከተማ ግብርና በከተማዋ ያለውን የኑሮ ውድነት ለመቀነስና “በከተማ ግብርና አይቻልም” የሚለውን የተሳሳተ አመለካከት በተግባር ለመቀየር ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክቷል።

የመንግስት ድጋፍ ከቁሳቁስ ባለፈ የገበያ ትስስርን ያካትታል። ነዋሪዎች ያመረቱትን እንቁላል በእሁድ ገበያና በባዛሮች ላይ እንዲያቀርቡ በማድረግ የገቢ ምንጫቸው እንዲያድግ ተደርጓል። ይህ ደግሞ አምራቹ ተገቢውን ዋጋ እንዲያገኝና ሸማቹም ትኩስ ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲሸምት ዕድል ፈጥሯል።

በቂርቆስ ክፍለ ከተማም ተመሳሳይ ስኬቶች እየተመዘገቡ ይገኛሉ። ፓስተር ሙሉጌታ ስዩም ከቤተሰባቸው ጋር ተደራጅተው በዶሮ እርባታና በጓሮ አትክልት ሥራ ተሰማርተዋል። ይህ ሥራ፣ ራስን በኢኮኖሚ ከመደጎም ባለፈ ለሌሎች ተርፎ ማህበረሰብን የማገልገል ዕድል እንደፈጠረላቸው ይገልጻሉ።

በቂርቆስ ክፍለ ከተማ የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ጽሕፈት ቤት አስተባባሪ ወይዘሮ ተሰም ገብረህይወት፣ በክፍለ ከተማው 273 የዶሮ እርባታ ሥራ ተጠቃሚዎች መኖራቸውን ጠቁመዋል። በእያንዳንዱ ዙር ለቤተሰቦች የሚሰጠው የ50 ዶሮዎች ድጋፍ፣ ነዋሪዎች የቤተሰባቸውን ፍጆታ እንዲሸፍኑና ኢኮኖሚያቸውን እንዲያሳድጉ ትልቅ ድርሻ አበርክቷል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የእንስሳት ሀብት ልማት ዳይሬክተር ዶክተር ደጀኔ ጌታቸው በሰጡት ገለጻ፣ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ውስጥ 4 ሺህ 101 አባወራዎችና እማወራዎች በቤተሰብ ደረጃ ወደሚሠራ የከተማ ግብርና ሥራ ገብተዋል። ይህም በአጠቃላይ ወደ 20 ሺህ የሚጠጉ ነዋሪዎችን በቀጥታና በተዘዋዋሪ ተሳታፊ አድርጓል። ዳይሬክተሩ እንደሚሉት፣ ይህ ሂደት ሥራ አጥ ዜጎች ራሳቸውን የሚችሉበትና የሥራ ዕድል የሚፈጠርበት ትልቅ መድረክ ነው።

አብዛኞቹ በቤተሰብ ደረጃ በሚሠራ የከተማ ግብርና ሥራ የተሰማሩ ነዋሪዎች ምርታማነታቸውን በማሳደግ ከ50 ዶሮዎች ተነስተው እስከ 600 ዶሮዎች የሚደርሱ ኬጆችን አሠርተው ሥራቸውን ማስፋፋት መቻላቸው የሚበረታታ ነው። ይህም የከተማ ግብርናን ወደ ከፍተኛ ቢዝነስ የመቀየር አቅም እንዳለው ያረጋግጣል። የዘርፉ እድገት የከተማዋን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥና የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋት ወሳኝ ሚና እየተጫወተ ይገኛል።

በቤተሰብ ደረጃ የሚከናወን የከተማ ግብርና መተግበሩ ተረጅነትን ከመቀነስ ባለፈ፣ የቤተሰብ አንድነትንና የሥራ ባህልን ለማሳደግ ታላቅ ድል ሆኖ ተመዝግቧል። መንግስት የሚያደርገው የቁሳቁስና የሙያ ድጋፍ ተጠናክሮ ከቀጠለ፣ እንዲሁም የመኖና የቦታ ችግሮች ዘላቂ መፍትሔ ካገኙ፣ ይህ የሥራ ዘርፍ ለሀገራዊ ብልጽግና ትልቅ መሠረት እንደሚሆን ጥርጥር የለውም።

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# የመዲናዋን አየር ጥራት ለመጠበቅ ምን እየተሠራ ነው?

- የብናኝ ብክለት መከላከያ መመሪያ ረቂቅ ተዘጋጅቶ ለመጽደቅ በሂደት ላይ እንደሚገኝ ተጠቁሟል



ፎቶ- ከፋይል

የአየር ብክለትን ለመከላከል የወንዝ ዳርቻ ልማትን ጨምሮ ከአካባቢው ጋር የተስማማ ልማት እየተከናወነ ነው

**በለይላ መሀመድ**

የአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ትኩረት አድርጎ ከሚሰራቸው ተግባራት መካከል የአየር ጥራት መጠንን መለካት አንዱ ነው፡፡ ለመሆኑ የአየር ጥራት ማለት ምንድ ነው? መለኪያውስ? አየር ተበክሏል የሚባለውስ ምን ሲሆን ነው? ባለስልጣኑስ በዚህ ዙሪያ ምን እየሰራ ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች እንደሚከተለው ዳስሰነዋል፡፡

አቶ ሰለሞን መለሰ በባለስልጣኑ የአየር ንብረት ለውጥ፣ አማራጭ ኢነርጂ ዳይሬክቶሬት፣ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልኬት ቅነሳ፣ አረንጓዴ ቴክኖሎጂ ማስፋፊያና የአየር ጥራት ክትትል ቡድን መሪ ናቸው፡፡ እሳቸው እንደሚገልጹት፤ የአየር ጥራት ሲባል ከቤት ውጭ በሚገኝ በአንድ በተወሰነ ቦታ ያለውን የአየር ጥራት ውጤት በጥራት መለኪያ መሣሪያ በመለካት የሚገኝ ነው፡፡ የተገኘው ውጤት ከተቀመጠው ስታንዳርድ (ደረጃ) አንጻር ከፍተኛ ነው ዝቅተኛ የሚለውን ይለያል። ውጤቱ ከስታንዳርዱ በላይ ከሆነ አካባቢው የተበከለ አየር የሚታይበትና ችግር ውስጥ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህም በዚያ ከባቢ አየር ላይ በካይ ጋዞች መኖራቸውን ያመለክታል፡፡ ምን ዓይነት በካይ ጋዞች እንዳሉ የሚታወቀው ደግሞ እንደተተከለው መለኪያ መሣሪያ ዓይነት ይወሰናል፡፡

በአዲስ አበባ አሁን ላይ በብዛት የተተከሉት መሣሪያዎች ብናኝን (Particulate Matter/PM2.5) የሚለኩ ናቸው፡፡ ይህም ጋዝ ሆኖ በብናኝ መልክ የሚታየውን የሚለካ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- በመኪና ጪስ ውስጥ ብናኝ ይታያል። በተጨማሪም ናይትሮጂን ኦክሳይድና ሰልፈር ዳይኦክሳይድ ሊወጡ ስለሚችሉ፣ እነዚህን መለካት የሚችል ሌላ ዓይነት መሣሪያ ያስፈልጋል፡፡

## አየር ሲበከል የሚያሳየው ምልክት ምንድ ነው?

ቡድን መሪው እንደሚያስረዱት፤ አየሩ በበካይ ጋዝ ተበክሏል ሲባል በሦስት መልኩ ሊታይ ይችላል፡፡ አንደኛው በበካይ ጋዝ ሳቢያ በሚመጡ በሽታዎች የሚያዙ ሰዎች ቁጥር በየጊዜው መጨመር ነው፡፡ ከመተንፈሻ አካላት ጋር ተያይዘው የሚመጡ እንደ ሳንባና ብሮንካይት ያሉ የሕመም ዓይነቶች እንዲሁም ያለ ዕድሜአቸው የሚሞቱ ሰዎች ቁጥር እያደገ መምጣቱን የጤና ተቋማት በሚያሳዩት መረጃዎች መረዳት ሲቻል ነው ፡፡ ሁለተኛው በተተከሉት የአየር ጥራት መለኪያ መሣሪያዎች የሚታይ ንባብ ነው፡፡ በተከታታይ ቀናት ንባብ የበካይ ጋዝ መጠን በዝቶ ሲታይ ብክለት መኖሩን ያመላክታል፡፡ ሦስተኛው ብክለቱ በጣም እያደገ ሲሄድ አየሩ በጉም ተሸፍኖ ይታያል፡፡ ቻይናና ሕንድ በከተማቸው እንዲህ ዓይነት ችግር ስለሚከሰት ነዋሪዎች የፊት መሸፈኛ ጭምብል (ማስክ) አድርገው ሲንቀሳቀሱ ይታያሉ። በተለምዶ በእኛ ሀገር ጉም የሚታየው በክረምት ወቅት ነው፡፡ አሁን ላይ ግን በበጋ ወቅትም አዲስ አበባ ውስጥ ጠዋት ላይ አየሩ ጉም መስሎ ይታያል፡፡ ከረፋዱ 4 ሰዓት በኋላ ይጠራል፡፡ ይህ በአካባቢው አየሩ የመበከሉን እድገት ያሳያል፡፡

አየር ተበክሏል ወይንም አልተበከለም የሚለውን ለመለየት በኢፌዲሪ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ያወጣው ስታንዳርድ አለ፡፡ ስታንዳርዱ ላይ የተቀመጠውን መስፈርት በተተከሉት መሣሪያዎች የተገኘውን በማንበብ ንጽጽር ይደረጋል። አዲስ አበባ የአየር ጥራት ልኬት የሚካሄደው "PM25" የተባለውን የብናኝ አይነት ነው፡፡ በተከታታይ ቀናት የ24 ሰዓት ንባብ ከ65 ማይክሮ ግራም (ug/m3) በላይ ከሆነ አካባቢው እየተበከለ መሆኑን ያሳያል፡፡ በተከታታይ ቀናት (ፓሪቲኩሌት ማተር/PM25) የብናኝ መጠን ከ65 ማይክሮ ግራም (ug/m3) በታች ከሆነ ብክለቱ አነስተኛና በጤና ላይ የሚያመጣው ተጽዕኖ ዝቅተኛ ነው። አካባቢው በዓመት ከተቀመጠው ስታንዳርድ አማካኝ ንባብ 15 ማይክሮ ግራም (15 ug/m3) መሆን አለበት፡፡ በአማካይ የየቀኑ ተደምሮ የሚገኝ ነው፡፡

የዓለም ጤና ድርጅት ያስቀመጠው ስታንዳርድ የቀን የብናኝ መጠን (15 ug/m3) ወይም 15 ማይክሮ ግራም ፐር ሜትር ኩዩብ ሲሆን፤ የዓመቱ ደግሞ 5 ማይክሮ ግራም ፐር ሜትር ኩዩብ (5 ug/m3) ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ወደዚህ ደረጃ ለመምጣት ብዙ ስራ እንደሚጠበቅ አቶ ሰለሞን ይናገራሉ፡፡

አዲስ አበባ የኢትዮጵያውያን ብቻ ሳትሆን የአፍሪካ ዋና ከተማ፣ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የሚገኙባት፣ በርካታ ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች የሚካሄድባት እንደመሆኗ የከተማዋን የአየር ጥራት የዓለም ጤና ድርጅት ወዳስቀመጠው ስታንዳርድ ለማስገባት እየተሰራ ነው፡፡ አሁን ላይ በከተማዋ የሚሰሩ የአረንጓዴ ሽፋንን የማሳደግና ከአካባቢ ጋር የተጣጣሙ ልማቶች የአየር ጥራትን ለማሻሻል የሚያስችሉ ናቸው፡፡ የልማት እንቅስቃሴዎችን የከተማዋን ፕላን በጠበቀ መልኩ መሥራት የአየር ብክለት ችግርን ያስቀራል፡፡ የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂን በመከተል በወንዝና ወንዝ ዳርቻ ልማት ሥራዎችን የማከናወን፣ ደረቅ ቆሻሻ ከማቃጠል የመቆጠብ፣ የሀይል ቆጣቢ እንዲሁም የኤሌክትሪክ ምድጃዎችን በመጠቀም ቤት ውስጥ የሚቃጠሉ ነገሮችን የማስቀረት፣ እንዲሁም የኤሌክትሪክ መኪናዎች የአየር ብክለት እንዲቀንስና ጥራቱ እንዲጠበቅ አስተዋፅኦ እንደሚኖራቸው ቡድን መሪው ገልጸዋል፡፡

## የአየር ጥራትን ለመጠበቅ ምን እየተሠራ ነው?

የቡድን መሪው አቶ ሰለሞን እንደሚገልፁት፣ የአየር ብክለትን ከመከላከል አኳያ ወደ ልማት የሚገባ ባለሀብትም ይሁን አገልግሎት ሰጪ ተቋም የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ማካሄድ እንዳለበት በህግ ተደንግጓል። ድርጅቶች የሚሰማሩበት ሥራ ከአየር ብክለት አንጻር የሚያስከትለው አሉታዊ ተፅዕኖ ካለ በፕሮጀክት ሰነዳቸው ውስጥ በማሳየት የአየሩ ብክለት መከላከያ ወይም መቀነሻ ዘዴዎችን ማስቀመጣቸው ሲረጋገጥ ይሁንታ ይሰጣቸዋል፡፡ ፕሮጀክቱ ወደ ሥራ ሲገባ በሰነዱ መሠረት አካባቢ ላይ ጉዳት በማያስከትል መልኩ እየሠራ ስለመሆኑ ክትትል ይደረጋል። ከዚህ ቀደም በንግድ ፍቃድ ብቻ ወደ ሥራ የገቡ የኢንዱስትሪና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የአካባቢ አስተዳደር ፕላን እንዲያዘጋጁ በማድረግ የአካባቢ አየር ብክለት እንዳያስከትሉ ግምገማ ይደረጋል፡፡

ተቋማቱ ከዘፈቀዳዊ አሰራር ወጥተው የሚፈጥሩትን ብክለት እንዲከላከሉ የሚያስችላቸውን አሰራር እንዲዘረጉ ይደረጋል፡፡ ይህንንም ለመቆጣጠርና ለመከታተል የሚያግዝ ከእነዚህ ደንቦች በተጨማሪ የብናኝ ብክለት መከላከያ መመሪያ ረቂቅ በአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ተዘጋጅቶ ለማጸደቅ በሂደት ላይ እንደሚገኝ አቶ ሰለሞን ያነሳሉ፡፡ ተሽከርካሪዎች የሚለቁትን የመኪና ጭስ ወይም ብናኝ ለመቆጣጠር የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ከዚህ ቀደም ያጸደቀውን መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ እየተሠራ ነው፡፡ የተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ምርመራ (ቦሎ) የሚያደርጉ ተቋማት ላይ ጥብቅ ቁጥጥር በማድረግ መመሪያው ስለመተግበሩ ይሰራል፡፡ ከዚህ አንጻር በበጀት ዓመቱ የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ ጋር በመሆን በመንገድ በሚንቀሳቀሱ መኪናዎች ላይ ድንገተኛ ፍተሻ ተደርጓል። በተደረገው ድንገተኛ ፍተሻም በቸልታ የታለፉ መኖራቸውን ለማወቅ ችለዋል፡፡ በቀጣይ ግን ባለስልጣኑ በራሱ ድንገተኛ ፍተሻ አከናውኖ ህጉን ተግባራዊ በማድረግ የቁጥጥር ሥራውን አጠናክሮ ለመሥራት አቅዷል፡፡

እንደ ቡድን መሪው ማብራሪያ፣ በተያዘው በጀት ዓመት በትራንስፖርት እና ሎጂስቲክ ሚኒስቴር በተዘጋጀው መመሪያ መሰረት በአዲስ አበባ 200 ተሽከርካሪዎች ላይ ፍተሻ የተደረገ ሲሆን፤ የፍተሻውን ግኝት የሚገልጽ ሪፖርት እየተዘጋጀ ነው። የቡድን መሪው አያይዘው እንደገለጹት፤ በአዲስ አበባ የአየር ጥራት ልኬት መሣሪያ በመትከል ክትትል ማድረግ ከተጀመረ 7 ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ መጀመሪያ ላይ በየአካባቢው ያለውን የአየር ሁኔታ ለማወቅ ለናሙና ከአንድ ቦታ ላይ ነበር መረጃው የሚወሰደው። በሂደት ግን መለኪያ መሳሪያዎች እየተቀየሩ ከመምጣታቸውም በተጨማሪ የትምህርት ተቋማት፣ የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ እና ሌሎችም እየተከሉ ይገኛሉ፡፡

የብናኝ መጠን ከፍተኛ የሚሆንባቸው ኢንዱስትሪዎች የሚበዙባቸው፣ እንደ ጥቁር አንበሳ አካባቢ፣ እስካይላይት ሆቴል ያሉ የትራንስፖርት መጨናነቅ ያለባቸው ቦታዎች፣ የአዲስ አበባ ከተማ ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ (ረጲ/ቆሼ)፣ ጀነሬተር በብዛት ጥቅም ላይ የሚውልባቸው እንዲሁም የመንገድ መሠረተ ልማት በሚሰራባቸው አካባቢዎች ብናኝ የመከላከል ስራ ካልተሰራ በከፍተኛ ደረጃ ሊታይ ይችላል፡፡ የአየር ጥራት መጠን የሚወሰነው አካባቢው እንዳለው እንቅስቃሴ ነው፡፡

የአየር ጥራት መለኪያ መሳሪያው የሚያነብበው በየ10 ደቂቃው ቢሆንም ባለስልጣኑ የየቀኑን እና አማካይ ንባብ በመውሰድ በወር ይፋ ያደርጋል፡፡ እስካሁንም በባለስልጣኑ 10 መሣሪያዎች የተገዙ ሲሆን 9ኙ ተተክለዋል። አንደኛው የቴክኒክ ችግር ስላለበት የመቀየር ሥራ ይሠራል፡፡ በቀጣይ ወራት "c40" በተባለ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ድጋፍ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ ጋር በመሆን የ15 መሣሪያዎች ተከላ ይካሄዳል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የትራንስፖርት ቢሮም 15 የብናኝ ብክለት ለመከታተል የሚያስችሉ መሣሪያዎችን መንገድን ተከትሎ የትራንስፖርት መጨናነቅ ያሉባቸው ቦታዎች ላይ በቀጣይ ቀናት ለመትከል ሥራ ላይ ነው፡፡ የእነዚህ መሣሪያዎች በከተማዋ በተለያዩ ቦታዎች መኖር የአየር ጥራት ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ስለሚያሳይ መወሰድ ያለበትን የመፍትሄ እርምጃ ለማምጣት እንደሚያግዝ አቶ ሰለሞን አስረድተዋል፡፡

## የአዲስ ... ከገጽ 6 የዞረ

የቤቶችን ለአብነት አነሳን እንጂ ቀንና ሌሊት በመስራት በፍጥነትና በጥራት በርካታ ፕሮጀክቶች ተገንብተው እየተጠናቀቁ ይገኛሉ፡፡ አዲስ አበባ በቀን ብቻ ሳይሆን በሌሊት የሥራ እንቅስቃሴዎች የሚከናወኑባት፣ በርካታ ወጣቶች በሥራ ዕድል ፈጠራ ተጠቃሚ የሚሆኑባት፣ በየጊዜው ፕሮጀክቶች የሚመረቁባት፣ የተነቃቃች፣ የሥራ፣ የመኖሪያና የመዝናኛ ከተማ ሆናለች፡፡ በቅርብ ዓመታት ያለውን ብናነሳ እንኳን በ2017 በጀት ዓመት ብቻ በአዲስ አበባ ከተማ በመንግስትና ኅብረተሰብ ተሳትፎ ከ19 ሺህ በላይ ፕሮጀክቶች ተጠናቅቀው ለአገልግሎት በቅተዋል፡፡ በ2018 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ ዓመትም 12 ሺህ በላይ ኘሮጀክቶችን ማከናወን እንደተቻለ የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ከወራት በፊት ለአዲስ አበባ ምክር ቤት ካቀረቡት ሪፖርት መረዳት ይቻላል፡፡

ጠንካራ የሥራ ባህል መኖሩ በጊዜ ርዝመት ምክንያት የሚፈጠሩ የፕሮጀክትና የአገልግሎት መጓተቶችን በማስቀረትና በዚህ ምክንያት ያስከትል የነበረውን የዋጋ ንረት በመቀነስ ለከተማዋ እድገት ትልቅ አስተዋፅኦ እያበረከተ ይገኛል፡፡ የልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ህንጻ ከአንድ ዓመት በፊት ተገንብቶ ለአገልግሎት በበቃበት ወቅት የአዲስ አበባ ከንቲባ ወ/ሮ አዳነች ባደረጉት ንግግር፤ “በከተማችን ውስጥ ተጀምረው የማያልቁ ፕሮጀክቶች ተፈልገው እስከማይገኙ ድረስ፣ ድሮ ተጀምረው የተረሱትን ሳይቀር እያፈላለግን እየጨረስን፣ አዳዲሶችን በፍጥነት ጀምረን በፍጥነት እየጨረስን ነው፡፡ ይህም የሥራ ባህልን እያዳበረ፣ ወጪን እየቀነሰ፣ ለህዝብ ልማት መዋል የሚገባውን በጀት መቆጠብ እያስቻለ ነው” ብለዋል፡፡

ከንቲባዋ ከአንድ ወር በፊትም በካዛንቺስ እየተገነባ ያለውን የህፃናት ዓለም ማዕከልና በቦሌ መድኃኒዓለም አካባቢ የሚገነቡ የኮሪደር ልማት አገናኝ መስመሮችን የምሽት የሥራ እንቅስቃሴ ተዘዋውረው በጎበኙበት ወቅት፤ የከተማ አስተዳደሩ ከፍተኛ አመራሮች በምሽት ሥራዎች በሚከናወኑበት ስፍራ ተገኝቶ ያሉበት ደረጃን በመመልከት የመደገፍ፣ ውሳኔ የመስጠት፣ ከፍጥነትና ጥራት አኳያ ችግሮች ካሉም ወዲያውኑ እንዲስተካከሉ በማድረግ በተቀመጠላቸው ጊዜ እንዲጠናቀቁ እየተደረጉ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ለኢዜአ በሰጡት ማብራሪያ፤ የኮሪደር ልማት እሳቤ በአዲስ አበባና ሌሎች የሀገሪቱ ከተሞች ተስፋ ሰጪ ለውጦችን ማምጣቱን በመጥቀስ፣ “አመራሩ ከቢሮ ወጥቶ በየመንገዱ ያሉ ችግሮችን እያየና እየፈታ የመሄድ ልምምድ መጀመራችን ከተሞቻችን የሚገባቸውን መልክ እንዲይዙ በእጅጉ እያገዘ ነው፡፡” ሲሉ እየተደረገ ያለው ክትትልና ድጋፍ ያስገኘውን አበርክቶውን አብራርተዋል፡፡

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች በማህበራዊ የትስስር ገጻቸው ሰሞኑን ባስተላለፉት መልዕክት፣ “ከተማችን እየተገበረች ባለችው ሁለንተናዊ ልማት ለሁሉም የምትመች፣ ሁሉንም በፍትሐዊነት የምታገለግል፣ ማንንም ያልዘነጋች የአካታች ልማት ማሳያ ከተማ እያደረግናት ነው። ለሕፃናት፣ ለወጣቶች፣ ለአረጋውያንና ለአካል ጉዳተኞች፣ ለእግረኛው፣ ለባለ መኪናውና ለባለ ሳይክሉ የትራንስፖርት አማራጮችንና መሠረተ-ልማቶችን በፍትሐዊነት ያመቻቸች፤ ለስማርት ከተማነት፣ ለአገልግሎት አሰጣጥ፣ ለሸማቹ፣ ለባለሀብቱ፣ ለንግድና ለኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታን የፈጠረች እና የኮፍረንስ ቱሪዝም ማዕከል ከተማ እየሆነች ነው።” ብለዋል

በአዲስ አበባ ፕሮጀክቶችን ቀንና ሌሊት ሰርቶ በማጠናቀቅ፣ የንግድ እንቅስቃሴዎችን በምሽት ጭምር የሚካሄዱበት ምቹ ሁኔታ በመፍጠር የሚሰራው ስራ ከፍተኛ ለውጥ እያመጣና ለሌሎች ከተሞች ተምሳሌት የሆነ ሥራ መሆኑን ያነሱት ወረታው (ዶ/ር)፣ እስከአሁን ወደኋላ የቀረንበትን ለማካካስ፣ በከተሞች የሚታዩ ውስብስብ ችግሮችን ለማቃለልና ምርታማነትን ለማሳደግ የሥራ ባህሉን ህዝባዊ ማድረግ ላይ መስራት እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

በጥቅሉ ሀገራዊ ለውጡ ከመጣ ወዲህ ባለፉት ስምንት ዓመታት የኢትዮጵያ፣ የአፍሪካና የዓለም የዲፕሎማሲ መዲናዋ አዲስ አበባ በከፍተኛ ደረጃ ተለውጣለች፡፡ ይህንንም ነዋሪዎቿ ብቻ ሳይሆን አፍሪካውያን፣ ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች የመጡ፤ የቀድሞ ገፅታዋን የሚያውቋት አሁን ያሳየችውን ለውጥ እያነፃፀሩ በማድነቅ ሲናገሩና ሲጽፉ መስማት አዲስ አይደለም፡፡ በአዲስ አበባ በኮሪደርና በወንዝ ዳርቻ ልማት፣ በርካታ ሰው ተኮር ፕሮጀክቶችን በቀን ብቻ ሳይሆን በሌሊትም በማከናወን በአጭር ጊዜና በጥራት በማጠናቀቅ የተሰሩ ሥራዎች የከተማዋን ገፅታ ከመቀየር ባለፈ ለኢትዮጵያና ለአፍሪካ ከተሞች በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው፡፡

## አዳዲሶቹ ... ከገጽ 7 የዞረ

መንገድ ብቻ ሳይሆን ሱቆችም እንዳሉ በመረዳት እየመጡ እየተገበያዩ እንደሆነ ገልጻለች፡፡

ሌላኛው የስራ ዕድል የተፈጠረላቸው በፎቶ ኮፒ (የጽህፈት) አገልግሎት እየሰሩ የሚገኙት አቶ ተገኝ አለሙ ናቸው፡፡ አቶ ተገኝ በአንድ የመንግስት መስሪያ ቤት ይሰራሉ፡፡ ባለቤታቸው ደግሞ ከዚህ ቀደም ስራ ስላልነበራቸው ቤት ውስጥ ነበር የሚውሉት፡፡ የፕላዛውን መከፈት ተከትሎ በጨረታ በተመጣጣኝ ኪራይ ሱቅ ማግኘት እንደቻሉና በጀመሩት ስራም ተጠቃሚ እንደሆኑ ተናግረዋል፡፡

አካባቢው ከፍተኛ የትምህርት ተቋም የሚገኝበት በመሆኑ ለተማሪዎች ከጽህፈትና ፎቶ ኮፒ ጋር በተያያዘ የተለያዩ አገልግሎቶችን እየሰጡ እንደሚገኙም አክለዋል፡፡

### የፕላዛዎች ኢኮኖሚያዊ አበርክቶ

በተባበሩት መንግስታት በአስተዳደር፣ ድህነት እና ዘላቂ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ የፖሊሲ አማካሪ፣ በአፍሪካ ሰብዓዊ ኔትዎርክና የተለያዩ የጥናትና ምርምር ተቋማት ቦርድ ሰብሳቢና አባል በመሆን የሰሩት ቆስጠንጢኖስ በርኼተስፋ (ዶ/ር) ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት፣ በከተማዋ ተገንብተው ለአገልግሎት ክፍት እየሆኑ የሚገኙት ፕላዛዎች ዘርፈ ብዙ ፋይዳ አላቸው፡፡ ፕላዛዎች ሰዎች የሚገናኙባቸው፣ የሚገበያዩባቸው፣ የሚዝናኑባቸው ሰፋ ያሉና ክፍት ቦታዎች ያሉባቸው ናቸው፡፡ በአሜሪካ ታዋቂውን የኒውዮርክ ሴንትራል ፓርክን መጥቀስ ይቻላል፡፡ በአውሮፓና በተለያዩ አገራት ባሉ ከተሞችም የተለመዱ ናቸው፡፡

በአዲስ አበባ ከዚህ ቀደም ሰዎች በመንገድ ዳር፣ በቆርቆሮ በታጠሩ ቤቶች ውስጥ ይሰሩ ነበር፡፡ ፕላዛዎች መገንባታቸው በተደራጀ መልኩ በአንድ አካባቢ የተለያዩ ምርትና አገልግሎቶችን የሚያገኙበት ሁኔታ መፈጠሩ ኑሮን የሚያቀል፤ የከተማዋን ገፅታ የሚቀይርና ድምቀትን የሚያላብስ ነው፡፡ ተጠቃሚው ንጹህ፣ አድራሻው በታወቀ ቦታ የሚገበያይበት ሁኔታ መፈጠሩ ዋጋው በኢኮኖሚ ብቻ የሚመነዘር አይደለም። በሱቆች የሚቀመጡ ቁሳቁሶች፣ በካፌና ሬስቶራንቱ የሚስተናገዱ ሰዎች ደረጃውን በጠበቀ መልኩ አገልግሎት ማግኘታቸው ወይም መስጠታቸው በንጽህና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎችን በመከላከል ረገድ ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡

የምጣኔ ሀብት ምሁሩ ቆስጠንጢኖስ (ዶ/ር) እንደሚገልጹት፣ የድል ፕላዛ ተመርቆ መከፈቱ የከተማዋን ኢኮኖሚ በማነቃቃት ከፍተኛ ጥቅም ያስገኛል፡፡ ለምሳሌ፡- ከዚህ ቀደም በቂ የተደራጁ የመኪና ማቆሚያ ስፍራዎች ባለመኖራቸው፣ በከተማዋ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ መንገዶች ቀለም እየተቀቡ የመኪና ማቆሚያ ሆነው ነበር። አሁን ከፕላዛዎች ጋር የተደራጁ የመኪና ማቆሚያዎች በመሰራታቸው መንገድ ላይ አይቆሙም፤ በዚህም ምክንያት የትራፊክ እንቅስቃሴው የተሳለጠ ሆኗል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የትራፊክ አደጋን መቀነስ ተችሏል፡፡ በፕላዛዎች ለመገበያየት፣ ለመዝናናት፣ ለመገናኘት የሚመጡ ሰዎችም መኪናቸውን ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ በማቆም የሚፈልጉትን አገልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

ፕላዛዎች የህዝብ የጋራ መገልገያ የሆኑ የንግድ ሱቆች፣ የመኪና ማቆሚያዎች፣ የተለያዩ መዝናኛዎችን የሚያካትቱ የከተማ መታደስ ምልክቶች ናቸው፡፡ በዚህ ረገድ ፕላዛዎችን ማስፋፋት አዲስ አበባን የዓለም ከተሞች ከደረሱበት ደረጃ በማድረስ ህዝብን ተጠቃሚ የማድረጉ አካል እንደሆነ የምጣኔ ሀብት ምሁሩ ቆስጠንጢኖስ (ዶ/ር) ተናግረዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የድል ፕላዛና የቁርጡሚ የወንዝ ዳርቻ ልማት መጠናቀቅን አስመልክቶ በይፋዊ ማህበራዊ ትስስር ገጻቸው እንዳሰፈሩት፣ የአዲስ አበባ የኮሪደር ልማትና መልሶ ማልማት ስራ አነስተኛ ቢዝነሶችን የሚያዳክም ሳይሆን ይበልጥ ዘመናዊ፣ ለስራ እና ለሸማቹ ሳቢ በሆነ መንገድ እንዲሰሩ እድል ፈጥሯል፡፡ የድል ፕላዛ እና የቁርጡሚ ወንዝ ዳርቻ ቀደም ሲል ከቦሌ አትላስ እስከ ብራስ መንገድ በኮሪደር ልማቱ ምክንያት ተነስተው የነበሩ የንግድ ተቋማት በፕላዛው ውስጥ በተገነቡ ሱቆች ስራቸውን እንዲጀምሩ መደረጉን ለማሳያነት አንስተዋል፡፡

በጥቅሉ ፕላዛዎችና አደባባዮች በተለያየ መልኩ ለከተሞች የኢኮኖሚ እድገት ሞተር ሆነው ማገልገል ይችላሉ፡፡ በፕላዛው አካባቢ ያሉ የንግድ እንቅስቃሴዎችን በማነቃቃት፣ ኢንቨስትመንትንና ቱሪዝምን በማበረታታት፣ የስራ ዕድል በመፍጠር ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳላቸው በዘርፉ የተጻፉ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

## የዓለም ... ከገጽ 11 የዞረ

ከሰሞኑ ደግሞ ዝነኛው አሜሪካዊ የራፕ ሙዚቃ ኮከብና የዲጂታል ይዘት ፈጣሪ ዳሪል ድዌይን ግራንቤሪ (ዲዲጂ) አዲስ አበባን መጎብኘቱ ይታወቃል። ይህ ጉብኝትም ከተማዋ ለዓለም አቀፍ ዝነኞች ያላትን ሳቢነት ዳግም አረጋግጧል። አርቲስቱ በመዲናዋ እምብርት የሚገኘውን የዓድዋ ድል መታሰቢያን በጎበኘበት ወቅት፣ የጥቁር ሕዝቦች ኩራት በሆነው የዓድዋ ድል ታሪክና በጀግኖች አባቶች ገድል ዙሪያ ሰፊ ገለጻ ተደርጎለታል። ይህ ጉብኝቱ አዲስ አበባ የዘመናዊነት ብቻ ሳይሆን፣ ጥልቅ የታሪክና የማንነት መፍለቂያ መሆኗን ለተከታዮቹ ለማሳየት ትልቅ አጋጣሚ ፈጥሯል።

ዲዲጂ በመታሰቢያው ውስጥ የሚገኙ ታሪካዊ ቅርሶችን፣ የጀግኖችን ተጋድሎ የሚዘክሩ የጥበብ ስራዎችንና የድሉን ታላቅነት የሚያሳዩ ምስሎችን ተመልክቷል። አርቲስቱ በታሪካዊ ጉብኝቱ ብቻ ሳይወሰን፣ የኢትዮጵያን ባህላዊ የቡና ሥነ-ሥርዓት በሀገርኛ አቀራረብ በመታደም የሀገሪቱን ልዩ እንግዳ ተቀባይነት አድንቋል። ይህ በባህላዊ እሴቶችና በታሪክ የታጀበ ቆይታው፣ አዲስ አበባ የቱሪስት መዳረሻነቷን ከማሳደጉም ባለፈ የጥበብ ሰዎች የአፍሪካን ጥንካሬና ውበት የሚረዱባት ማዕከል መሆኗን አስመስክሯል።

የዲዲጂ እና የሌሎች አርቲስቶች ጉብኝት መዲናዋ ባለፉት ስምንት ዓመታት ያስመዘገበችውን የለውጥ ጉዞና የገነባቻቸውን ታላላቅ ፕሮጀክቶች ለዓለም የሚያስተዋውቅ ነው። ምክንያቱም እንደ ኡሙ ሳንጋሬ ሁሉ፣ ዲዲጂም በከተማዋ መሠረተ ልማትና በታሪካዊ ስፍራዎች አሰራር መገረሙ፣ አዲስ አበባ ለዓለም አቀፍ የጥበብ መድረክነት ያላትን ዝግጁነት ያሳያል። እንደነዚህ ያሉ የዝነኞች ጉብኝት ከተማዋ በመዝናኛ መዳረሻነት፣ በልማት፣ በውበትና በታሪክ እንድትታወቅ በማድረግ ረገድ የማይተካ ሚና ይጫወታሉ።

በአጠቃላይ፣ የአዲስ አበባ ያለፉት ዓመታት የለውጥ ጉዞ ለቱሪዝም ዘርፉ ከፍተኛ መነቃቃትን ከመፍጠሩም በላይ፣ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ የጥበብ መድረክ ላይ ያላትን ተጽዕኖ እያሳደገው ነው። ከተማዋ እያስመዘገበች ያለው እድገት በኪነ-ጥበብ ሰዎች እይታ፣ አዲስ አበባ የጥንታዊነትና የዘመናዊነት ስምምነት የሚንጸባረቅባት፣ ለፈጠራ ስራዎች ምቹና ለጎብኚዎች ማራኪ መሆኗን ያሳያል። ይህ ደግሞ መዲናዋ ወደፊትም የጥበብና የባህል አምባ ሆና እንድትቀጥል የሚያደርጋት ትልቅ መሠረት ነው።

# የቅጥር ማስታወቂያ

## የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከዚህ በታች በተገለጹት ክፍት የሥራ መደቦች ላይ አመልካቾችን አወዳድሮ ለመቅጠር ይፈልጋል።

| ተ.ቁ | የሥራ መደብ መጠሪያ | ደረጃ | ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ | አግባብ ያለው የሥራ ልምድ | የሙያ ዓይነት | መደብ መታወቂያ ቁጥር | ብዛት | የቅጥር ሁኔት | ደመወዝ | የሥራ ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ለሀብት አስተዳደር ዘርፍ** | | | | | | | | | | |
| 1 | የጉልበት ሠራተኛ | II | 8ኛ/10ኛ ክፍል ያጠናቀቀ | 2/0 ዓመት | ቀለም | አ/18.984 እስከ አ/18.987 | 4 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሠረት | አ/አ |
| **ለቋንቋዎች ዘርፍ** | | | | | | | | | | |
| 2 | የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ዶክመንተሪ አዘጋጅ | XII | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 7/5ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቲያትሪካል አርት፣ በህግ፣ እንዲሁም በጤና፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ፣ በማህበራዊ ሳይንስ፣ በሥነ ትምህርት ዘርፎች ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.673 | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሠረት | አ/አ |
| 3 | የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ትምህርታዊ ከፍተኛ ሪፖርተር | X | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 5/3 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቲያትሪካል አርት፣ በህግ፣ እንዲሁም በጤና፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ፣ በማህበራዊ ሳይንስ፣ በሥነ ትምህርት ዘርፎች ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.675 | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሠረት | አ/አ |
| 4 | የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ዶክመንተሪ ረዳት አዘጋጅ | XI | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 6/4 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቲያትሪካል አርት፣ በህግ፣ እንዲሁም በጤና፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ፣ በማህበራዊ ሳይንስ፣ በሥነ ትምህርት ዘርፎች ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.681 | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሠረት | አ/አ |
| 5 | የእንግሊዘኛ ቋንቋ ከፍተኛ ሪፖርተር | X | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 5/3 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቲያትሪካል አርት፣ በህግ፣ እንዲሁም በጤና፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ፣ በማህበራዊ ሳይንስ፣ በሥነ ትምህርት ዘርፎች ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.802 | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሠረት | አ/አ |
| 6 | የእንግሊዘኛ ቋንቋ ረዳት አዘጋጅ | XI | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 6/4 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቲያትሪካል አርት፣ በህግ፣ እንዲሁም በጤና፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ፣ በማህበራዊ ሳይንስ፣ በሥነ ትምህርት ዘርፎች ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.798 | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሠረት | አ/አ |

**ማሳሰቢያ፡-**

1. አመልካቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10/አስር/ ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የትምህርት ማስረጃችሁን ዋናውንና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ በመያዝ በተቋሙ የሰው ኃብት ሥራ አመራር እና ልማት ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 05 ድረስ በመምጣት እንድትመዘገቡ እናሳስባለን፡፡
2. ከግል ድርጅቶች የሚቀርብ የሥራ ልምድ ማስረጃ የሥራ ግብር የተከፈለበት ስለመሆኑ ከግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ማስረጃ ማምጣት ይኖርባቸዋል፡፡
3. የስራ ልምድ የሚጠይቀው ከወጣው ክፍት መደብ ጋር ቀጥተኛ መሆን አለበት፡፡
4. በቴክኒክና ሙያ/ሌቬል የሚወዳደሩ የብቃት ማረጋገጫ/COC ማቅረብ አለባቸው፡፡
5. የምዝገባው ቀን ከመጋቢት 28/2018ዓ.ም እስከ ሚያዝያ 12 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ
6. የፈተና ቀን በውስጥ ማስታወቂያ ይገለፃል፡፡
7. ለበለጠ መረጃ አድራሻ አምስት /5/ ኪሎ ቅድስተ ማርያም ፊት ለፊት ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን ስልክ 0111551848

## አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ

**የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ**

ከላይ በርዕሱ ለመግለፅ እንደተሞከረው የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በወረዳ 13 ደመቀ ወልደሚካኤል ስም የተመዘገበ ኮንዶሚኒየም ቤት የቤቱ ልዩ መለያ ቁጥር AA000051304443253000004 የተሰጠበት ቀን 27/05/2013 ዓ/ም የሆነ የሙብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንደጠፋባቸው በቁጥር የካ/ወ/ቁ/151/11796 በቀን 22/07/2018 ዓ.ም የሚገልፅ መረጃ በማቅረብ አመልክተዋል፡፡ ይህም በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታውን አይቻለው ወይም ሙብት አለኝ የሚል በ90 ቀናት ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ ቀርቦ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ምትክ ሰርተፍኬት የሚሰጥ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 ህብረት ስራ ጽ/ቤት ተደራጅቶ የሚገኘው ሮሆቦት ኃላ/የተ/ቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበር በአደረገው ጠቅላላ ጉባኤ ማህበሩ እንዲፈርስ በሙሉ ድምፅ የተወሰነ በመሆኑ ይህን የማህበሩን መፍረስ የሚቃወም ወይም ይገባኛል የሚል አካል ካለ በአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 92 መሰረት ጋዜጣው አየር ላይ ከዋለ ጀምሮ በ2 ወራት ውስጥ ተቃውሞውን በአካል በመቅረብ ለአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ኅብረት ሥራ ጽ/ቤት ቢሮ ቁጥር 505 እንዲያቀርብ እየገለጽን በዚህ ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ንብረት የመጠየቅ መብት የሌለው መሆኑን በመግለጽ ጥሪ እናስተላልፋለን፡፡

**በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ አስተዳደር ኅብረት ሥራ ጽ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 አስተዳደር ውስጥ በካርታ ቁጥር 043224 ሴሪ.ቁጥር 119540 አሳምነው ፈለቀ ተስፋዬ የተመዘገበ ይዞታ ማህደራቸው ከማህደር ክፍላችን መገኘት የነበረበት የጠፋባቸው ስለሆነ ማህደሩን የያዘ ግለሰብ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ድረስ መጥተው ካላሳወቁ ማህደር በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 5 ክልል ውስጥ በላንቺሁን ቢዝነስ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ስም በይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA 000070502992 ሴሪ ቁጥር L 0120508 በሆነ የተመዘገበው ይዞታ፤ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ/የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጁ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን 21/07/2018 ዓ.ም ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 አስተዳደር ውስጥ በካርታ ቁጥር 028699 በሴሪ ቁጥር 013794 በአቶ ከበቡ ዘርጋ ስዋረ የተመዘገበ ይዞታ ማህደራቸው ከማህደር ክፍላችን መገኘት የነበረበት የጠፋባቸው ስለሆነ ማህደሩን የያዘ ግለሰብ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ድረስ መጥተው ካላሳወቁ ማህደር በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

መዲሃ መሃመድ አህመድ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 የካርታ ቁጥር ቦሌ12/3/3/9/57-6012/215352/02 የሆነው ይዞታ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቁን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክፍለ ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

አቶ ከበደ ካሳ እና በተጋሪ ወ/ሮ የሺወርቅ ወርቁ በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 2 የቤት ቁጥር 393 በካርታ ቁጥር 02/08/10516/00 የተመዘገበው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በማህደር ውስጥ መገኘት የነበረበት ካርታ ከነማህደሩ የጠፋ በመሆኑ ይህን አስመልክቶ የሚቀርብ ማንኛውም ተቃዋሚ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ በ30 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ መሬት ልማት አስተዳደር ጉለሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማስረጃውን ይዞ ካልቀረበ ካርታው እንደጠፋ ተቆጥሮ በምትኩ አዲስ ካርታ በማዘጋጀት አገልግሎቱን የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የጉለሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ለ/ኩራ9/35/3/43861/150/11/00 ሴሪ ቁጥር 1676102 ሊድያ ታደሰ ደምሴ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ እናት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ልናደራጅላቸው ስለሆነ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ መመሪያው በሚፈቅደው መሠረት ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ጌታቸው ዘነበ ወልደአረጋይ በጉ/ክ/ከተማ ወረዳ 08 የቤት ቁጥር 735 የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000100804151 በሴሪ ቁጥር R064546 የሆነው ይዞታ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ/ሰርተፍኬት/ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግንቸዋለው/ይዥዋለው/ የሚል ሰው ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረበ በምትኩ ሌላ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ/ሰርተፍኬት/ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ጉለሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ምትኩ ወ/ጊዮርጊስ በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 5 የቤት ቁጥር - በካርታ ቁጥር ጂ.አይ.ኤስ 9766 የተመዘገበው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በእጃቸው ላይ መገኘት የነበረበት የጠፋ በመሆኑ ይህን አስመልክቶ የሚቀርብ ማንኛውም ተቃዋሚ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ በ30 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጉለሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማስረጃውን ይዞ ካልቀረበ ካርታው እንደጠፋ ተቆጥሮ በምትኩ አዲስ ካርታ በማዘጋጀት አገልግሎቱን የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የጉለሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

የአቶ መላክ ቢምረው ገ/ሚካኤል በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 12 ክልል ውስጥ ነዋሪ የሆኑ ካርታ ቁጥር ቦሌ12/42/3/3/36882/256914/01 ሴሪ ቁጥር 056385 ተመዝግቦ የነበረው ኦሪጅናል/ዋናው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋባቸው በተለያየ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባለው 30 ቀናት ውስጥ በቦሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ካልቀረበ በምትኩ ሌላ አዲስ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማት አስተዳደር ቢሮ ቦሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ቦሌ9/85/7/3/11223/00 ሴሪ ቁጥር 1448516 በኤስኤን ቢ. ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ እናት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ልናደራጅላቸው ስለሆነ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ መመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ሮማን ገብረክርስቶስ ያሬድ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 10 የሚገኘው የይዞታ ካርታ ቁጥር AA00006100261230402l7 የሆነው ሰርተፊኬት ተመዝግቦ የሚገኘውን ቤት ባለቤትነት ካርታ ሴሪ ቁጥር C.036291 ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግንቸዋለሁ የሚል ግለሰብ ይሁን ሌላ አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካላቀረበ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት/ካርታ ተዘጋጅቶ እንደምንሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የለሚ ኩራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 በሴሪ ቁጥር R 002658 በይዞታ መለያ ቁጥር AA000010700139 በወ/ሮ እህተ ደግፌ ቅጣው ስም በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የተሰጣቸው የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (ካርታ) የጠፋብን በመሆኑ ምትክ ይሰጠን በማለት ያመለከቱ በመሆኑ ይኸው የይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (ካርታ) በእኔ እጅ ይገኛል ይዤዋለሁ የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በአየር ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ በአዋጅ ቁጥር 1381/2017 አንቀፅ 36(3) መሰረት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አራዳ ክፍለ ከተማ መሬት ይዞታ መዝገባና መረጃ ቅ/ጽ/ቤት በመቅረብ እንዲያመለክት ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የአራዳ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ታሪኩ መብራቱ ቸርነት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 ካርታ ቁጥር ቦሌ11/68/9045/00 በሴሪ ቁጥር 014930 የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ/የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክፍለ ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

መለሰ ሊራንሶ ኤርሳዶ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከ/ወረዳ 1 የሚገኘው ካርታ /የይዞታ ልዩ መለያ/ ቁጥር AA000080126917 ሴሪ ቁጥር 0162331 በጽ/ቤታችን በስማቸው የተመዘገበ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት /ካርታ/ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

# ከመሠረተ ልማት ግንባታ እስከ ተቋማዊ ድጋፍ



ፎቶ- ከፋይል
በከተማዋ ባለፉት 8 ዓመታት በሺህ የሚቆጠሩ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ተገንብተዋል

**በሳህሉ ብርሃኑ**

የአንዲት ዘመናዊ ከተማ ውበት የሚለካው በሰፋፊ መንገዶቿና በረጃጅም ሕንጻዎቿ ብቻ ሳይሆን፣ በስፖርት ዘርፉም ጭምር ነው። ይህንን በተገቢው የተረዳችው አዲስ አበባ፣ የስፖርቱ ዘርፍ እንደ አንድ የመዝናኛ ዘርፍ ብቻ ሳይሆን፣ እንደ ከተማ ግንባታና የወጣቶች ሰብዕና መቅረጫ ቁልፍ መሣሪያ ተደርጎ ተወስዷል። ባለፉት ጥቂት ዓመታት በአዲስ አበባ የታዩት የመጫወቻ ሜዳና የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ግንባታ ለዚህ ትልቅ ማሳያ ናቸው። ከታላላቅ ስታዲየሞች ባለፈ፣ በየአካባቢው የተገነቡትና ዘመናዊ ሰው ሠራሽ ሣር የተነጠፈባቸው ሜዳዎች፣ ስፖርቱ በሰፈር ደረጃ እንዲያንሰራራና ተተኪ ስፖርተኞችን ለማፍራት ምቹ ሁኔታን ፈጥረዋል።

ይህ የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ስፖርቱን ለሁሉም ተደራሽ ከማድረጉም በላይ፣ ከተማዋ ለታላላቅ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ስፖርታዊ ኩነቶች ዝግጁ እንድትሆን አድርጓታል ማለት ይቻላል። እዚህ ጋር ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ አበባ ዓለም አቀፍ የአትሌቲክስ ውድድር ለማዘጋጀት ዕድል ማግኘቷን በማሳያነት ጠቅሰን እንለፍ። በከተማዋ እየተካሄደ ያለው የኮሪደር እና የወንዞች ዳርቻ ልማት ሥራዎች ከስፖርት እንቅስቃሴ ጋር በቅርበት የተሳሰሩ ናቸው። ለብስክሌት መንዳትና ለእግር ጉዞ የተዘጋጁ መንገዶች እንዲሁም በፓርኮች ውስጥ የተካተቱ የስፖርት መገልገያዎች አዲስ አበባን የስፖርት ከተማ ለማድረግ የታለሙ ናቸው።

የስፖርት ተንታኞችና የዘርፉ ባለሙያዎች እንደሚጠቁሙት፣ አዲስ አበባ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ለስፖርቱ የሰጠችው ትኩረት ከወትሮው የተለየና ስልታዊ ነው። ባለሙያዎቹ እንደሚሉት፣ ስፖርት ከሜዳ ላይ ውድድር ባለፈ የከተማዋን ገጽታ በመገንባት፣ የቱሪስት መስብህ በመሆንና ወጣቶችን ከሱሰኝነትና ካልተገቡ ተግባራት በመታደግ ረገድ የላቀ ሚና አለው። በተለይም በኮሪደር ልማት ውስጥ የተካተቱት የብስክሌትና የእግር ጉዞ መንገዶች፣ እንዲሁም በየሰፈሩ የሚገነቡ የስፖርት መሠረተ ልማቶች ከተማዋን ለነዋሪዎቿ ምቹና ጤናማ እያደረጓት መሆኑን ይገልጻሉ።

የመዲናዋ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በአብዛኛው ተለውጠዋል በሚለው አስተያየት የ"አዲስ ተስፋችን" እግር ኳስ ፕሮጀክት መሥራችና አሰልጣኝ መሐመድ ናስር ይስማማል። "የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች የአዳጊና ወጣት ፕሮጀክቶች ስፖርቱን ለማስፋፋትና ለማሳደግ ዋነኛ መሠረቶች ናቸው" የሚለው አሰልጣኝ መሐመድ፣ አሁን ላይ በመዲናዋ በሲኤምሲ አካባቢ ከ7 እስከ 17 ዓመት ያሉ አዳጊዎችን በፕሮጀክት አቅፎ በማሰልጠን ላይ ይገኛል። "የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በአሳሳቢ ሁኔታ እየቀነሱ ነው" የሚለው ረዥም ዓመታትን ያስቆጠረው ቅሬታም መፍትሔ እያገኘ ስለመሆኑ ያስረዳል።

በተለይም ባለፉት ስምንት የለውጥ ዓመታት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርትን ከከተማዋ ውበትና ከነዋሪዎች ጤና ጋር በማስተሳሰር፣ ንቁና አምራች ዜጋ ለመፍጠር የጀመረው ሥራ፣ ዛሬ እንደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ያሉ አንጋፋ ክለቦችን ከመፍረስ እስከ መታደግ የደረሰ ሰፊ እይታ ያለው መሆኑን ያረጋግጣል። የከተማ አስተዳደሩ ለስፖርቱ የሰጠው ትኩረት በግንባታ ብቻ የተወሰነ አይደለም፤ የክለቦችን ተወዳዳሪነትና የፋይናንስ አቅም ለማጠናከርም ልዩ ልዩ ስልቶችን ሲተገብር ቆይቷል።

በተለይም በከተማዋ ሥር የሚገኙ ክለቦች በበጀት እጥረት ሳይንገላቱ ውጤታማ እንዲሆኑ አስፈላጊው ድጋፍ የሚደረግበትን አሠራሮች ዘርግቷል። አሁን ላይ ለቅዱስ ጊዮርጊስ እግር ኳስ ክለብ የተደረገው ድጋፍም የዚሁ ዕቅድ አካል ሲሆን፣ የከተማ አስተዳደሩ የግሉ ዘርፍ በስፖርቱ ላይ ኢንቨስት እንዲያደርግና በስፖርት ማኅበራዊ ኃላፊነቱን እንዲወጣ በማነቃቃት ረገድ የላቀ ሚና ተጫውቷል። ይህ ጥረትም ክለቦች ራሳቸውን ችለው በጠንካራ የፋይናንስ መሠረት ላይ እንዲቆሙና የከተማዋን ዝና በዓለም አቀፍ መድረክ እንዲያሳድጉ ያለመ ነው።

ባለፉት ሰማንያ ዘጠኝ ዓመታት የኢትዮጵያ እግር ኳስ መተንፈሻ ሳንባ ሆኖ የዘለቀው ይህ ፈር ቀዳጅ ክለብ፣ ከገጠመው የፋይናንስ ችግር የተነሳ ሕልውናው አደጋ ላይ ወድቆ ሰንብቷል። ይሁን እንጂ የአዲስ አበባ ከተማ

በየአካባቢው የተገነቡትና ዘመናዊ ሰው ሠራሽ ሣር የተነጠፈባቸው ሜዳዎች፣ ስፖርቱ በሰፈር ደረጃ እንዲያንሰራራና ተተኪ ስፖርተኞችን ለማፍራት ምቹ ሁኔታን ፈጥረዋል

አስተዳደር "ታሪክ አይፈርስም" በሚል በወሰደው ቁርጠኛ እርምጃና ባሰባሰበው የ100 ሚሊዮን ብር ድጋፍ፣ የክለቡን መጻኢ ዕድል ብሩህ የሚያደርግ አዲስ ምዕራፍ ከፍቷል።

ቅዱስ ጊዮርጊስ ክለብ ከሜዳ ላይ እንቅስቃሴው ባለፈ፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ደጋፊዎቹ ልብ ውስጥ የሚኖር ትልቅ ሰብዕና ነው። ክለቡ የገጠመው የፋይናንስ ቀውስ በደጋፊው ዘንድ የፈጠረው ሥጋትና ጭንቀት ቀላል ባይሆንም፣ የመንግሥት ድጋፍ ግን የደጋፊውን ተስፋ መልሶ ያለመለመ ሆኗል። የቅዱስ ጊዮርጊስ ደጋፊዎች እንደገለጹት ይህ ድጋፍ ከገንዘብ በላይ የከተማዋን የስፖርት ወግ የመጠበቅ ትልቅ ኃላፊነት መገለጫ ነው።

አዲስ አበባ በኮሪደር ልማትና በመሠረተ ልማት ግንባታ አዲስ መልክ እየያዘች ባለችበት በዚህ ወቅት፣ የከተማዋን ስም የሚሸከሙ እንደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ያሉ አንጋፋ የእግር ኳስ ክለቦች መዳከም ለከተማ አስተዳደሩ የማይታለፍ ጉዳይ ሆኗል። መንግሥት ለክለቡ ሕልውና ማስቀጠያ ፈሰስ ያደረገው 100 ሚሊዮን ብር ድጋፍ፣ የከተማ ግንባታ ሥራ ከድንጋይና ከኮንክሪት ባለፈ ማኅበራዊ እሴቶችን መታደግ መሆኑን ያረጋገጠበት ክስተት ሆኖ ተመዝግቧል።

ለወራት የዘለቀ የደመወዝ እጦት፣ የተጫዋቾች መበተን ሥጋትና የክለቡ ደጋፊዎች ጭንቀት... የታሪካዊው የቅዱስ ጊዮርጊስ ስፖርት ክለብ ሰማይ ላይ ያንዣበበው ጥቁር ደመና በመንግሥትና በባለሀብቶች የተቀናጀ ጥረት ሊገፈፍ ችሏል። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሪነቱን ሚና በመውሰድና የግል ኢንቨስትመንት ግዙፎችን በማስተባበር ያበረከተው የገንዘብ ድጋፍ፣ ክለቡን ከመፍረስ አፋፍ ከመታደጉም በላይ ወደ ቀድሞ ክብሩ የሚመለስበትን በር ከፍቶለታል።

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ እንደገለጹትም ቅዱስ ጊዮርጊስ የእግር ኳስ ክለብ የተጫዋቹ እና የማኅበሩ ብቻ ሳይሆን የከተማዋ ጠንካራ ክለብ ነው። "በመሆኑም ይህንን አገራችንን እና ከተማችንን የወከለ ታሪካዊ የስፖርት ክለብ ከመፍረስ የመታደግ ኃላፊነት እንዳለብን እናምናለን" ብለዋል።

ከንቲባዋ አያይዘውም ይህ አንጋፋ የስፖርት ክለብ ላለፉት 6 ወራት ደመወዝ መክፈል የማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሶ እና የመበተን አደጋ ተጋርጦበት መታየት ስለሌለበት የከተማ አስተዳደሩን በጀት በመወሰን፣ ለባለሀብቶች በቀረበው ጥያቄ መሠረት ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ እና ቢጂአይ ኢትዮጵያ በሰጡን ፈጣን ምላሽ በጥቅሉ የ100 ሚሊዮን ብር ድጋፍ ለተቋቋመው ጊዜያዊ ኮሚቴ ስለማስረከባቸው ገልጸዋል።

ከንቲባዋ በማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው ባሰፈሩት ጽሑፍ "ይህ ድጋፍ አስተዳደራችን ክለቡን ከውድቀት ለመታደግ እና ለስፖርት ወዳድ ሕዝብ የሰጠው ክብር አንዱ ማሳያ ሲሆን፤ ቅዱስ ጊዮርጊስ የእግር ኳስ ክለብ ሁሉንም ባሳተፈ እና በግልጽነት አዲስ ቦርድ መርጦ ከገጠመው ጊዜያዊ ችግር ተላቅቆ ወደ ቀድሞ ጥንካሬውና ዝናው የሚመለስበት ጊዜ ቅርብ እንዲሆን እመኛለሁ" ብለዋል።

የቅዱስ ጊዮርጊስ እግር ኳስ ክለብ በማኅበራዊ ትስስር ገጹ ባሰፈረው መልዕክት "ክለባችን የገባበትን ችግር ተረድተው ትኩረት በመስጠት ለሰጡን ድጋፍ እና ቆራጥ አመራር እናመሰግናለን። ክብርት ከንቲባ ስለ ቅዱስ ጊዮርጊስ ታሪካዊነት እና ስላለው ዋጋ በተገቢው መልኩ በመረዳትዎም ምስጋናችን ላቅ ያለ ነው" ብሏል።

አያይዞም "ራሳችንን የኢትዮጵያ እና የአዲስ አበባ ክለብ ነን ብለን ስንጠራም በእንዲህ ዓይነት ቀን ከተማችን ከጎናችን እንደምትሆን በማመን ነበር፤ በእርስዎ ተግባር አዲስ አበባ እና ቅዱስ ጊዮርጊስ የማይነጣጠሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ መሆናቸውን አረጋግጠናል" የሚል መልዕክትም አስተላልፏል።

ከተማዋን ለነዋሪዎቿ ምቹ የማድረግ ሥራው የሚጠናቀቀው ስፖርታዊ ማዘውተሪያዎች በታሪካዊ ክለቦች ሲሞቁ ነው። የቅዱስ ጊዮርጊስ እግር ኳስ ክለብ የተጫዋቹ እና የማኅበሩ ብቻ ሳይሆን የከተማዋ የጥንካሬ መገለጫ ነው። ይህ 100 ሚሊዮን ብር ለክለቡ የተሰጠ ገንዘብ ብቻም ሳይሆን የከተማዋ አስተዳደር ለስፖርት ወዳዱ ሕዝብ ያለውን ክብርና ተቆርቋሪነት በተግባር ያሳየበት ነው። እግር ኳስ ክለቡ ሁሉንም ባሳተፈ እና በግልጽነት አዲስ ቦርድ መርጦ ከገጠመው ጊዜያዊ ችግር ተላቅቆ ወደ ቀድሞ ጥንካሬውና ዝናው የሚመለስበት ጊዜ ቅርብ እንደሚሆን ይጠበቃል።